ዐብይ ርዕስ



“ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነጻነት ቀንዲልና መሰባሰቢያ ማዕከል መሆኗ ይቀጥላል”

ገፅ 3

የሕዝብ ሀብትና ልማት



የሳይበር ምኅዳሩን ያለ ስጋትና ያለ ጥቃት!

ገፅ 16

የዕውቀት በር



አካል ጉዳተኞችን እኩል ተጠቃሚ ያላደረገው የትምህርት ስርዓት

ገፅ 24

መዝናኛ



የተዘነጋው የፑሽኪን ሐውልት

ገፅ 32

ዘመን ኅዳር 2014

# ርዕሰ አንቀጽ

## ያለን ምርጫ፣ መክተት ብቻ!

አሸባሪው ሕወሓት መራሹ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ ጀምሮ ያለፉት 30 ዓመታት የጋራ መስተጋብራችንን የሚበጥስና አብሮነትን የሚንድ በርካታ ተግባራትን ፈፅሟል። መለያየትን ሥርዓታዊና ሕገ መንግሥታዊ መሠረት በማስያዝ፣ የተጨቆኑ ማንነቶችን እውቅና ለመስጠት በሚል ሽፋን ኢትዮጵያዊነት እንዲፈርስ ቀላል የማይባል ዘመቻ አከናውኗል። ለአገር ክብርና ለሕዝቦች አንድነት የተጋደሉ ብዙዎችን ገድሏል፣ተሰደው አገር አልባ ሆነዋል።

በተባበረ ሕዝባዊ ትግል ከፈላጭ ቆራጭነቱ ሲሸኝ ግን የሠራው ሴራ መክኖ፣ ያወረደው መዓት ተገቶ የሀገር አንድነትን ማስቀጠል ወደሚያስችል አዲስ ምዕራፍ መሸጋገር ተችሏል። በአገራችን አዲስ የለውጥ ጅምርና የመደመር ቀንዲል መለኮሱ ደግሞ አዲስ ተስፋ አጭሯል። ይሁን እንጂ ከማእከል ተገፍቶ የወጣው ይህ አሸባሪ ኃይል ባለፉት ሦስት ዓመታት የነበረውን የለውጥ ሂደት ከመፈታተን አልቦዘነም። በተለይም ከስምንት ወራት ወዲህ በሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይን ሲያስተዳድር በነበረው ይህ ጠንቀኛ ቡድን በለኳሽነት ጦርነት መቀስቀሱ የለውጡን ሂደት ፈተና አክብዶታል።

ይህ አደገኛ ኃይል ራሱን ወደ ጁንታነት ቀይሮ ሥርዓተ መንግሥቱን ለማፍረስ በመሞከሩ፣ ራሱንና የወጣበትን ማኅበረሰብ ለከፋ ችግር አጋልጧል። አካባቢው እንዳይረጋጋ፣ ቀውሱ እንዳይቆም፣ ሕዝቡም መከራ በዛብኝ ብሎ በመንግሥቱ ላይ ይበልጥ እንዲማረር እየሠራ ነው። ከዚያም አልፎ በውሸት ፕሮፖጋንዳ ዓለምን በማሳሳት የውጭ ኃይሎች በአገር ላይ ጫና እንዲያደርሱ አድርጓል። አሸባሪው ሀገር በማፍረስ፣ዜጎችን በመግደል፣ በማፈናቀል፣ ዘግናኝ ጭፍጨፋ በመፈጸም፣ ጥላቻ በመስበክ እንቅስቃሴውን ቀጥሏል። ከሀገራችን ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በግልጽ እየሠራም ነው። በአጎራባች ክልሎች ወረራዎችን ፈጽሟል። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን አንድ መገንዘብ ያለብን ቁምነገር ማንም ይሁን ማን ሕግን ጥሶ፣ በእብሪት ሥርዓትን ገርስሶ እንዲኖር መፍቀድ ዘላቂ ጉዳትን በራሳችንና በቀጣይ ትውልድ ላይ መጋበዝ መሆኑን ነው። አንድነታችንም ሆነ ሰላማችን ሊጠበቅ የሚችለው ሕግና ሥርዓት ሲከበር፣ አሸባሪና ከሃዲ ኃይሎች ሲቀጡ፣ ለየትኛውም ጫና ሳንበረከክ የጉዟችንን እንቅፋት ለመጥረግ ስንረባረብ ነው!!

በመሆኑም ወቅቱ አገርን ለመበታተን ቆርጦ ከተነሣ አሸባሪ ቡድን ጋር እየተፋለምን የምንገኝበት ነው። ደኅንነታችንን ማስጠበቅ የምንችለው፣ ሀገር እንዲኖረን ማድረግ የምንችለው ይህን ኃይል በአንድነት ቆመን በመመከት ብቻ ነው። ጠላት ከመሣሪያው በላይ በምላሱ ሳያሸብረን፣ አንድነታችን ሳይፈተን፣ ከሠራዊታችን ጎን መቆም አማራጭ የሌለው ነው። በተለይ በጠላት የፕሮፖጋንዳ ታክቲክ ሳንፈታ፣ በጊዜያዊ ችግሮች ልባችን ሳይከፈል ወቅቱን የሚመጥን ስነ-ልቦና መያዝ ይኖርብናል። ወቅቱ የህልውና ጦርነት እየተካሄደበት ያለበት ወቅት በመሆኑ በህልውና ዘመቻው መንግሥት ያስተላለፈውን የክተት ጥሪ በመቀበል ራስን አዘጋጅቶ እና ተደራጅቶ ጠላት በመጣበት አግባብ ምላሽ መስጠት አማራጭ የሌለው ነው።

# መን እንጠይቅልዎ?

**ስሜነህ ደስታ**

በማሕበረሰብ ዐቀፍ ጤና መድኅን ተቋም ውስጥ አባል ለሆኑ ግለሰቦች ከዚህ በፊት በመንግሥት ህክምና ተቋማት በሀኪም በታዘዘው መሠረት የአባልነት መታወቂያቸውን እያሳዩ በከነማ ፋርማሲዎች መድኃኒቶች ይወስዱ ነበር። በተለይ በ2014 ዓ.ም. የተለያዩ መድኃኒቶችን የከነማ ፋርማሲዎች «አትስጡ ስለተባልን ከፈለጋችሁ በገንዘብ ግዙ ብለውናል፤ለምን ስንል ተገቢ ምላሽ የሚሰጠን አላገኘንም» የሚል ቅሬታ በተጠቃሚ አባላት ሲነሳ ይሰማል። ይህን ለማጣራት ወደ ከነማ መድኃኒት ቤት በመሄድ የቅሬታ አቅራቢን ሀሳብ፣ የቅርንጫፍ መድኃኒት ቤቱን ኃላፊ እንዲሁም የከነማ መድኃኒት ቤቶች ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ከከነማ መድኃኒት ቤት ጋር ውል የገባውን ክፍለ ከተማ በማናገር ምላሽ አቅርበናል።

**ቅሬታ ፡-** ወይዘሮ አይናለም ገብረፃዲቅ ልጃቸው ስለታመመችባቸው ከየካቲት 12 ሆስፒታል የተሰጣቸውን የመድኃኒት ማዘዣ ይዘው አንበሳ ግቢ ከሚገኘው የከነማ መድኃኒት ቤት ለመውሰድ ልጃቸውን አዝለዋት መጥተው አግኝተናቸዋል። የአባልነት መታወቂያቸውን እና የመድኃኒት ማዘዣውን አያይዘው ለባለሙያዋ ሲሰጧት «ይህ መድኃኒት በነጻ አይሰጥም፤ከፈለግሽ በገንዘብ መግዛት ትችያለሽ። ይህ የተሰጠን ትዕዛዝ ነው» መባላቸውን ይገልጻሉ። ከልጇ በላይ የሚሆን የለም በማለት የተጠየቁትን 381.60(ሶስት መቶ ሰማንያ አንድ ብር ከስልሳ ሳንቲም) ሲከፍሉም ተመልክተናል። «አይሰጥም ከተባለ ማንን እጠይቃለሁ? ምላሽ የምታገኙ ከሆነ እናንተ ጠይቁ» በማለት ቅሬታቸውን አሰምተዋል።

**የአንበሳ ግቢ ከነማ መድኃኒት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ትዕግስት ኃይሌ፡-** ቀደም ሲል በመንግሥት ተቋማት ሀኪም ከታዘዘ እንዲሁም በተቋማቱ ውስጥ መድኃኒቱ አለመኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ይዘው እስከመጡ ድረስ አባል ለሆኑ ግለሰቦች በከነማ መድኃኒት ቤት ያለውን መድኃኒት ያለልዩነት እንሰጥ ነበር። አሁን ግን "ብራንድ" የሆኑ መድኃኒቶች እንዳይሰጡ "በጀነሪክ"(በጽንስ ስም) እንዲሰጥ የሚል ከዋናው መሥሪያ ቤት በደብዳቤ ደርሶናል። ለአባላቶቹ በጀነሪክ የታዘዙትን በነጻ እንሰጣለን፤በብራንድ የታዘዙትን በነጻ አንሰጥም። ግለሰቦቹ ከፈለጉ በገንዘብ እንዲወስዱ እናደርጋለን።

**የከነማ መድኃኒት ቤት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ምስጋናው ከበደ ፡-** ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ በክፍለ ከተማ ጤና ጽ/ቤት ደረጃ ከሚያስተባብረው አካል ጋር መድኃኒት የምንሰጥበትን ስርዓት በተመለከተ ውል ገብተን ለአባላት በከነማ መድኃኒት ቤት ውስጥ ያሉትን ማንኛውንም መድኃኒት ስንሰጥ ቆይተናል። ለአባላት የሰጠናቸውን መድኃኒቶች ማስረጃ በማቅረብ ገንዘቡን ከሶስት ወር በኋላ ከየክፍለ ከተሞቹ እንቀበላለን። አሁን ግን መድኃኒቶች መሰጠት ያለባቸው በጀነሪክ ስማቸው ነው፤ በብራንድ ስማቸው እንዳይሰጥ የሚል ደብዳቤ ከሁሉም ክፍለ ከተሞችና ጤና ቢሮ ተሰጥቶናል። ስለሆነም ለአባላቱ በጀነሪክ ስም ብቻ የታዘዙትን ነው እየሰጠን ያለነው። ብራንድ መድኃኒቶች ደግሞ በባህሪያቸው ውድ ናቸው። ለአባላቶቹ የምንሰጣቸው መድኃኒቶች ቀደም ሲል እንደነበረው በወቅቱ እየተከፈለን አይደለም። በአጠቃላይ ከአርባ ሚሊዮን ብር በላይ ያልተከፈለ ገንዘብ አለን። ለዚህም የሚሰጡን ምክንያት በካዝናቸን ውስጥ ገንዘብ ስለሌለ ታገሱን የሚል ነው።

**የአራዳ ክፍለ ከተማ የማሕበረሰብ ዐቀፍ ጤና መድኅን ሥራዎች አስተባባሪ አቶ እስጢፋኖስ ነጋሽ፡-** በብራንድ ስም የሚሰጡ መድኃኒቶች ዋጋቸው ውድ ስለሆነ በከነማ መድኃኒት ቤቶች እንዳይሰጡ ደብዳቤ መሰጠቱን ገልጸው ይህም የሆነው ከደረሰ ከፍተኛ የበጀት እጥረትና ውልን መስመር ለማስያዝ ሲባል መሆኑን አስረድተዋል። ሀኪሞች ለአባላት በብራንድ መድኃኒት እንዳያዙ ለሁሉም ጤና ጣቢያዎችና ሆስፒታሎች ደብዳቤ ስለተሰጠ በአባላትና በከነማ መድኃኒት ቤቶች መካከል ይከሰት የነበው ውዝግብ መፍትሔ እንደሚያገኝም ተናግረዋል።


**በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እየታተመ የሚወጣ**

ዋና አዘጋጅ፡- ሳሙኤል ይትባረክ
ፖ.ሣ.ቁ፡- 30145
ስልክ፡- 011-1264207
Sammes.zellek@gmail.com
zemenpress@gmail.com
ከፍተኛ አዘጋጆች፡- ማለደ ዋስይሁን
ስሜነህ ደስታ

አዘጋጆች፡- የትናየት ፈሩ
ሀብታሙ ስጦታው
ዮርዳኖስ ፍቅሩ

ማስታወቂያና ደንበኞች አገልግሎት
ስልክ፡- 011 1 56 98 73
ፋክስ፡- 011 1 57 44 40

ማከፋፈያ፡-
ስልክ፡- 011 1 57 02 70

ሌይአውት ዲዛይን
ዮሐንስ አሥራት

ፎቶግራፍ፡-
ገባቦ ገብሬ
ሀዱሽ አብርሃ
ሣሙኤል ተስፋዬ

# “ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነጻነት ቀንዲልና መሰባሰቢያ ማዕከል መሆኗ ይቀጥላል”

**አቶ የሱፍ ኢብራሒም**
**የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)**
**ምክትል ሊቀመንበር**

የትናየት ፈሩ

**የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ሕወሓት በመከላከያ ሰራዊት ላይ የፈጸመውን የክህደት ጥቃትን ተከትሎ ለስምንት ወራት በተካሄደው የህግ ማስከበር ዘመቻ ተጠቃሽ ተሳትፎ ካደረጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል አንዱ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት የተናጠል ተኩስ አቁም አውጀ መከላከያ ከትግራይ ከወጣ በኋላም ከሐምሌ 5 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ሕወሓት በአማራና አፋር ክልሎች የፈጸመውን መጠነ ሰፊ ወረራ ለመመከት እየተደረገ ባለው የህልውና ዘመቻ ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ይገኛል። ዘመን መጽሔት በተለያዩ ግንባሮች በመገኘት ህዝብ የማንቃትና የማደራጀት ሥራ እየሰሩ ካሉት የንቅናቄው አመራሮች መካከል አንዱ ከሆኑት አቶ የሱፍ ኢብራሒም ጋር በህልውና ዘመቻው እያደረጉ ያሉትን አጠቃላይ እንቅስቃሴና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ቆይታ አድርጋለች፤እንደሚከተለው ቀርቧል።**



**ዘመን ፡- በቅርቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ሆነው ተሹመዋል። ከመንግሥት ጋር ስልጣን ተጋርቶ መስራትን እንዴት አገኙት?**

**አቶ የሱፍ ፡-** የኢትዮጵያ ፖለቲካና ማህበራዊ ሁኔታ እጅግ በጣም ፈታኝ የሆነ ፤ በምስቅልቅል የተሞላ እና ቀደም ሲልም ብዙ ችግሮች የነበሩበት ነው። ከውጭም ከውስጥም ያሉ ኢትዮጵያ ጠል ኃይሎች በቅንጅትና በሴራ በህዝብና በአገር ላይ ከፍተኛ በደል ፈጽመዋል። እኛ እንደ አብን የአገራችን ችግር በአንድ አካል ብቻ እልባት የሚያገኝ አይደለም የሚል ጥቅል አቋም አለን። በጎ አገራዊ ኃይሎች በተናጠል በጥቃቅን ልዩነቶች የታጠረ ፖለቲካ ከመምራት ይልቅ ያለውን አገራዊ ችግርና አደጋ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተሻለ ትብብር ማድረግ አለባቸው። ከመንግሥት ጋር መሰረታዊ የሚባሉ በርካታ ልዩነቶች እንደነበሩን ይታወቃል። ነገር ግን ኢትዮጵያን በተመለከተ የማያወላዳ አቋም አለን። እኛ ጉዳያችን የጥሬ ስልጣን ግብግብ አይደለም። ህዝባችንና አገራችን ከመዋቅራዊና ስርዓታዊ ችግር መላቀቅ አለባቸው የሚል አቋም ነው የምናራምደው። ከመንግሥት ጋር አብሮ መስራት በሚያስፈልግበት ሰዓት አብረን እንሰራለን። በምንለያይባቸው ጉዳዮች እንለያያለን ፤ በሰለጠነ እና በሰላማዊ መንገድ ሀሳቦቻችንን ለህዝብ አቅርበን እንወዳደራለን። የፖለቲካ ምህዳሩ ለረጅም ጊዜ ችግር የነበረበት ከመሆኑ አንጻር በአንድ ወቅትና በአንድ ጀምበር ሊፈታ እንደማይችል ስለምንገነዘብ በጊዜ ሂደት የራሳችንን በጎ አስተዋጽኦ እያደረግን መቀጠል ነው የምንፈልገው።

በስድስተኛው አገራዊ ምርጫ አብን ግንባር ቀደም ተፎካካሪ ፓርቲ ሆኖ በክልልና በፌዴራል መንግሥቱ ውክልናዎችን አግኝቷል። ከመንግሥት ጋር አብሮ መስራት የሚለው ሀሳብ በእኛ ጥቅል አጀንዳ ውስጥ ስለነበረ ከምርጫ በኋላ መንግሥት በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ከተወዳደሩና የህዝብ ድጋፍ ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አብሮ ለመስራት ያቀረበውን ጥያቄ ተቀብለናል። መደበኛ በሆነ መንገድ ባይሆንም ቀደም ሲልም ከመንግሥት ጋር ብዙ ነገሮችን በትብብር ስንሰራ ነበር። እኛ በትብብር ችግሮች እልባት ማግኘት አለባቸው ብለን ነው



የምናምነው። ማን ሰራቸው የት ቦታ ሆነ የሚለው ለእኛ መሰረታዊ ነገር አይደለም። እኛ ቦታዎችን የምንፈልገውና አማራጮችን የምናቀርበው ቦታና ስልጣኑን ማግኘት ለአገርና ለህዝብ እስከ ጠቀመ ድረስ ብቻ ነው። ስለዚህ ከራሳችንም እሳቤ ጋር አብሮ ስለሚሄድ መንግሥት ያቀረበውን ጥሪ በጥቅሉ ተቀብለነዋል። እስካሁን ባለው ሁኔታም የተሰጠንን ቦታ ተቀብለን እየሰራን ነው ያለነው።

**ዘመን ፡- የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች የገዢውን ፓርቲ ፕሮግራሞች የሚያስፈጽም ካቢኔ ውስጥ መካተታቸው ትርጉም የለውም ሲሉ የሚተቹ ወገኖች አሉ። የአብን ምላሽ ምንድ ነው?**

**አቶ የሱፍ ፡-** ችግር የሚፈጥሩት የኢትዮጵያን አጠቃላይ ማህበረ ፖለቲካ ግልብና ጥራዝ ነጠቅ በሆነ መንገድ የሚያዩ ሰዎች ናቸው ። ይሄ እንደ አገር የነበረብንን ችግር ፣ የደረሰብንን ጉዳት እና ባሳለፍናቸው ሥርዓቶች በተለይም ባለፉት ሰላሳ ዓመታት በትህነግ መር ሥርዓት የደረሰብንን አጠቃላይ ችግር የመርሳት አባዜ ነው። በአንድ ጊዜ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ ማግኘት እንችላለን የሚል እጅግ በጣም ግብዝ የሆነ አስተሳሰብ አለ። ነባራዊ ሁኔታዎችን ተንትኖ የኃይል አሰላለፉን ተመልክቶ ግራና ቀኝ ያለውን ፍላጎትና አቅም ከግንዛቤ አስገብቶ በአንጻራዊነት የተሻለውን እና በጊዜ ሂደት የጋራ አጀንዳን እውን ለማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ በደንብ የማይፈትሹ አካላት ናቸው እንደዚህ የሚሉት።

እኛ ከመንግሥት ጋር የምንተባበረውና ስንተባበርም የቆየነው በሌላ ጎን ያለውን ኃይል ፍላጎትና አቅም ስለምናውቅ ነው። አገር ለማፍረስ ህዝብን ለመበተን ዘወትር ዝግጁ የሆኑ ለዚህም ጠብ መንጃውንም በጀቱንም ያዘጋጁ ኃይሎች በአንድ በኩል አሉ። በሌላ በኩል ማዕከላዊ መንግሥቱ እንዲጸና እና ኢትዮጵያ እንድትቀጥል የሚፈልግ በውስጡ ሰርጎ ገቦችና ኃላፊነታቸውን የማይወጡ ሰዎች ያሉበት ኃይል አለ። ከዚህ ኃይል ጋር አብረን መስራት አለብን የሚል አቋም አለን። ይህ ኃይል የአገር ሥርዓት ስለሆነ እየተሻሻለና እኛም በውስጡ ቦታ እየያዝን ተባብረን እየሰራን እንቀጥላለን። የምርጫ ስርዓቱ ከፍተኛ ድምጽ ያገኘውን ብቻ የሚያሳልፍ በመሆኑ ነው እንጂ የተመጣጣኝ ውክልና የሚለው ስርዓት ቢሆን ኖሮ እኛ በርካታ ድምጽ ሊኖረን ይገባ ነበር። ዞሮ ዞሮ የበርካታ ማህበረሰብና የህዝብ ፍላጎት ከእኛ ጀርባ አለ። ስለዚህ ለዚህ ህዝብ ፍላጎት ዘላቂ ጥቅም እና ለኢትዮጵያዊነት ስኬት ለአገር ቀጣይነትና አንድነት ጠቃሚ ነው ያልነውን ሁሉ ነው የምንሰራው።

የተናጠል አንድ የፖለቲካ እሳቤ ሊኖር አይችልም። እኛ መንግሥትን ለመደገፍ አይደለም የምንሰራው። መንግሥት መተቸትና መሻሻል አለበት። ህዝብ ለሚፈልግበትና አደራ ለሰጠው ነገር ሁሉ ፈጥኖ ደራሽ መልስ ሰጭ ደህንነቱን የሚያስከብር ተቋም እንዲሆን እንፈልጋለን። ይሄ ግን በአንድ ጀንበር የሚሆን ነገር አይደለም። ድግሞም ከሌላ በይሁንታና በችሮታ ብቻ የሚሰራና በአንድ ወገን የሚከናወን ነው ብለን አናምንም። እኛ ራሳችን ባለድርሻ እንደመሆናችን መጠን በተለይም መንግሥት ያለንን የህዝብ ድጋፍ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀደም ብለን ስናቀርብ የነበረውን የትብብር ጥያቄ ተቀብሎት አብሮ የመስራት ፍላጎት ሲያሳይ አብረን የማንሰራበት ምንም ምክንያት የለም።

መንግሥት መር የሽግግር ጊዜ እንጂ የሽግግር መንግሥት አያስፈልግም ስንል የሽግግር መንግሥት ቢቋቋም እዚያ ውስጥ አብን የአማራን ህዝብ ወክሎ ሊመጣ እንደሚችል እናውቃለን። ግን ያ ተጨባጭና አዋጭ የሆነ አካሄድ አይደለም። ልክ እንደ 1983 ዓ.ም ህዝባችንን እና አገራችንን ለጽንፈኛ ኃይሎች አሳልፎ የሚሰጥና በጎ አገራዊ ኃይሉን ከጀርባ የሚወጉ ሴረኞችና በአሻጥር የተሞሉ ኃይሎች የሚሰባሰቡበት ማዕከል እንደሆነ ጠንቅቀን ስለምንረዳ በተቃራኒው መስመር መቆም ግድ ስለሆነ ነው።

የውጭ አገር ኃይሎች ከውስጥ ካሉት ጋር በመቀናጀት መንግሥትን ለማስወገድ ርብርብ ሲያደርጉ እኛ ከመንግሥት ባልተናነሰ ከኤምባሲዎችና ከዲፕሎማቲክ ተቋሞች ጋር እየተገናኘን መንግሥትን የምንከላከለው ችግር ስለሌለበትና ብቃት ስላለው ሳይሆን በዛ ደረጃ ኃላፊነት መውሰድ አስፈላጊ ስለሆነ ነው። አገሪቱ በበጎ ኃይሎች ትብብር ስር መውደቅ አለባት የሚል እምነት ስላለን ነው። በስልጣን ላይ ያለ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት ብቻውን ይሄንን አገር ማሻገር ይችላል ብለን አይደለም። በጎ ኃይሉ በተፎካካሪነት የሚሰራቸው ሥራዎች አሉ ፤ ጽኑ የሆኑ አገራዊ አጀንዳዎች ሲመጡ ደግሞ አብረን መስራት አለብን ብለን እናምናለን።

በመንግሥት ውስጥ ሆነን ስንሰራ አንደኛ በሕግ ነው ሁሉም ነገር የሚሰራው። ስልጣን ሲሰጠን በአዋጅ ነው። አዋጁ ደግሞ ደምብ አለው። ራሳችንም አብረን እየተሳተፍን የምናወጣው ነው። መመሪያውንም እዚያው ውስጥ የምናደርገው ነው። ልምድ ይገኝበታል። አብሮ መስራት መተማመንን ያተርፋል። የምናስባቸውን ሃሳቦች በቀጥታ መንግሥታዊ አጀንዳ የማድረግ ዕድልና መብት ይፈጥርልናል። ተቃውሞ ካለን እናስመዘግባለን፤ በአገራችን እና በስርዓታችን ጉዳይ ላይ ጽንፈኛ ሆነን አፍራሽ እርምጃ ሳንወስድ የራሳችንን በጎ ድርሻ እንወጣለን። ለመደበኛ ፖለቲካችንም መንግሥትን ይሄን አድርገሃል አላደረግህም ብለን ለመተቸት ይበልጥ ዕድል እናገኛለን። አኩራፊነትና ጠርዝ ወጥቶ ለአገርና ለህዝብ የማይጠቅም እንቅስቃሴ ማድረግ ተችሏል። በዚህም የሽብር ቡድኑን እንቅስቃሴ በአካል ብቃትም ይሁን በአመለካከት ስራ መክቶ ማሸነፍ የሚችለው ኃይል ወደ ግንበር እየተመመ ነው ያለው። አሁን ከቀን ወደ ቀን የህወሓት ጀንበር እየጠለቀች የሚሸነፍበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው። የኃይል ሚዛኑም ወደ ኢትዮጵያዊያን እያመዘነ ነው። በመካከል ግን የተሻሉ የቀውስ ጊዜ አመራሮችን በመስጠት ጉዳቱን መቀነስና አገራችን ላይ የተፈጸሙ ወከባዎችን ማስቀረት የምንችልባቸውን ዕድሎች መፍጠር እንችል ነበር የሚል እምነት አለኝ።

**ዘመን፡- አሸባሪው ህወሓት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ሲኦል እንገባለን እንዲሁም ከአማራ ጋር ሒሳብ እናወራርዳለን ሲል በአደባባይ ተናግሯል። የድርጅቱ አማራ እና ኢትዮጵያ ጠልነት ከየት መጣ ?**



# የአገራችንን ህልውና እናስጠብቃለን ። ለዚህም ሃያ አራት ሰዓታት ያለእረፍት እየሰራን ነው

**አቶ የሱፍ፡-** ሕወሓት ከውሸት የተወለደ ኢትዮጵያዊ እሴት የሌለው ውሸታም ድርጅት ነው። ሲሰራ የቆየው በህዝቦች መካከል በጎ ድንበር ተሻጋሪ ግንኙነቶች እንዳይኖሩ ለማድረግና የነበሩትንም ለማፍረስ ነበር ። ሕወሓት የአማራን ህዝብ ጠላቱ ያደረገው የቅኝ ገዢ ኃይሎች ውላጅና ውርስ የሆነ ሀሳብን በመግዛት ነው። አንደኛ ተፈጥሯዊ በሆነው በመልክዓ ምድር አቀማመጡ የአማራው ቀጠና ወደ ማዕከል በመምጣት ስርዓቱን ለማፍረስ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ በቀላሉ አልፎት መሄድ የማይችለው ጎረቤት ክልል ስለሆነበት ነው። የአማራ ህዝብ ደግሞ በታሪኩ አገሩን ለማቆየት ከጠላት ፣ ከወረራና ከቅኝ ግዛት ለመከላከል ብዙ ዋጋ ከፍሏል። በየትኛውም የኢትዮጵያ ማዕዘን አጋሩ ወገኑ ሲጠቃ ይዘምታል ፤ መስዋዕትነት ይከፍላል። ይሄ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለ የአማራ ህዝብ ጥቅል ማህበራዊ መገለጫው የሆነ ተግባሩ ነው ማለት ይቻላል። ብዙ ጉዳቶችን አስተናግዶ እዚህ ደርሷል። ስለዚህ አንደኛ ምክንያቱ እንደፈለግኩ ኢትዮጵያን አፍርሼ ለሌላ የውጭ አካልና የአገር ውስጥ የሽብር ቡድኖች ሲሳይ እንዳላደርጋት እንቅፋት ይሆንብኛል የሚለው የአማራን ህዝብ ነው።

‹‹ኢትዮጵያን ለማፍረስ አማራውንና ክርስትና እምነትን መምታት ነው›› የሚል ግልጽ አቋም ነበራቸው። ከሕወሓት ጋር በተመሳሳይ ዘመን የተመሠረቱ ድርጅቶችም ማኒፌስቷቸው እንዲሁ ነው። ኢትዮጵያን ከአንድ ብሔር ጋር ብቻ በማስተሳሰር ኢትዮጵያን ለመገንባትና ለመጠበቅ በአርበኝነት በታሪክ የተመዘገቡ የሌሎችን ዜጎች ሚና ሁሉ በመካድ፣ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ በመንዛት፣ ጽንፈኞችን በመፈልፈል ላይ የተመሰረተ ስምሪት ያለው ነው። ስለዚህ የአማራን ሕዝብ መምታት የሚፈልጉት የኢትዮጵያዊነት ወሳኝ አገናኝ ድልድይ ነው ብለው ለሚያምኑ ኃይሎች ስለሚሠሩ ነው። በሌላው ማኅበረሰብ ዘንድም ልቦለዳዊ ቅራኔ በመፍጠር ማኅበራዊ ጭቆና በሕዝብ ደረጃ እንደነበረና እንዳለ አድርገው የውሸት ትርክት ያራምዱ ነበር።

ዋነኛ መዳረሻው ግን ኢትዮጵያን ማፍረስ ወይም ደግሞ ለዚህ ቡድን ብቻ የምታገለግል ፣ በጭቆናና በአምባገነንነት ቀንበር ውስጥ የምትገኝ እና በሯን ለውጭ ኃይሎች ከፍታ የምትተው ኢትዮጵያን በማበጀት የቀጣሪዎቹ ፍላጎት ለማስፈጸም መንቀሳቀስ ነው። አማራን የሚጠላው ኢትዮጵያን ለማፍረስና ሌሎች ፍላጎቶቿንም እንዳልፈጽም ዋነኛ ተገዳዳሪ ኃይል ይሆንብኛል ብሎ ስለሚያስብ ነው። ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም መከላከያ ላይ ተኩስ በተከፈተበት ዕለት ዳንሻ ላይ አምስተኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ ላይ ጥቃት በተሰነዘረ ጊዜ የአማራ ሕዝብ ከአርማጭሆና ከአካባቢው ማንም ነጋሪ ሳያስፈልገው መከላከያን ለመታደግ ዘምቷል። ሕወሓት ይህንን ቀድሞም ስለሚገነዘብ ነው አማራን የሚጠላው።

**ዘመን፡- አብን በህልውና ዘመቻው እያደረገ ያለው ተሳትፎ ምን ይመስላል?**

**አቶ የሱፍ ፡-** ሕወሓት የኢትዮጵያን መከላከያ በማጥቃት ጦርነት ሲከፍት አብን ግልጽ አቋሙን በመግለጫ አሳውቋል። ይሄ አገር ጠልና ወንጀለኛ ድርጅት ነው። አሁን የመጨረሻውን የአገር ክህደትና የባንዳነት ስሜቱን በተግባር አረጋግጧል። መከላከያን አጥቅቶ ሀገርን ለጠላት ተጋላጭ አድርጓል። ስለዚህ የመጨረሻውን ቀይ መስመር ስለተላለፈ ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል። በሕግ ጥላ ስር መዋል አለበት የሚል አቋም ነው የወሰደው። መንግሥት መከላከያ ሠራዊቱ በሚወስደው ስምሪት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብሮ እንዲቆም ሲጠይቅም አብንም በማንኛውም መንገድ በዘመቻው እንደሚሳተፍ አረጋግጦ ከመከላከያው ጎን ተሰልፏል።

አሁንም አባሎቻችን ከመከላከያ ሠራዊት ፣ ከፋኖ ፣ ከሚሊሻውና ከልዩ ኃይሉ ጋር ሆነው ሥራ እየሠሩ ነው። ወጣቶች መከላከያን እንዲቀላቀሉ የማንቃትና የማደራጀት እንዲሁም ማኅበረሰቡ ደጀን እንዲሆንና ሰርጎ ገቦችን በመቆጣጠር ደኅንነቱን እንዲያስጠብቅ እና ማናቸውንም የመንግሥት አቅጣጫ እየተቀበለ ትብብር እንዲያደርግ እያስተባበርን እንገኛለን።

**ዘመን፡- በወሎ ግንባር ተገኝተው ህዝብን የማደራጀት ሥራ ሲሰሩ ከነበሩት የአብን አመራሮች መካከል እርስዎ አንዱ ነበሩ። በወሎ የተደረገውን ተጋድሎና አሁናዊ ሁኔታ እንዴት ይገልጹታል?**

**አቶ የሱፍ ፡-**በወሎ የነበረው ሁኔታ ከባድ ነበር። ከራያ አላማጣ ጀምሮ ቆቦ ፣ ሮቢት፣ ወልዲያ፣ መርሳና ሌሎችም በዚያ አካባቢ በነበሩ ሕወሓት በወረራቸው አካባቢዎች የነበረው ሕዝብ በጅምላ ተፈናቅሎ፣ ተጠልሎ የነበረው ደሴ ከተማ ነበር። ስለዚህ ስደተኞችንም ያስተናግድ ነበር። የሕዝብ ፍሰቱ አጠቃላይ እንቅስቃሴው እጅግ ከባድ ነበር። ነዋሪው ማኅበረሰብ ላይም የነበረው ጫና የትየለሌ ነበር። ሕወሓት ደግሞ ሰርጎ ገቦችን በማሰማራት ይታወቃል። በተጨማሪ ደግሞ በኢትዮጵያዊነት በአብሮነት መንፈስ ለበርካታ ዐሠርት ዓመታት ደሴና ከምቦልቻ ይኖሩ የነበሩ የትግራይ ተወላጆችንም በመመልመል በሳይበርና

በተለያዩ መንገዶች ስምሪት ሰጥቷል። የፕሮፓጋንዳ ኃይሎችን በመጠቀም አካባቢውን ሊቆጣጠር እንደደረሰና እንደተቆጣጠረም ያስነግር ነበር።

እኛ መሬት ላይ ያለውን እውነት በማጋለጥ በየጦር ግንባሩ ድረስ በመሄድ መከላከያ ሠራዊቱንና አጠቃላይ ማኅበረሰቡ የሚያደርጋቸውን ትብብሮች በማሳለጥ ስንቅና ትጥቅ እንዲቀርብ ጥረት አድርገናል። የሕወሓት ኃይል የሚታይባቸውን ቀጠናዎች ሕዝቡ እንዲጠቁምና እንዲያጋልጥ በማድረግ ለወገን መረጃዎችን በማቀበል መንግሥትም እርምጃ እንዲወስድ ከመከላከያ አመራሮችም ጋር ጭምር ተናበን በመስራ ጠላት ከፍተኛ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት እንዲደርስበት አድርገናል።



መከላከያ ጠላትን አሸንፎት ሐይቅና ኩታበር ላይ የወያኔ ኃይል እየሸሸ ነበር። በእነዚህ ቦታዎች ላይ የደረሰበት ጉዳት ደሴና ከምቦልቻን አልፎ ለመራመድ እንዳይችል አቅም አሳጥቶታል የሚል እምነት አለን። እዚያ አካባቢ የነበረው የመከላከያ ኃይል ትግል፣ የማኅበረሰቡም ደጀንነት በምሳሌ ሊጠቀስ የሚችል ነው። አንድ ቁልፍ ችግር ግን ነበር፤ ከሠላሳ እስከ አርባ ሺህ የሚገመቱ የትግራይ ተወላጆች በከተማ ውስጥ ይገኙ ነበር። የደሴና ኮምቦልቻ ሕዝብ አብረውን ኖረዋል ዝምድና ፈጥረናል በአንድ ዕድር በአንድ እምነት የምንኖር ነን ብሎ አምኗቸው የኖሩ ናቸው። እነዚህ ናቸው እንግዲህ እንደ አለመታደል ሆኖ እምነታቸውን በመብላት ከመሃል የደበቁትን ጠመንጃ በማውጣት መሐል ከተማ ላይ ሽብር በመንዛት ከተማዎቹን ከመሃል ያፈረሷቸው።

ደሴና ኮምቦልቻ በሚፈርሱበት ጊዜ ተዋጊው የሕወሓት ኃይል ከተማዎቹ ጫፍ እንኳን አልደረሰም። ሰርጎ ገቦቹ የልዩ ኃይሉ እና የመከላከያ ዩኒፎርምን አስገብተውላቸው ያንን እየለበሱ እያምታቱ ሠርተዋል። ይሄንን አጠቃላይ የክልሉና የከተማው የደኅንነት መዋቅር መቆጣጠር ነበረበት። ጊዜ አጠረን እንጂ ከመሃል የሚኖሩ ችግሮችን ካልተቆጣጠርን ችግር ይገጥመናል የሚል ማሳሰቢያም ሰጥተን ነበር። በጊዜው ባደረግናቸው ግምገማዎች ለምሳሌ በሐይቅ ከመከላከያ ጀርባ ገብተው በስንቅ አቀባይነትና በደጋፊነት አብረው ከሕዝቡ ጋር ተሰማርተው «በቦሩና በኩታበር ያለው መከላከያ እየፈረሰ ነው ፤ እናንተ ለምንድነው የምትለፉት!» እያሉ ሽብር ሲነዙ የያዝናቸው የትግራይ ተወላጆች ነበሩ። ያን ጊዜ ግን ትሕነግ ተመቶ እየሸሸ የነበረበት ወቅት እንጂ አንዳችም የመከላከያ ክፍል ቦታ ለቆ ያፈገፈገበትና የከዳበት አግባብ አልነበረም። እንዲህ ባሉ መንገዶች በጣም በሚያስቆጭ ሁኔታ ያገኘነውን ድል አጥተነዋል።

አንዱ ጦር ወደ ሌላው የሚተኩስ በማስመሰል ከፊሎቹ የልዩ ኃይል ልብስ ከፊሎቹ የመከላከያ ልብስ ለብሰው ሳይመታቱ ግን እንደሚተኳኮሱ ዓይነት ድራማ ሠርተው ለከተማ ሕዝብ በማሳየት ለማሸበር ተንቀሳቅሰዋል። ይህን እንዳለ የሚወስዱ ጥራዝ ነጠቅ ሰዎች በጸጥታ ኃይሉ መካከል ቅራኔ ያለ አስመስለው ፕሮፓጋንዳ ለመንዛት ሞክረው ነበር። ብዙ ሴራዎችን ነው ሲሠሩ የነበሩት። ገዳይ እስኳድ አስገብተው ስምሪት ላይ የነበርነውን አስተባባሪዎች ለማስገደል ተደጋጋሚ ሙከራ አድርገው ፋኖና የመከላከያ ሠራዊቱ በወሰዱት እርምጃ በቁጥጥር ስር የዋሉ አሉ። እኔ አርፍበት የነበረውን ሆቴል የክፍል ቁጥሩን ሁሉ በመለየት በከባድ መሣሪያ አፍርሰውታል። በአጋጣሚ እኛም በደኅንነት ጥንቃቄ እናደርግ ስለነበር እዚያ አልነበርንም። ሕዝቡ ደጀን እስከሆነ ድረስ ጠላት መደምሰስ እንደሚችል ስለምንገነዘብ የወገን ኃይል ማስተባበር ላይ አተኩረን ሠርተናል። እንቅስቃሴያችን ተጽእኖ አሳድሮባቸው ስለነበር በዘወትር ቃል አቀባያቸው በጌታቸው ረዳ ስማችንን እየጠቀሱ ዛቻና የማስፈራራት ሥራዎችንም ሠርተዋል።

ጠላት ሰተት ብዬ ወደ አዲስ አበባ እገባለሁ ብሎ ያቀደበትን አቅምና ዕቅድ በደሴና ኮምቦልቻ በተደረገ መከላከል በደረሰበት ጉዳት አጥቷል። አሁን በሁሉም ቀጠናዎች በከበባ ውስጥ ሆኖ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት እንቅስቃሴ እያደረገ ነው ያለው። የታፈነና የመሞቻ ጊዜውን ብቻ እየጠበቀ ያለ ወራሪ ኃይል ነው። አሁን ኮምቦልቻን አልፎ በደሴም መስመር በሸዋ ፣ ወደ አፋር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሁሉ ፍላጎቱ በዚህ ፍጥነት እዚህ እደርሳለሁ ብሎ ለቀጣሪዎቹ የገባውን ቃልኪዳን ማስጠበቅ የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ አጠቃላይ ግብዓተ መሬቱን እየጠበቀ ነው።

**ዘመን፡- በተለያዩ የአማራ ክልል አካባቢዎች በመንቀሳቀስ ህዝብ ለማደራጀት እያደረጋችሁ ያላችሁት ጥረት ምን ያህል ውጤታማ ነው?**

**አቶ የሱፍ ፡-** በእኛ እምነት ትግሉ መጠናቀቅ ያለበት በማሸነፍ ብቻ ነው። አማራ ብቻ ሳይሆን ሌለውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ማሸነፍ አለበት። ማእከላዊ ሥርዓቱ መጽናት አለበት። በውስጥም በውጭም የእኩያን ኃይሎች የተከፈተብንን ዘመቻ የመከላከል ታሪካዊ ኃላፊነት አለብን። የእኛ ሕይወት መከላከያ፣ ፋኖ ወይም ልዩ ኃይል ውስጥ ካለው ሕይወት የበለጠ ዋጋ እንዳለው ማሰብ አይገባም። መስዋዕትነት መክፈል ካለብን ማንኛውንም መስዋዕትነት መክፈል አለብን በሚል ቃል ኪዳን ገብተን ነው ስምሪት የወሰድነው። ደሴ ከተያዘና በአስቸጋሪ ሁኔታ ከወጣን በኋላ መኪናችንን ለመምታት

የመጨረሻው ቀጠና ድረስ መድፍ እየተተኮሰብን ነበር።

የተሻለ ነገር ለማድረግ እኛ ወዲያው ኮምቦልቻ ከተማ ገባንና ደሴ ላይ የነበረውን ስሕተት ኮምቦልቻ ላይ በፍጥነት ማረም እንችላለን ወይ ብለን መዋቅራችንን ለማወያየት ብንሞክርም ወረራው ፈጣን ስለነበርና ከደሴም የወጣው ማኅበረሰብ መረጋጋት ስላልቻለና ለእንቅስቃሴም አመቺ ሁኔታ ስላልተፈጠረ ኮምቦልቻ ላይ መሥራት አልቻልንም። ወዲያውኑ ግን ቀጣዩ የጠላት እንቅስቃሴ ወዴት ሊሆን ይችላል የሚለውን የራሳችንን ትንተናዎች ወስደን ሥራችንን ቀጥልን።

አንድ ነገር ስላጣን እንደተሸነፍን ሳናስብ በቁጭት የጠላትን እንቅስቃሴ ማኮላሸት በሚያስችል ደረጃ ለመደራጀት የሄድነው ወደ ሸዋ ነው። እንደጠበቅነውም መረጃው ዝግጅቱም ያልነበረባቸው አካባቢዎች ነበሩ። ስለዚህ ወጣት አደረጃጀቶችን፣ ፋኖዎችን አስቀድመንም በተለያየ አግባብ እንገናኝ ስለነበር መኮይ ላይ ሄድን በዚያ አደርን። መተላለፊያ በዚህ ስለሚኖር ኬላ ይጠበቅ ፋኖ እና ሚሊሻ ዝግጁ ሆነው ቀጠናዎቹን ተቆጣጥረው እንዲጠብቁ አሳስበን ሄድን። ከዚያም መንዝ ግሼ ራቤል ሔድን መዋቅራችንን ሰብስበን ተገቢውን ሥራ ስንሠራ ቆየን። መሐል ሜዳ እንቅስቃሴዎች አሁኑኑ መደረግ እንዳለበትና ወደ መኮይ ፣ ማጀቴ አጣዬ አካባቢ መንቀሳቀስ እንደሚያስፈልግ ለማስገንዘብ ጥረናል። በዚያም ሰርጎ ገቦች እንዳይኖሩ፣ ደሴና ኮምቦልቻ የተፈጸመው ስህተት እንዳይደገም ከመንግሥትም ከራሳችንም መዋቅር ጋር ተመካክረናል። ከአጠቃላይ የሸዋ ፋኖ መሪዎች ጋር ተወያይተናል። እኛ እዚያው ሆነን ውይይት እያደረግን ባለንበት ሰዓት የማኅበረሰቡ የጸጥታ እንቅስቃሴ ሲለወጥ በዓይናችን እናየው ነበር። በጣም ደስ የሚል ስምሪት ነበር።

በቀጣይ ቀናት ወደ ጃማ ወረኢሉ ከዚያም ቦረና መካነሰላም ገባን። እዚያም ከአካባቢው ሁሉ የተሰባሰቡ የወሎ ፋኖዎች ነበሩ። የልዩ ኃይል ባላትና የመከላከያ አባላትም ነበሩ። በዚያም ተደራጅተው ጠላትን መከላከል እንዲችሉ በማድረግ የሚጎድል ካለ ማህበረሰቡና ደጋፊዎቻችን ትብብር እንዲያደርጉ የማሳለጥ ሥራዎችን ሠራን። ከዚያም መርጡለ ማርያምና ሞጣ ሔደን ተመሳሳይ ሥራዎችን ለመሥራት ጥረናል። በባህርዳርም ከክልሉ መንግሥት አመራሮች ጋር ተገናኝተን በቀጣይ መሠራት ስላለባቸው ነገሮች በስፋት ተነጋግረናል። ከዚያም ወደ ጎንደር ሄደን በደብረታቦር በኩል በጋሸና በታች በጋይንት ወዳሉት ግንባሮች በማቅናት ጠላትን እንዴት ማጥቃት እንዳለብን ተወያይተናል። በደቡብ ጎንደር ጋሳይ ፣ ክምር ድንጋይ፣ ደብረታቦርም የተሳኩ ሕዝባዊ ውይይቶችን አድርገናል። መዋጋት የሚችለው ኃይል ጠመንጃ ስላጣ ነው ፤ ስለዚህ አቅመ ደካሞች የዋስትና ፎርም እየተሞላ ጠመንጃችሁን ለሚዋጋው ኃይል ለፋኖ ስጡ የሚል ውይይት

## ሕወሓት የውጭ ኃይሎች ቅጥረኛ ሲሆን፤ ሸኔ ደግሞ የሕወሓት ፈረስ ነው

አድርገን እኛ እንኳን ባለንበት መድረክ በአንድ ቀን 240 ጠመንጃ ለወጣቶች የተሰጠበት ትዕይንት ነበር። እነዚያ ልጆች ግንባር ገብተዋል።

ሌላው ከክልሉ ጋር በነበረን ግብረ ኃይል ጎንደር ላይ ስብሰባ ነበረን። ወደ ልዩ ኃይልና መከላከያ ወጣቶች እንዲገቡ ቅስቀሳ ነበር። ወደ ማሠልጠኛ ከመግባታቸው በፊት የኢንዶክትሪኔሽን ስልጠናዎችን በትብብር ሰጥተናል። በማኅበረሰቡ ውስጥ የወጣቱ እንቅስቃሴ እጅግ የሚገርም ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለው እንቅስቃሴ እጅግ ሰፊ ነው። የወሎና የጎንደር ፋኖዎች የሚያስፈልጋቸውን ግብዓት ከመንግሥት ጋር በመነጋገርና ከየመዋቅሩም ጋር በማገናኘት እና ባለሀብቱ እንቅስቃሴ የሚያደርግበትንም መንገድ ለመቀየስ ጥረናል። በተወሰዱ ስምሪቶችም አመርቂ ውጤት እየተገኘ ነው። ይሄ አሁንም ይቀጥላል። ጠላትን ደምስሰን የአገራችንን ህልውና እናስጠብቃለን የሚል ጽኑ አቋም አለን። ለዚህም ሃያ አራት ሰዓታት ያለእረፍት እየሰራን ነው።

በዚህ ሳምንት የአብን መዋቅር ከጎንደር ሁሉንም ጠርተን ስምሪቶችን ሰጥተናል። በየግንባሩ መደረግ ስለሚገባው ነገር ግንዛቤ ሰጥተናል። ከራያ ቆቦ ጀምሮ በርካታ የአብን አመራሮች በትግሉ እየተዋደቁ ነው። እስከ አሁን ድረስ በተዋጊነትም በአመራርነትም የሚሳተፉ ለሕዝባቸው ቀናዒ ሆነው ታሪክ እየሠሩ ያሉ የአብን አባላት አሉ። እስከ መጨረሻው ድረስ የሚቀጥል ነው። እኛ የምንችለውን ፣ የምንፈልገውንና ትክክለኛ የሆነውን ነገር እያደረግን ነው። ተጠናክሮ ይቀጥላል። አሁን እየሠራን ባለነው ሥራ በተጨባጭና በፍጥነት እየመጣ ባለው ውጤት ኩራት ይሰማናል። የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ ለተሠራው ሥራ ምስክር ይሆናል።

**ዘመን ፡- አሸባሪው ሕወሓት በአማራ እና አፋር ክልሎች የፈጸመው ወረራ መጨረሻው ምን ሊሆን ይችላል?**

**አቶ የሱፍ ፡-** ይሄ አሸባሪ ድርጅት ተመቷል። የመጀመሪያው ነገር የሐሳብ ቅቡልነት የለውም፤ የነተበ ሐሳብ ይዞ የሚንቀሳቀስ ነው። ሰዎችን በሐሳብ አሸንፎ አሳምኖ የሚገዛበት በር ከተዘጋ ቆይቷል። አሁን በጉልበት ሐሳቤን አስፈጽማለሁ ብሎ መንቀሳቀሱ ነው። ብዙ ጥፋቶች አድርሷል። አሁንም ያለው ቀላል አይደለም ሊናቅ አይገባም። የወንጀል የሽብር ግብረአበሮች አሉት። የእነሱም ሚና መናቅ የለበትም። አሁን ያለው የኃይል አሰላለፍ ግን ሚዛን ላይ ከተቀመጠ ከመቼውም ጊዜ በላይ ትሕነግ ተሸናፊ የመሆኑ ነገር እውን እየሆነ መጥቷል። ሕወሓት በአፋር ግንባር በግልጽ ተሸንፏል። በጀርባ በኩል ከወልዲያ እስከ አላማጣ ድረስ ያለውን የራያ ፋኖና ማኅበረሰቡ ዘግቶበታል። የዘረፈውን እንኳን ማስተላለፍ የማይችልበት ደረጃ ላይ ነው። በደቡብ ወሎ በኩል በወረኢሉ በተላላ በኩል ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች በሽንፈት ተገድበዋል። በከሚሴ በኩል ወደ ሸዋ ሮቢት የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከሌሎችም በባሰ ሁኔታ ተሸንፎ እንደውም በወገን ኃይል የማጥቃትና የጸረማጥቃት ሰፊ እንቅስቃሴ ምክንያት ባልተቋረጠ ሽሽት ውስጥ እንደወደቀ መረጃ አለኝ።

አሁን የወገን ኃይል እየተጠናከረ እየበዛ እያለ





# አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የአባቶቹንና የቅድመ አያቶቹን ገድል ለመፈፀም በማያወላዳ ሁኔታ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሷል

ሕወሓት በሕዝባዊ ማእበል ይዞት የመጣው ኃይል በየቦታው ሰረጎ እየተበተነ ሙት ፤ ቁስለኛና ተማራኪ እየሆነ ነው። ስለዚህ በእኔ ግምገማ ረጅም ጊዜ መቆየት የሚችል አይመስለኝም። መቆየትም የለበትም ብለን በብዙ ምክንያት እናምናለን። በሙሉ ከበባ ውስጥ ስለሆነ ዕድሉም የለውም። የተወሰነ መፈራገጥና ችግር መፍጠር ይፈልጋል፤ ለምሳሌ ዳውንት ላይ የዘር ጭፍጨፋ እንዳደረገ መረጃዎች ያሳያሉ። ያደረሰው ጥፋት ከድል በኋላ ሲመረመር ኢትዮጵያውያንና የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ሊያስደነግጥ ይችላል። ድሉ ግን የኢትዮጵያውያን የመሆኑ ጉዳይ ሳይታለም የተፈታ ነው።

**ዘመን ፦ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በአሸባሪነት የተፈረጁት ሕወሓትና ሸኔ ስለፈጠሩት ጥምረት አብን ምን ይላል?**

**አቶ የሱፍ ፦** የሕወሓትና የሸኔ ጥምረት ምንም አስደናቂ ነገር የለውም። ሸኔ ግልጽ የሆነ ዓላማ የለውም። ግቡ ከሕወሓት ጋር በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይ ነው። ችግር እየፈጠረ የሚገኘው በራሱ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ነው። የኢትዮጵያን ማዕከላዊ ስርዓት ማፍረስና የአማራን ሕዝብ ማጥቃት የሚል የሚጋሩት ሀሳብ አለ። ንፁሃንና ሴቶችን ኢላማ አድርጎ የፖለቲካ ትርፍ ማምጣት እችላለሁ የሚል የዘወትር ተሸናፊ ድርጅት ነው። በኦሮሞ ሕዝብ ውስጥ ቦታ የለውም። በኦሮሞ የፖለቲካ ኃይሎችም የተገፋና ቦታ የሌለው ድርጅት ነው። ሕወሓት የውጭ ኃይሎች ቅጥረኛ ሲሆን፤ ሸኔ ደግሞ የሕወሓት ፈረስ ነው። ይህ ድርጅት በ1983 ዓ.ም ከሕወሓት ጋር በተወሰነ ደረጃ ጥምረት እንፈጥራለን ብሎ በአንድ ቀን ትዕዛዝ ሠራዊቱን የትም በትኖ የፈረጠጠ ነው። ረጅም ዘመን ከአገር ውጭ የተለያዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎችን ለማድረግ ቢሞክርም አልተሳካለትም። እንደውም ከገፋው የሕወሓት ስርዓት ጋር በጀርባ በማበር መረጃዎችን በመስጠት የኦሮሞ ወጣቶችን ለእስራት፣ ለእንግልትና ለሰቆቃ መዳረጉን የሚያሳዩ ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉ።

በአጭሩ ሸኔ የሕወሓት እንቁላል ነው ማለት ይቻላል። በትርፍራፊ ገንዘብ በመናኛ ፍጆታ በጣም ለጨቋኙ ሕወሓት ቡድን ያደረ ነው። በጣም በሚያሳዝን መልኩ በታላቁ የኦሮሞ ሕዝብ ስም ተደራጅቻለሁ እያለ የኦሮሞን ሕዝብ ተነግሮ ለማያልቅ ሰቆቃ የዳረገውን ሕወሓት መራሹን አምባገነንና ዘረኛ ስርዓት እንደገና ወደ ማዕከል ለማምጣት የሚሠራ በፖለቲካ ሳይንስ ታይቶም የማይታወቅ ድርጅት ነው። በጦር ሜዳም ያን ያህል ልምድም ሆነ ገድል የለውም። ሰሞኑን በወሎና በአማራ ክልል ኦሮሚያ ልዩ ዞን አካባቢ አንዳንድ የሽብር ሥራዎችን ከሕወሓት ጋር በጥምረት ለማከናወን ሙከራ አድርጎ ነበር። ነገር ግን የኦሮሞ ማህበረሰብ ራሱ አትወክለንም ለአገራችንም ለሕዝባችንም የማትሆን ድርጅት ስለሆንክ በእኛ እግር ስር ልትሆን አትችልም በሚል ከመከላከያ ፤ ከልዩ ኃይሉና ከፋኖ ጋር በመሆን እርምጃ ወስዶበታል።

ስለዚህ ሕዝብ የተጠየፈው ጥምረት ነው ማለት ነው። አሁን በአደባባይ ያወጡት እንጂ በወለጋ እንዲሁም በተለያዩ የኦሮሚያ ክፍሎች ኦነግ ሸኔ ለሚፈጽማቸው የሽብር ተግባራት ሕወሓት የገንዘብና የመረጃ ድጋፍ ያደርጋል። የአሁኑ በቃል ከመገለጽ ውጭ የተለየ ትርጉም ያለው ነገር አይደለም። የኦሮሞ ሕዝብና የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ይህንን ኃይል ፊት ለፊት እየተጋፈጠው ነው ያለው። ማህበረሰቡ እየተደራጀ ሰርጎ ገቦችንና ወንጀለኞችን አንገታቸውን እየያዘ ወደ ፍርድ አደባባይ እያወጣቸው ነው ያለው። የኦሮሞ ድርጅት ነኝ የሚለው ሸኔ የኦሮሞ ልጆች በማዕከላዊ ስርዓት ውስጥ በእኩልነትና በፍትሕ ለመተዳደር ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው ጋር አብረው የሚሠሩበት መድረክ እየተፈጠረ ባለበት ሁኔታ ይሄን ለመዝጋትና ወደ ደም መፋሰስና ሽብርና አገር የማፍረስ እንቅስቃሴ የመግባቱ እንቆቅልሽ ከሕወሓት ግብዓተ መሬት መፈጸም ጋር አብሮ የሚፈታ ይሆናል።

**ዘመን ፦ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ ላይ ሁሉንም አይነት ጦርነት ከፍተው በቅንጅት እየሰሩ ነው። ፍላጎታቸው ምንድን ነው?**

**አቶ የሱፍ፦** ኢትዮጵያ በአፍሪካ የነጻነት አርማ ፤ የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት፣ ለቅኝ ግዛት ያልተንበረከከችና ያልገበረች አገር ስለሆነች ምዕራባውያኑ ታሪካችን አይመቻቸውም። በሰብዓዊነት፣ በነጻነትና በፍትሕ ሥም የመሸጉ አካላት የቅኝ ግዛት ውርስና ምልከታ አሁን ድረስ አለ። አሜሪካ ውስጥ ጥቁር ሕዝቡ የሚኖርበት የዘረኝነት ሁኔታ የምናውቀው ነው። የዘረኝነት ፖለቲካ የመጨረሻው የመንግሥት ማዕቀፍ ውስጥ



ያለ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ኢትዮጵያዊነትን መሠረት ሲያደርግና ነጻነቷንና ታሪኳን በቅጡ እውቅና እየሰጠ ሲሄድ ተረብሸዋል። በሕወሓት ስርዓት ወቅት ከፍተኛ መኃሳቆልና መጉደፍ የደረሰበት ኢትዮጵያዊነት ወደ ቦታው መመለሱ ፤ አርበኝነት ቦታውን መያዙ ፤ የነጻነት ፍላጎትና ጣልቃ ገብነትን መከላከል እምቢተኝነት መደራጀቱ ፤ የኢትዮጵያ ሉአላዊነት መሠረቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጂ የማንም ፍላጎትና ጣልቃ ገብነት ሊሆን እንደማይችል እና የሌላ አገር ሕዝብም ይሁን መንግሥት ስርዓት ሊሆን እንደማይችል ተግባቦት ላይ እየተደረሰ መምጣቱ በጉልህ እየታየ መምጣቱ አልተመቻቸውም።

ኢትዮጵያ ጠንካራና የለማች በሕዝቧ ፍቃድና ይሁንታ የምትተዳደር አገር መሆን የለባትም የሚል የቆየ የውርስ ፖለቲካ አላቸው። ያንን አሁን በየቦታው እያጡት ሲመጡ ነው ተቃውሞ እያቀረቡ ያሉት። ሕወሓት ቀድሞም ተንበርካኪ ስለነበር በትጥቅ ፣ በመረጃና በገንዘብ የተወሰነ ድጋፍ ቢደረገለት ኢትዮጵያን ለማፍረስ ይችላል በሚል ነው አብረውት እየተሰለፉ ያሉት። ስለዚህ በአጠቃላይ ሰብዓዊ ድጋፍ ፣ የዜጎች መብት ፣ በሕግ የበላይነት ወዘተ. እየተባለ የሚወራው ሁሉ ፖለቲካ ነው። ሕወሓት ቀደም ሲል በፈጸማቸው ሰቆቃዎች ፣ ጅምላ ፍጅቶች ፣ አፈናዎች፣ እስራቶች፣ ግርፋቶች እና ግድያዎች ከእነዚህ የውጭ ኃይላት ጉልህ ድምጽ ተሰምቶ አያውቅም። አሁን በልዩ ሀኔታ ኢትዮጵያ ላይ እየተደረገ ያለው ርብርብ ተንበርካኪ አገር ለመመስረት ባላቸው ፍላጎት ነው።

ኢትዮጵያ በጂኦ ፖለቲካዊ ይዞታዋ በጣም አስፈላጊ አገር ስለሆነች በራሷ እግር መቆም ከጀመረች ስጋት ትሆንብናለች ብለው ያስባሉ። ስለዚህ ለእነሱ ፍላጎት የሚጋለብና ተንበርካኪ የሆነ ፣ የአገርን ጥቅም ትቶ ለእነሱ ጥቅም ብቻ የሚሠራ ፣ ለቡድንና ለግለሰብ ጥቅም የሚንቀሳቀስ ኃይል ወደ ማዕከል ማምጣት ይፈልጋሉ።

ይህ የሆነው በእኛ አገር ብቻ አይደለም። ሊቢያና ሶሪያ ላይ እንዲሁም በርካታ አገራት ላይ ተፈጽሟል። የአሜሪካ መንግሥት በሕዝብ መካከል ፈንጂ የሚያፈነዱ የኮንትራት ሚሊሻዎችን በላቲን አሜሪካ እያሰማራ ፕሬዚዳንቶችን፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮችን፣ አመራሮችን ሲያስገድልና ሲገድል የነበረ ስርዓት ነው። ይሄ በታሪክ ተመዝግቦ ያለ ጉዳይ ነው። ምዕራባውያኑ በአፍሪካ ውስጥ አምባገነንና ዘረኛ፣ የተወሰነ ቡድን ብቻ የሚወክሉ ስርዓቶችን በጦር መሳሪያ ፣ በገንዘብና በፕሮፖጋንዳ ሲደግፉ የኖሩ ናቸው። ይሄንን በተገቢው ተገንዝበን በልኩ መመከት ይኖርብናል።

**ዘመን ፡- ኢትዮጵያውያን የምዕራባውያኑን ጫና ተቋቁመው ሁኔታውን ለመቀልበስ ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?**

**አቶ የሱፍ፡-** ውለው ያደሩ በርካታ ችግሮች አሉብን። እነሱን ለመፍታት ስንንቀሳቀስ ሰቆቃ መጥቶብናል። ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያዊነት ይሄንን ሁሉ ውጣ ውረድ ይቋቋማሉ። ከዚህም በኋላ ቀጣዩ ትውልድ ልጆቻችን እና የልጅ ልጆቻችን የተሻለ አገር ይወርሳሉ። ለዚህም ስኬት እኛ እጅ ለእጅ ተያይዘን ልዩነቶቻችንን በጉያችን ይዘን ትብብሮችን በማድረግ ማሸነፍ መቻል አለብን። ይሄ የታሪክ ጥሪ ነው። የእያንዳንዳችን አስተዋጽኦ ለታሪኩ ፍሰት ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ በተሠማራንበት ሁሉ በውስጥም በውጭም ርብርብ ማድረግ ይገባናል። አሁን ግንባር ቀደም ጉዳያችን የአገርንና የሕዝብን ህልውና አደጋ ላይ የጣለውን የሽብር ጥምረቱ በፈለገውና እየተንቀሳቀሰበት ባለው መንገድ በጠመንጃ ማንበርከክና ማሸነፍ ነው።

ከዚያ በኋላ ሕዝቡ እንደየፍላጎቱ ይወክሉኛል የሚላቸውን አደረጃጀቶች በማዋቀር አመራሮችን በመወከል ሰፊ አካታች ብሔራዊ ውይይትና ድርድር ይኖራል። አዲስ ማህበራዊ ውል ሊጻፍ ይችላል፤ ይጻፋልም። ያለፉ ችግሮቻችን እንዴት ፈተን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መውጣት አለብን የሚል ሥራ ይጠብቀናል። ምሁራኖቻችን፣ አመራሮቻችን፣ የፖለቲካ ኃላፊዎቻችን እና የሕዝባችን ተወካዮች ሁሉ የሚሳተፉባቸው በርካታ የተለያዩ መድረኮች ይፈጠራሉ። ዝርዝሩ ከዋናው ሂደት በፊት በውይይትም በስምምነትም የሚታይ ነው የሚሆነው። ከዋናው መድረክ በፊት ቅድመ ድርድሮች ይኖራሉ። ዞሮ ዞሮ መውጫ መንገዱን ሁላችንም በጋራ የምንተልመው ይሆናል። አሁን ግን በእንደዚህ አይነት ሰላማዊ ፣ ፍትሀዊ እና እኩል በሆነ መድረክ በሰለጠነ መንገድ መፍታት የማይፈልገው ኃይል ከፖለቲካ ማዕቀፉ በፈለገውና በመረጠው አግባብ ተገፍቶ መወገድና መሸነፍ አለበት።

በውስጥና በውጭ እኩያን ኃይሎች ጥምረት አገራችንን እና ሕዝባችንን ለማፍረስ የሚደረገውን ርብርብ በታሪክ አስመዝግበናቸው እንዳለፍናቸውና ነጻነታችንን አስጠብቀን እንደኖርንባቸው ድሎቻችን ዳግም ታሪክ የምንሠራበት ወቅት ነው የሚል መልዕክት አለኝ።

**ዘመን፡- በቀጣይ የኢትዮጵያ እጣ ፋንታ ምን ይሆናል?**

**አቶ የሱፍ፡-** ኢትዮጵያ ያጋጠሟትን ተግዳሮቶችና ስጋቶች ሁሉ በታሪክ እንደተሻገረቻቸው አሁንም ትሻገራለች። የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ተሞክሮዎች አሉት ፤ ብዙ ሰቆቃዎችንና ጥቃቶችን አስተናግዷል። እንደ አገርና ሕዝብ ነጻነታችንን ያስከበርነው እንደሌሎች አገራት በውጭ ወይም በሶስተኛ ወገን ፍላጎትና ይሁንታ ሳይሆን መራር መስዋዕትነት በመክፈል ነው። ይህ ታሪክ ተመዝግቦ ያለ እውነት ነው። ከዚህ ተሞክሮና ልምድ እንወስዳለን። ታሪክ ተመዝግቦ የሚነበብ ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ተመሳክሮ ለተግባራዊ ስምሪት የሚውል ነው። አሁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የአባቶቹንና የቅድመ አያቶቹን ገድል ለመፈፀም በማያወላዳ ሁኔታ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሷል።

ኢትዮጵያ አሸናፊ ሆና ትወጣለች ለዚህ ምንም ጥያቄ የለም። ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነጻነት ቀንዲልና መሰባሰቢያ ማዕከል መሆኗ ይቀጥላል ፤ ተስፈኞቹም ይሸነፋሉ። እንደዚህ አይነት ስምሪት ዳግም እንዳይወሰድ ትምህርት ይሰጥበታል። እኛም አገር በመገንባቱ ሂደት የበኩላችንን ጥረት እያደረግን እንቀጥላለን። ይሄ በቅርቡ እውን የሚሆን ጉዳይ ነው። ዝም ብሎ መላምት ሳይሆን ተጨባጭ የሆኑ ነገሮች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሰጠ ትክክለኛ የሆነ አስተያየት ነው።

**ዘመን ፡- የተጣበበ ጊዜዎትን መስዋዕት በማድረግ ሰፊ ጊዜ ወስደው የተብራራ ምላሽ ስለሰጡን ከልብ እናመሰግናለን።**

**አቶ የሱፍ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# "በቀበሮ ጉድጓድ..."

**የትናየት ፈሩ**

ሕወሓት በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት መፈጸሙን ተከትሎ በተደረገ ሕግ የማስከበር ዘመቻ መቐለን ጨምሮ የተለያዩ የትግራይ ከተሞችን በሦስት ሳምንት ውስጥ መቆጣጠር መቻሉ ይታወሳል። ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ መቐሌ መያዟን ተከትሎ ኅዳር 19 ቀን 2013 ዓ.ም በሰጡት መግለጫ ጦርነቱ መጠናቀቁን ጠቅሰው ቀጣይ የመንግሥታቸው ተግባር በሕግ የሚፈለጉ የሕወሓት አመራሮችን በቁጥጥር ሥር ማዋልና ትግራይን መልሶ መገንባት መሆኑን አስታውቀዋል። መከላከያ ሠራዊት በትግራይ በነበረው ቆይታ ከፍተኛ የሕወሓት አመራሮችን በቁጥጥር ስር አውሎና ደምስሶ ከስምንት ወራት በኋላ የተናጥል ተኩስ አቁም በማወጅ ሙሉ ለሙሉ ክልሉን ለቅቆ መውጣቱም የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

ሕወሓት በከፈተው ጦርነት የኢትዮጵያ ጠላቶች ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም እንዲንቀሳቀሱ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። የሱዳን ጦር አጋጣሚውን በመጠቀም የኢትዮጵያን መሬት ወርሯል። ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን የሚተነትነው ጂኦ ፖለቲክስ የተባለው ተቋም ያጋለጠው መረጃ እንደሚያመለክተው የሕወሓት ቡድን በሀገር መከላከያ ሠራዊት የሰሜን እዝ ላይ የፈጸመውን ጥቃት ተከትሎ የሕግ ማስከበር ዘመቻው ከተጀመረ በኋላ የአውሮፓ ኅብረት ባለስልጣናት እ.ኤ.አ ኅዳር አንድ ቀን 2013 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግሥት ሊዳከም በሚችልበት ሁኔታ ላይ ውይይት አድርገው ባለ ሰባት ገጽ ሰነድ እስከ ማዘጋጀት ደርሰዋል።

ምዕራባውያኑ የሕግ ማስከበር ዘመቻውን ተጠቅመው የአዲሲቷን ኢትዮጵያ እውን መሆን ለማደናቀፍና ለእነሱ ታዛዥ የሆነ እንደፈለጉ እጁን የሚጠመዝዙት መንግሥት ለመመሥረት ሕወሓትን በተለያየ መንገድ በማገዝ፣ ለወንጀሎቹ ሽፋን በመስጠት የተለያዩ አካላትን ያሳተፈና የተናበበ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህ ጽሑፍ በዚህ ረገድ ያለውን የምዕራባውያኑን ፈርጀ ብዙ እንቅስቃሴ፣ የኢትዮጵያን ተጋድሎ እና የወዳጅ አገራትን ድጋፍ ይቃኛል።

## የተቀናጀ ዘመቻ

ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችና ብዙኃን መገናኛዎች የኢትዮጵያን ስም በማጠልሸት ዲፕሎማሲያዊ ጫናዎችን ለማበርታትና ማዕቀቦችን ለማስከተል በተደጋጋሚ የተቀናጁ ዘመቻዎችን አድርገዋል። ሲ. ኤን. ኤን፣ ሮይተርስ፣ ኒውዮርክ ታይምስ፣ አሶሼትድ ፕረስ፣ ዋሽንግተን ፖስት፣ ቢቢሲ እና ሌሎችም ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሙያዊ መርኅን ባልተከተሉ ሐሰተኛ ዘገባዎች የኢትዮጵያን እውነት አዛብተው ለዓለም ሲያቀርቡ ቆይተዋል፤ አሁንም ቀጥለውበታል።

ሲ. ኤን. ኤን. ብቻ ኢትዮጵያን የተመለከቱ አያሌ ሐሰተኛ ዘገባዎችን አሰራጭቷል። ለአብነትም ጳጉሜ 4/2013 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ወታደሮች ተገድለው ተከዜ ወንዝ ውስጥ ስለመጣላቸው "የአስከሬን ምርመራ ባለሙያዎች ማረጋገጫ ሰጥተውበታል" በሚል ያለ ተጨባጭ ማስረጃ ያቀረበው ዘገባ ተጠቃሽ ነው። ጣቢያው "የኢትዮጵያ አየር መንገድ የጦር መሣሪያዎችን ወደ ጎረቤት አገር ኤርትራ አጓጉዟል" ሲልም መሠረተ ቢስ ክስ በማቅረብ የአየር መንገዱን ስም ለማጠልሸት ሞክሯል። በአንጻሩ በማይካድራ፣ በአፋር ክልል ጋሊኮማ፣ በአማራ ክልል ዳባት እና ጭና በተባሉ አካባቢዎች አሸባሪው በርካታ ንጹሐንን በጅምላ መፍጀቱን እንዲሁም በደብረ ታቦርና ተቆጣጥሯቸው በነበሩት አካባቢዎችም ባደረሰው ጥቃት በርካታ ሆስፒታሎችና የጤና ተቋማት መዘረፍና መውደማቸውን ለመዘገብ አልደፈረም።

እንደ አምንስቲ ኢንተርናሽናል ያሉ በሰብአዊነት ስም የፖለቲካ አጀንዳዎችን ለማስፈጸም የሚንቀሳቀሱ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት እና በተ.መ.ድ ስር ያሉ ድርጅቶች ለአሸባሪው ቡድን የወገኑ የተጋነኑ እና የፈጠራ ሪፖርቶችን በማውጣት የምዕራባውያኑን ፍላጎት ለማስፈጸም በከፍተኛ ደረጃ ሲንቀሳቀሱ ታይተዋል።

የተ.መ.ድ አድሏዊነት ፀሐይ ከሞቀ ከራርሟል። እስራኤል እየገነባች ባለችው የአይሁድ ሠፈራ መንደሮች የፍልስጤምን ጩኸት የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ በማለቱ፤ በኢራን የኑክሌር መርኅ ግብር ላይ አሜሪካንን ኮቴ እየተከተለ ድጋፍ በመቸሩ እና ዛሬም ላይ እየወደሙ ስላሉት ሶሪያ፣ ኢራቅ፣ ሊቢያና ሶማሊያ ግድ የማይሰጠው ድርጅት መሆኑና ምንም አለመፈየዱን በመጥቀስ የሚተቹት በርካቶች ናቸው። ምዕራባውያን ሶሪያን ለማውደም ጣልቃ በመግባት ዐማፅያኑን በመደገፍ የእርስ በእርስ ግጭቱን ለዓመታት ሲነዱት ተ.መ.ድ ዝምታን መርጧል።

ድርጅቱ ከውልደቱ እስከ ጉልምስናው በምዕራባውያኑ ቁጥጥር ስር ያለ አሻንጉሊት መሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ሩዋንዳ ውስጥ የተከሰተውን የዘር ማጥፋት እልቂት ቀድሞ መከላከል ያልቻለው ድምፅን በድምፅ የመሻር መብት ባላቸው አሜሪካን እና ፈረንሳይ ውሳኔ ነው። አሜሪካ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ፣ ፈረንሳይ ደግሞ አጋሮቿን ላለማጣት በሚል ከየጥቅሞቻቸው በመነሣት ስሌት ውስጥ በመግባታቸው የአንድ ሚሊዮን ገደማ ሩዋንዳውያንን እልቂት ማስቆም ሳይቻል ቀርቷል።

> **"ሕወሓት በከፈተው ጦርነት የኢትዮጵያ ጠላቶች ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም እንዲንቀሳቀሱ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል**

ኢትዮጵያ ከ53 የድርጅቱ መሥራች ሀገሮች አንዷ ነች። ለዓለም አቀፍ ሰላምና የጋራ እንቅስቃሴ ማደግ የበኩሏን አስተዋጽኦ ስታበረክት ቆይታለች። ሰላምና ፀጥታ የማስከበር ሚናዋን በኮሪያ፣ ኮንጎ፣ ሩዋንዳ፣ ብሩንዲ፣ ላይቤሪያ፣ ሶማሊያ፣ አብዬና ዳርፉርም በሚገባ ተወጥታለች። ይኸው ተሳትፎ አሁንም ቀጥሏል። በ1959 ዓ.ም፣ ከ1981 ዓ.ም እና በ2009 ዓ.ም የመንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ተለዋጭ አባል በመሆን ተመርጣ ለሦስት ጊዜ አገልግላለች። ድርጅቱ ለዚህ ውለታዋ የማይመጥን ምላሽ ሲሰጣት ይህ የመጀመሪያዋ አይደለም። ኢትዮጵያ በጣሊያን ዳግም ወረራ በተፈጸመባት ወቅትም ፍርደ ገምድልነቱን በተግባር አሳይቷል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ በቅርቡ ከአልጀዚራ ጋር ባደረጉት ቆይታ አሸባሪውን ቡድን "ጠንካራ ተዋጊ ነው የኢትዮጵያ መንግሥት ሊያሸንፈው አይችልም" ሲሉ በማሞካሸት ከድርጅታቸው መርኅ ጋር የሚጣረስ አስተያየት እስከመስጠት መድረሳቸው ይታወሳል። ጉተሬዝ ይህን መሰል አስተያየት ሰጥተው ሲያበቁ፣ የዓለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (አይ. ኦ. ኤም) የኢትዮጵያ ኃላፊ ማውሪን አቻንግን እና የሥነ ሕዝብ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዋ ዴኒያ ጌይልን "የድርጅቱን እሴቶች የማያንጸባርቅ" አስተያየት ሰጥታችኋል በሚል

**ኢትዮጵያ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያላት ግንኙነት በመሻከሩ አሸባሪው ቡድን የሰነዘረባትን ጥቃት ለመቀልበስ ከሌሎች ወዳጅ አገራት ጋር ያላትን ሁለንተናዊ ግንኙነት አጠናክራለች**

ኒውዮርክ ወደ ሚገኘው የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ተጠርተው አስተዳደራዊ ዕረፍት እንዲወስዱ አድርገዋል። ኃላፊዎቹ ከኢትዮጵያ የተጠሩት ተ.መ.ድ ከሽብርተኛው ቡድን ሕወሓት ጋር ባለው ግንኙነት ተቋማዊ አድሏዊነትን መከተሉን በግልፅ በመናገራቸው፤ አሸባሪውን ቡድን «ጨካኝ» ብለው በመግለጻቸው እና የተ.መ.ድ የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ አስተባባሪዎች አዲስ አበባ የሚገኙ ከፍተኛ የተ.መ.ድ ኃላፊዎችን በማግለል በድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት ካሉ ኃላፊዎች ጋር በቀጥታ ይገናኛሉ ብለው በመናገራቸው ነው።

አሜሪካዊው የፖለቲካ ተንታኝና ጋዜጠኛ አንድሪው ኮርይብኮ "የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ የፈጸማቸው ሦስት ቅሌቶች" በሚል ባቀረቡት ጽሑፍ ፣ ተ.መ.ድ እና አሜሪካ በመንግሥታቱ ድርጅት ሙሰኛ ሠራተኞች አማካይነት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ጫና ለማሳደር እያከናወኑት ያለውን ድብቅ ሴራ አጋልጠዋል። ለአብነትም የሰብአዊ እርዳታ ጭነው ትግራይ ክልል የገቡ የዓለም ምግብ ድርጅት 428 ተሽከርካሪዎች ሳይመለሱ ስለመቅረታቸው ተ.መ.ድም ሆነ አሜሪካ ምንም ዓይነት መረጃና ምላሽ ከመስጠት መቆጠባቸውን አንሥተዋል። ተሽከርካሪዎቹን ሕወሓት ወደ ጦር ሜዳ አስገብቶ እየተጠቀማቸው መሆኑን ለመናገር እንዳልደፈሩም ጠቅሰዋል።

በተገላቢጦሹ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሰብአዊ አቅርቦት እንዳይደርስ መተላለፊያ መንገዶችን ዘግቷል የሚል መሠረተ ቢስ ክስ ላይ መጠመዱን ይገልጻሉ። ይህም የመንግሥታቱ ድርጅት እና አሜሪካ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት ባለፈ መንግሥት በትግራይ ክልል የሰብአዊ እርዳታ እንዲደርስ እያደረገ ያለውን ጥረት ለማጠልሸት ብሎም እውቅና ላለመስጠት የሚያደርጉት ሴራ ነው ይላሉ። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ መንግሥት በሀገሪቱ የተሰማሩ የመንግሥታቱ ድርጅት ሰባት ሙሰኛ ሠራተኞች ከተሰጣቸው የሥራ ሃላፊነት ውጪ ለሽብር ቡድኑ ድጋፍ ሲሰጡ በመገኘታቸው ከሀገር እንዲወጡ ማድረጉን አስታውሰዋል። ይሁን እንጂ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሠራተኞቹ የፈጸሙትን ያልተገባ ሥራ ማጣራት እና ቅጣት ማስተላለፍ እንዲሁም በሌሎች ታማኝ ሠራተኞች መተካት ሲገባው ዓይኑን በጨው አጥቦ በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ አላስፈላጊ ጫና ለማሳደር ታትሮ እየሠራ መሆኑን በመጥቀስ ተችተዋል።

## ትዕዛዝ እና ዛቻ

አሜሪካ በተደጋጋሚ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን ከራሱ ግዛት እንዲወጣ ትዕዛዝ እስከመስጠት ደርሳለች። በአውሮፓ ኅብረትና በአሜሪካ መንግሥታት ውስጥ ከፍተኛ ባለሥልጣናት የነበሩት አሌክስ ሮንዶስ እና ማርክ ሜዲሽ ፖሊቲኮ በተባለ መጽሔት ላይ በጋራ ባወጡት ጽሑፍ "ሰላም ለማምጣት የሚደረገው ጥረት ካልተፋጠነ ኢትዮጵያ የዩጎዝላቪያ ዕጣ ሊገጥማት ይችላል ውጤቱም የከፋ ይሆናል" ሲሉ ዝተዋል።

የአውሮፓ ኅብረትና አሜሪካ የዓለም ባንክና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት ለኢትዮጵያ ከሚሰጡት ብድር የተወሰነውን እንዲይዙ ሊያደርጉ እንደሚችሉ እና ኢትዮጵያን ምርታቸውን ከቀረጥ ነጻ ወደ አሜሪካ ከሚልኩ የአፍሪካ አገራት ዝርዝር ውስጥ ለማስወጣት በመዛት የኢትዮጵያ መንግሥትን ለማንበርከክ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል። ተጨማሪም በየፊናቸውም ለኢትዮጵያ ለመስጠት ያቀዱትን በመቶ ሚሊየኖች ዶላር የሚቆጠር ድጋፍ በማቀብ እርምጃዎችን ወስደዋል።

በካሊፎርኒያ እስቴት ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ ፕሮፌሰሩ አለማየሁ ገብረማርያም በቅርቡ ከዘመን መጽሔት ጋር ባደረጉት ቆይታ የባይደን አስተዳደር ሁሉንም ዓይነቶች የኢኮኖሚያዊ፣ ዲፕሎማሲያዊ እና ፖለቲካዊ ማዕቀቦች በመጠቀም አስፈራርቷል። አሜሪካ የአውሮፓ የገንዘብ ተቋማት ተመሳሳይ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ተናባ እየሠራች ነው። አሜሪካ በምታደርገው ማዕቀብ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ፣ ማኅበረሰባዊ እና የፖለቲካ ሂደት በማተራመስ አከርካሪዋን ለመስበር እና ጉልበቷ ስር ለማንበርከክ ሁሉንም ነገር ትጠቀማለች። አሜሪካ ከአውሮፖ ኅብረት ጋር በመሆን በጉልበቷ እንደ ዓለም ባንክ እና ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም ያሉ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት አዳዲስ ብድሮችን እንዲከለክሉ፣ የብድር መክፈያ ጊዜ እንዳያራዝሙ ወዘተ እና ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ስምምነቶችን እንዳያድሱ ለመከልከል ተባብራ እየሠራች ነው ብለው እንደሚያስቡ ገልጸው ነበር። የሆነውና እየሆነ ያለው ይሄው ነው። ምዕራባውያኑ የምናዛችሁን ካልፈጸማችሁ እንዲህ ያለ ቅጣት ይከተላችኋል በሚል ማስፈራሪያ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዛቸውን ለማስፈጸም አሮጌ አቁማዳቸውን ይዘው ኢትዮጵያ በር ላይ ቆመዋል።

መቀመጫቸውን ካናዳ ያደረጉት የኢትዮጵያ ጉዳዮች ተንታኝ ፕሮፌሰር ፊትዝ ጀራልድ አሜሪካና የአውሮፓ ኅብረት በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ የቅጣት እርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀታቸውን ይተቻሉ። "ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከሕጋዊው የኢትዮጵያ መንግሥትና በጦርነቱ ከተጎዱት ከትግራይ፣ ከአማራ እንዲሁም ከአፋር ክልሎች ጋር ነው መቆም ያለበት። በሕወሓት በተፈጸሙ ጭፍጨፋዎች ላይ በማተኮር መሣሪያውን እንዲያስቀምጥ ጥሪ ማቅረብ አለባቸው" ሲሉም ይመክራሉ።

## የወዳጅ አገራት አጋርነት

ኢትዮጵያ ከአሜሪካና ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያላት ግንኙነት በመሻከሩ አሸባሪው ቡድን የሰነዘረባትን ጥቃት ለመቀልበስ ከሌሎች ወዳጅ አገራት ጋር ያላትን ሁለንተናዊ ግንኙነት አጠናክራለች። ምዕራባውያኑ ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ ከኢራን፣ ከቱርክ እና ከቻይና፣ የገንዘብ ብድር ከዩናይትድ አረብ ኤምሬትስና ሳዑዲ አረቢያ እንዲሁም ፖለቲካዊ ድጋፍ ደግሞ ከሩሲያና ቻይና በማግኘት ከምዕራባውያን ውጪ የምትፈልገውን ለማሳካት እየተንቀሳቀሰች ነው" በሚል ስጋት ሲገባቸው እየተስተዋለ ነው። ሩሲያና ቻይና በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት ኢትዮጵያን በተመለከተ በአሜሪካና አጋሩዎቿ የሚቀርቡ የውሳኔ ሐሳቦችን ውድቅ ማድረጋቸው የስጋታቸው እምብርት ነው።

የመንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት በኢትዮጵያ ጉዳይ ከዐሥር ጊዜ በላይ ስብሰባዎችን አድርጓል። አየርላንድ የጸጥታው ምክር ቤት በትግራይ ክልል ስላለው የሰብአዊ እርዳታ የኢትዮጵያን መንግሥት በመጫን በአንድ ድምፅ መናገር አለበት ስትል የአሜሪካ፣ የዩናይትድ ኪንግደም፣ ፈረንሳይ፣ ኖርዌይ እና ኢስቶኒያን ድጋፍ ይዛ በተደጋጋሚ ብትወተውትም ሩሲያ እና ቻይና "በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳይ ጣልቃ መግባት ነው" የሚል አቋም በማራመዳቸው ምክንያት ያለውጤት ተበትኗል።

በእነዚህ መድረኮች ቻይና "በሰብአዊ እርዳታ

> **በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምዕራባውያኑ በአንዲት ሉዐላዊት አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ፈላጭ ቆራጭ ለመሆን እያደረጉ ያሉትን ጥረት ተቃውመዋል**

ስም የውጪ ጣልቃ ገብነት መኖር የለበትም። የአፍሪካ ችግር በአፍሪካውያን ይፈታ" የሚል አቋም ይዛለች። ኢትዮጵያ ላይ የተጣሉ ማዕቀቦች ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጻረሩ እና ችግሩን ከመፍታት ይልቅ የሚያባብሱ መሆናቸውን በመግለጽም የምዕራባውያኑን እርምጃ ተቃውማለች።

ሩሲያ በሰሜን ኢትዮጵያ ያለውን ሰብአዊ ሁኔታ ከፖለቲካ ጉዳይ መነጠል ያስፈልጋል። በትግራይ በሚደረገው ሰብአዊ እርዳታ መድልዎ መኖርም የለበትም ብላለች። የውጭ ድጋፍ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና የፖለቲካ ነጻነት በጠበቀ መልኩ ብቻ መሰጠት አለበት ስትልም አሳስባለች። የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት አገሪቱን በአንድነት ወደ ሰላም የመውሰድ አቅም አለው ብላ በጽኑ እንደምታምን በመግለጽ እንደ ቻይና ሁሉ ኢትዮጵያ ላይ የተጣሉ ማዕቀቦችን አውግዛለች። የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ማሪያ ዛካሮቫ የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም በሌሎች ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት የሚያደርገውን ሙከራ እንዲያቆም በመጠየቅ ሩሲያ ለኢትዮጵያ ያላትን አጋርነት አሳይተዋል።

ሕንድ የኢትዮጵያ መንግሥት የሰብአዊ ቀውስ ለማሻሻል እያደረገ ባለው ጥረት የሰብአዊ እርዳታ አቅርቦት እየተሻሻለ መሆኑን በመግለጽ ኢትዮጵያ ለምታደርገው ጥረት ከዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዕውቅና ሊሰጣትና አስፈላጊው ድጋፍ ሊደረግላት ይገባል። በኢትዮጵያ ለተፈጠረው ችግር መፍትሔ ለማምጣት የሚደረገው ጥረት በእራሷ በኢትዮጵያ የሚመራና በሕገ መንግሥቷ ማዕቀፍ ውስጥ መሆን አለበት በማለት ሕንድ ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ነጻነት፣ ሉዓላዊነትና የግዛቷ መከበር ቁርጠኛ መሆኗን ገልጻለች።

ሌላዋ የኢትዮጵያ ወዳጅ ቱርክም አጋርነቷን በአደባባይ ገልጻለች። ፕሬዝደንት ሬሲፕ ጣይብ ኤርዶጋን ከጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አህመድ ጋር በስልክ ባደረጉት ውይይት "ቱርክ ለኢትዮጵያ የትኛውንም አይነት ድጋፍ ማድረጓን ትቀጥላለች፤ ለኢትዮጵያ ሰላም እና መረጋጋት ትልቅ ዋጋ ትሰጣለች" ሲሉ ከኢትዮጵያ ጎን መቆማቸውን አረጋግጠዋል።

በኋላም ፕሬዝደንት ሬሲፕ ጣይብ ኤርዶጋን በቱርክ የስራ ጉብኝት እንዲያደርጉ ያቀረቡላቸውን ግብዣ ተቀብለው ወደ ቱርክ ያቀኑት ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ የአገራቱን የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከር የሚያስችሉ በወታደራዊና በውኃ ዘርፎች የሚደረጉ ትብብሮችን ያካተተ ስምምነት ተፈራርመዋል።

በርካታ የአፍሪካ አገራት ኢትዮጵያ አሸባሪውን ቡድን ለማስወገድ እየወሰደች ያለችው እርምጃ የአንድ አገር ውስጣዊ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ ከምዕራባውያኑ በተቃራኒ አቅጣጫ በመቆም ድጋፋቸውን ቸረዋታል። በጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በዓለ ሲመት ላይ የተገኙት የአፍሪካ አገራት መሪዎች ባደረጓቸው ንግግሮች ከኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ጎን መቆማቸውን የገለጹበት መንገድ ይህን የሚያረጋግጥ ነው።

## ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን

ምዕራባውያን አገራት ኢትዮጵያን አላወቋትም፤ ፈጽሞ አልተረዷትም። ደበበ ሰይፉ "የብርሃን ፍቅር" በሚል ርዕስ ባሳተመው የግጥም ስብስቡ "በቀበሮ ጉድጓድ" የተሰኘ አንድ ግጥም አካቷል። ግጥሙ ምዕራባውያኑ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ የሄዱበት መንገድ ከኢትዮጵያ በኩል ያልጠበቁትን ምላሽ ይዞ እንደሚመጣ ፈጽሞ አለማሰባቸውን ለማሳየት ጥሩ ምሳሌ ነው።

በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው
በቀበሮ ጉድጓድ ቀበሮ መስሏቸው
ውሾቹ አጓሩ በዛ ጩኸታቸው
አየሩን በከለው
ምድሩን አገረኘው፣
ትፉት ድንፋታቸው!
አይ የውሾች ነገር
ማን በነገራቸው
ማን ባስተማራቸው
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው !
አንበሳ እንደሆነ የሚጠብቃቸው !

ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ለ2014 ዓ.ም ዘመን መለወጫ በዓል ባስተላለፉት መልዕክት "ኢትዮጵያን የሚፈትኗት ኢትዮጵያን የማያውቋት ናቸው። ኢትዮጵያ ለሺሕ ዓመታት በነጻነት ኖረች ሲባል ትርጉሙን አይረዱትም ማለት ነው። ጠላት አጥታ አይደለም ሺሕ ዘመን በነጻነት የኖረችው። ፈተና ረስቷት አይደለም የነጻነት ቀንዲሏ ሳይጠፋ እስከ ዛሬ ያለው። ከከፍታዋ ያልወረደችው ኃያላን ራርተውላት አይደለም ። ሁሉንም እንደ አመጣጣቸው አሸንፋ ብቻ ነው። ታሪካችንን ሳያውቁ የሚገጥሙንን ታሪካችንን ዐውቀን እንጠብቃቸዋለን። ለወዳጃችን ወተት፣ ለጠላታችን ዕሬት መስጠት እንችልበታለን። ከቶም ኢትዮጵያ የሚለው ስም ከማሸነፍ እንጂ ከመሸነፍ ጋራ ተጠርቶ አያውቅም። ከነጻነት እንጂ ከባርነት ጋራ ዝምድና የለውም። ኢትዮጵያ ተፈትና ታውቃለች። ተሸንፋ ግን አታውቅም። ቀጥና ታውቃለች፤ ተበጥሳ ግን አታውቅም። የዘመመች መስላ ታውቃለች፤ ወድቃ ግን አታውቅም" በማለት ለምዕራባውያኑ ቆፍጠን ያለ አቋማቸውን አሳውቀዋቸዋል።

በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምዕራባውያኑ በአንዲት ሉዐላዊት አገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ፈላጭ ቆራጭ ለመሆን እያደረጉ ያሉትን ጥረት ተቃውመዋል። በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶች የሚኖሩ በሺሕዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በኒውዮርክ የመንግሥታቱ ድርጅት ዋና ጽሕፈት ቤት፣ በ ሲ. ኤን. ኤን. እና በኒውዮርክ ታይምስ ቢሮዎች በመገኘት ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል። የመንግሥታቱ ድርጅትና ሌሎችም አካላት በጽንፈኛው የሕወሓት ደጋፊዎች የሚሰራጨውን የሐሰት ፕሮፖጋንዳ ተመርኩዘው በኢትዮጵያ ላይ ለመፍጠር እየሞከሩ ያለውን ያልተገባና ኢ-ፍትሃዊ ጫና እንዲያቆሙ ጠይቀዋል። የኢትዮጵያ አሜሪካዊያን የዜጎች ምክር ቤትም በሲ.ኤን.ኤን የሚስተናገዱ ዘገባዎች ሙያዊ መርኅን ያከበሩና ትክክለኛ እንዲሆኑ ጣቢያውን ጠይቋል።

በቀጣይም የኢትዮጵያ መንግሥትና ዜጎቿ ምዕራባውያኑና በጥቅም የሚደለሉ የተ.መ.ድ. ሠራተኞች በውስጥ ጉዳያቸው ላይ እያደረጉ ያሉትን ጣልቃ ገብነት በማስረጃ በማጋለጥ በተደራጀ መንገድ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት አክብረው ከሚንቀሳቀሱ አጋር አገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከርና ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስሮችን ለማደርጀትም በትኩረት መሥራት አለባቸው።

# የሥልጣን ማጋራት ታሪካችን ሀ፧ሁ...

**ማለደ ዋስይሁን**

ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን ተገዳዳሪ፣ ተሻሚ፣ ተቀናቃኝ አያጣውም። ሁሌ መደላደል የለም፤ ጎንታይና ተጎንታይ ይኖራል። ለተጎንታይም ሆነ ለጎንታይ ደግሞ ተከታይ ተጽዕኖ መፍጠሪያ ኃይል አላቸው። ሁሉም በየደጁ ኃያል ነው። ወይም በሶሻሊስቶች አባባል ሁሉም በየመደቡ ኃይል ያደራጃል። እነዚህ የመገዳደር አካሄዶች የሚፈቱባቸው መንገዶችም ልዩ ልዩ ሆነው ታይተዋል። አንዳንዱ በኃይል ተገዳዳሪውን ከነወገኑ አጥፍቶ ወይም ረግጦ ለጊዜያት የመግዛት አካሄድ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ሰላማዊ በሚባለው መንገድ ልዩ ልዩ ማቻቻያ ጥበቦችን ተጠቅሞ ማለዘብ ነው። ከግጭት፣ ከፍጭት፣ ከጥፋት፣ ከምሬት አውጥቶ ተቻችሎ ለመዝለቅ ደግሞ እንደየመንግሥቱ ባሕርይ ችግር መፍቻ ጥበቦች ነበሩ።

መንግሥታት ንጉሣዊ/ዘውዳዊ/ ሥርዓት መልክ ይዘው ሊገኙ ይችላሉ። መንግሥታት ሪፐብሊክ ሆነው ሊሠሩ ይችላሉ። በፕሬዚዳንቶች፣ በጠቅላይ ሚኒስትሮች የሚመሩ መንግሥታት አሉ። እንዲሁ በአንድ ፓርቲ የሚመሩ እና መድብለ ፓርቲ ሥርዓት የሚከተሉም መንግሥታት ይኖራሉ። እነዚህን መሰል ቅርጽ ይዘው በሚሄዱት የትኞቹም መንግሥታት ግን ገዢውን የሚገዳደር ኃይል ይጠፋል ማለት አይቻልም።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ረጅሙን ጊዜ የወሰደው የዘውዳዊ ሥርዓት ነበር። ዘውዳዊ ሥርዓት መሆኑ ግን ተገዳዳሪ እንዳይበቅልበት ሊከለክል አይችልም። ስለዚህ የራሱ ሥልጣን ማጋሪያ መንገድ ይኖረዋል። ይህን በተመለከተ አስተያየት የሰጡን የባህልና ቱሪዝም ስተራቴጂ ኢክስፐርትና በታሪክና ቋንቋ ምሁር የሆኑት ዶክተር ታደለ ፈንታው «የዘውድ ሥርዓት ሥልጣን መቆናጠጫ ዋነኛ መስፈርቱ ደም ነው። ከንጉሣዊው ዘር የመወለድ ነገር ዙፋን የመቆናጠጥ ቁልፍ መንገድ ነው።» ይላሉ። በእርግጥም የኢትዮጵያ የዘውዳዊ ሥርዓት መወሰኛ ዋናው ሰነድ ክብረ ነገሥት ሆኖ ቆይቷል። ክብረ ነገሥት በዙፋን የሚቀመጠው ሰው ከእስራኤሉ ንጉሥ ከሰሎሞን እና ከንግሥተ ሳባ የሚወለደው የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የዙፋኑ ወራሽ መሆኑን ይወስናል።

ክብረ ነገሥት በምዕራፍ 87 ላይ ንግሥት ማክዳ ስላደረገችው ነገር ሲገልጽ እንዲህ ይላል፤ «መኳንንቶቹንም ‹በኢትዮጵያ መንግሥት ዙፋን ላይ የዳዊት ዘር ከሆነው ከንጉሥ ሰሎሞን ወንድ



**የልዕልት ዘነበወርቅና የራስ ኃይለሥላሴ ጉግሳ ጋብቻ**

ልጅ ካልሆነ በቀር ለዘላለሙ ሴቶችን እንዳታነግሡ ማሉ› አለቻቸው። ሁሉም የቤተ መንግሥቱ ታላላቆችና መኳንንቱ አማካሪዎችና ሹማምንቱ ሁሉ ማሉ። መንግሥቱንም አደሱ።...» በዚህም መሠረት በትረ ሥልጣን የሚገባቸው ሰዎች ማንነት የንጉሥ ዳዊት የዘር ግንድ ብቻ ነው።

ክብረ ነገሥት እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ድረስ ለኢትዮጵያ የሕገ መንግሥት ያህል ያገለግል ነበር። መጽሐፉ ተፈላጊና ለሚነግሡ ሰዎች የሥልጣን ዋስትና መስጫ መሆኑን ለመረዳት ዐፄ ዮሐንስ ተዘርፎ ጠፍቶ የሄደ ክብረ ነገሥት ከእንግሊዝ ለማስመለስ ያደረጉትን ጥረት ማስተዋል ይቻላል።

ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ (1864 ዓ.ም - 1881 ዓ.ም) ለንግሥት ቪክቶሪያ በነሐሴ 8 ቀን 1864 ዓ.ም በላኩት ደብዳቤ የእንግሊዝ ጦር ዐፄ ቴዎድሮስ ከሞቱ በኋላ በምርኮ ከመቅደላ ከተወሰዱት ንብረቶች መካከል ክብረ ነገሥት እንዲመለስላቸው ሲጠይቁ «... ደግሞ ክብረ ነገሥት አለ፤ አብሮ ሂዷል። የአገሬ ሹማምንቱን የአብያተ ክርስቲያናትን ስራት የሚናገር ነው፤ ባገሬ ተፋልሶ ሁኖብኛል፤ አሁንም ሁለቱን ክብረ ነገሥቱንና ኩራተ ርእሱን ቢሰዱልኝ እወዳለሁ፤ ካለበት ሁሉ አስፈልገው። ...» በማለት ደብዳቤ መጻፋቸው፤ የክብረ ነገሥትን አስፈላጊነትና ምን ያህል ጠቀሜታ እንደነበረው የሚያሳይ ነው። /ሕገ መንግሥት በኢትዮጵያ፣ቃለዓብ ታደሰ ሥጋቱ፣2009 ዓ.ም/

በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ዘመናዊ የሚባል ሕገ መንግሥት ተዘጋጀ በተባለበት ጊዜ ይኸው የክብረ ነገሥት የሥልጣን ማቆናጠጫ ሐሳብ የወጣው አዲስ ሕገ መንግሥት መነሻ ነበር። በ1923 ዓ.ም የወጣው ሕገ መንግሥት ምዕራፍ አንድ ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ተወላጅነትና ስለ ዘውዱ አወራረስ ሲናገር በመጀመሪያው አንቀጽ «የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዙፋንና ዘውድ ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰሎሞንና ንግሥተ ሣባ ከተባለችው ከኢትዮጵያ ንግሥት ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ተያይዞ ለመጣው ለንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘር ሊተላለፍ በሕግ ተወስኗል።» ይላል።

በ1948 ዓ.ም ተሻሽሎም ሲዘጋጅ በአንቀጽ ሁለት እና አራት ያሉት ይዘቶች የሚከተለውን የሚሉ ነበሩ።

«ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትነት ከኢትዮጵያ ንግሥት ከንግሥተ ሳባና ከኢየሩሳሌም ንጉሥ ከሰሎሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ሳያቋርጥ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘር ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ ሳይወጣ ምንጊዜም ይኖራል።»

«ንጉሠ ነገሥቱ ከነጋሢ ዘር በመሆኑና ቅብዐ መንግሥት በመቀባቱ ክብሩ የማይቀነስ፣ ማዕረጉ የማይገሰስ፣ ሥልጣኑ የማይደፈር ሆኖ በቆየውም ልማድ በአዲሱም ሕግ በሚገባው ክብር ሁሉ ይከበራል። ክብሩንም ለመንካት በድፍረት የሚነሣ ማንም ሰው በሕግ እንዲቀጣ ተወስኗል።»

ይህ የሚያመለክተው ለረጅም ዘመናት የሥልጣን ምንጭ የሆነው ደም/ከነገሥታት ዘር መወለድ ነው። ይህ ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ በነገሥታት ዘመን የነበሩ የገዢዎቹ ተገዳዳሪዎች ተቀናቃኝነታቸውን እንዲያለዝቡና የሥልጣን ተካፋይነት እንዲሰማቸው የሚደረግበት መንገድ የተቃውሞ መሪ የሆነው ሽፍታ፣ መስፍን፣ መኰንን... በጋብቻ ከትውልዱ እንዲቀላቀል በማድረግ ነበር።

ሄራን ሠረቀብርሃን የተባሉ ጸሐፊ በዓለም አቀፉ የአፍሪካ የታሪክ ጥናት መጽሔት ላይ Marriage and politics in the Nineteenth Century Ethiopia በሚል ርዕስ በጻፉት ጥናት የፖለቲካ ጋብቻ ሁነኛ ተቃዋሚዎችን ሥልጣን ማጋሪያ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ነው። ከጥንት የነበረውን ትተን በቅርብ ስለነበረው እናውሳ። ዐጼ ምኒልክ ልጅ ኢያሱን አልጋ ወራሽ አድርገው ሲናዘዙ ሥልጣኑን ለማደላደል ግን ከትግሬ ሰዎች፣ ከትግሬ መሳፍንት ጋር ያላቸውን ፍትጊያ መፍታት ስለሚያስፈልግ ኢያሱ የትግራዩን የራስ መንገሻ ዮሐንስን የሰባት ዓመት ሕፃን ልጅ ሮማነወርቅን እንዲያገባ ተደርጎ ነበር። የፖለቲካ ጋብቻ ሁኔታ እቴጌ ጣይቱን የዚህ አካሄድ ቀንደኛ ፈጻሚ ሆነው ተስለው እናገኛቸዋለን።

ፕሮፌሰር ባሕሩ በመጽሐፋቸው «ሮማነወርቅ ለጣይቱም ዝምድና ስለነበራት ጋብቻው

**“ለረጅም ዘመናት የሥልጣን ምንጭ የሆነው ደም/ከነገሥታት ዘር መወለድ ነው። ይህ ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ በነገሥታት ዘመን የነበሩ የገዢዎቹ ተገዳዳሪዎች ተቀናቃኝነታቸውን እንዲያለዝቡና የሥልጣን ተካፋይነት እንዲሰማቸው የሚደረግብት መንገድ የተቃውሞ መሪ የሆነው ሽፍታ፣ መስፍን፣ መኰንን... በጋብቻ ከትውልዱ እንዲቀላቀል በማድረግ ነበር”**

የንግሥቲቱንም ፍላጎት ለማርካት ተብሎ ሳይሆን አይቀርም። » /ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ገጽ 126/ ብለዋል። «የፖለቲካ ጋብቻ ለኢትዮጵያ እንግዳ ነገር ባይሆንም እንደ ጣይቱ ግን ከፍተኛ ደረጃ ያደረሰው ሰው የለም ተብሎ ይታመናል። እንዲህ ካመቻቸቻቸው ጋብቻዎች ምናልባት ዋነኛው የወንድሟ የራስ ወሌ ብጡል ልጅ የሆነው የራስ ጉግሳ ወሌና የዘውዲቱ ምኒልክ ጋብቻ ነው። »/ ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ገጽ 127/

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም ከትግሬና ከሌሎችም አካባቢዎች የፖለቲካ ልሂቃን ጋር የነበራቸውን ተገዳዳሪነት ለማለዘብ ይህንኑ መንገድ ተከትለዋል። ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በውጤቱ ብዙም ባይጠቀሙም፣ እስከ ክህደትም ድረስ የደረሰ ተገዳዳሪነት ቢያጋጥማቸውም ልዕልት ዘነበወርቅን ለትግራዩ ራስ ኃይለሥላሴ ጉግሳ ድረው ነበር።

ዶክተር ታደለ ፈንታውም በጋብቻ የሚሰጠውን ሥልጣን በተመለከተ ሲያብራሩ የፖለቲካ ጋብቻ የባላንጣዎችን ጫና ለማቅለል፣ የራስን ሥልጣን የበለጠ ሰላማዊና የተደላደለ ለማድረግ ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስጠበቅ ጠቅሟል ይላሉ። ጋብቻው በነገሥታቱ ሳይወሰን መሳፍንቱና መኳንንቱ ተፎካካሪና ተገዳዳሪዎቻቸውን በዚሁ መንገድ ለማለዘብ ያውሉት ነበር። መሠረቱ ተገዳድለው በደም የሚፈላለጉ ሰዎች ደም ለማድረቅ እንደ መፍትሔ ይጠቀሙበት ከነበረውም ባህል ጋር የተሳሰረ ይመስላል።

የፖለቲካ ሥልጣኑ ግን በደም ውርስ መሆኑ ጋብቻን ብቸኛ መፍትሔ ማድረግ ለዘውድ ሥርዓቱ እንደ ጥበብ ነበር። ከዚህ ያፈነገጠውን ግን አፈንጋጭ፣ ዘረ ቢስ፣ ወረኛ፣ ሕግ አፍራሽ ወዘተ ብሎ ማውገዝ የተለመደ ነው። አገው ሥርወ መንግሥት በሰሎሞናውያን ይነቀፍ የነበረው ይህን በክብረ ነገሥት የተቀመጠውን የሰሎሞናዊ ደም በዙፋን ከማስቀመጥ ያፈነገጠ አዲስ ሥርወ መንግሥት ሆኖ በመገኘቱ ነበር።

በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና የጂኦፖለቲክስ ጉዳዮች ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር የሺጥላ ወንድሜነህ በበኩላቸው በዳግማዊ ምኒልክና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የሚኒስቴር ቦታዎችን በዘር ሳይሆን በተጫለ መጠን ብቃት ላላቸው ሰዎች የመስጠት ልምምድ እንደነበርም መረሳት የለበትም ይላሉ። ዓላማው ግን መንግሥትን የማዘመንና የማደላደል እንጂ የማጋራት ሐሳብ መሆኑ ላይ ጥያቄ ሊነሣ እንደሚችል ያሳስባሉ።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት መውደቅ በኢትዮጵያ የነበረውን የፖለቲካ ባህል ወደ ጎን የገፋ ነው። የፖለቲካ ኃይል ሆኖ ለመውጣት እንደ መደራጀ ሆኖ መታየት የጀመረው ርዕዮተ ዓለም ነው። ንጉሡን ሥልጣን ያስለቀቀው ወታደሩ ኃይል ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ያቋቋመ ሲሆን፣ ሕዝባዊ መንግሥት ለማቋቋም ለዜጎች ቃል ገብቶ ነበር። ይሁን እንጂ የነገሩ ሁኔታ ያላማራቸው የማኅብረሰብ ክፍሎች በተለይም የተማረው ክፍል የሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም ጥያቄ በማንሣት ለጊዜው ለተደራጀው መንግሥታዊ ኃይል ጎንታይ ሆነው ወጥተዋል። እነዚህ ወገኖች በሂደት ለሥልጣን የሚያሰልፍ የፓርቲ አደረጃጀት መፍጠር ቀጥለዋል። በምሕጻረ ቃል ኢሕአፓ፣ መኢሶን፣ ኢጭአት፣ ወዝሊግ፣ ማሌሪድ የተባሉ የግራ ክንፍ ፖለቲካን የሚከተሉ ኃይሎች ወጥተዋል። የደርግ ሰዎችም ይሄንን የአደረጃጀት ሰልፍ የሚገዳደር ሌላ የፖለቲካ ኃይል ለማደራጀት ተነሥተው አብዮታዊ ሰደድ የተባለ የመለዮ ለባሹ ጓዶች መታገያ ሆኖ ተመሥርቶ ነበር። በእርግጥ የተቋቋሙት ሁሉ ድርጅቶች /ከኢሕአፓ በስተቀር/ ራሳቸውን ፓርቲ ሳይሉ ንቅናቄ፣ ሊግ፣ ትግል፣ድርጅት፣ ሰደድ እያሉ ነበር።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በመጽሐፋቸው እንዳብራሩት ሕዝቡ ሳይነቃ መሪ ፓርቲ ማቋቋም አይቻልም የሚል እምነት የነበራቸው ብዙ ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ኃይሎች ግን በርዕዮተ ዓለም የግራ ክንፍ ፖለቲከኞች መሆናቸው ከመገዳደር፣ ከመገፋፋት አላዳናቸውም። ስለዚህ የነበረው ጥያቄ የሥልጣን ቅርምት መሆኑን ያመላክታል። ደርግ ለጊዜው ነገሮችን በመቻቻል የያዛቸው ቢመስልም ኢሕአፓ ወዲያውኑ የደርግ መንግሥት መራር ተቃዋሚ ሆኖ ወጣ። ወዝሊግ እና መኢሶን ግን የደርግ አባሪ፣ ተባባሪ ሆነው ተሰልፈው ነበር። በ1968 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ሕዝብን ለማጥቃትና ለማደረጃት ለሚደረገው ጥረት የፕሮግራሙ አስፈጻሚ አካል ሆኖ ጊዜያዊ ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽሕፈት ቤት ተቋቁሞ ሥራ ሲጀምር በተቋቋመው ኮሚሲዮን ውስጥ መኢሶን ሰብሳቢ እስከ መሆን ደርሶ ሌሎችንም በስፋት ያሳተፈ እንቅስቃሴ ተደርጎ ነበር። ነገሩ ሲጀመር አብዮቱ ዲሞክራሲያዊ መልክ የያዘ መስሎ እንዲታይና ሥልጣንን ሁሉም የሚጋራበት ሥርዓት የሚመጣ አስመስሎ ነበር።

ከኢሕአፓ በስተቀር ሌሎቹ የፖለቲካ ኃይሎች ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ አንድ ግንባር ቀደም ፓርቲ ሊመሠረት የሚችለው ሰፊውን ሕዝብና ተራማጅ ኃይሎችን በማንቃትና በማደረጃት ነው በሚል በ1969 የሚስማሙት ቡድኖች በጋራ ኢማሌድኅን በየካቲት 1969 አቋቋሙ። ይህ ኅብረት ፓርቲዎች በጋራ ለመሥራት ልምድ ያደረጉበት የመጀመሪያ ምዕራፍ ይመስላል። ይሁን እንጂ ይዞታው ከመጠራጠር ያልጸዳና፣ ከአደገኛ የሥልጣን ጥማት ያልራቀ ትብብር በመሆኑ ውጤት እንዳላመጣ ፕሮፌሰር ባሕሩ እንዲህ ይገልጹታል «ኢማሌድኅ እንደታሰበው የግንባር ቀደሙ ፓርቲ አዋላጅ መሆኑ ቀርቶ አባል ቡድኖቹ ለድርጅታዊ የበላይነት የሚፋለሙበት መድረክ ሆኖ አረፈው። በተለይ መኢሶን ያነሳ የነበረው የበላይነትና የመኰራራት ስሜት የሌሎቹን የተባበረ ጥላቻ አተረፈ»/ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ገጽ 259/ ።

እነዚህ ሁኔታዎች ሄደው ሄደው ዜጎች ሰላም የሚያገኙበት፣ ሀገር የምትረጋጋበት የሥልጣን ተሳትፎ ሥርዓት ማበጀት አልቻለም። በአንድ በኩል የኢሕአፓ ትግል እየከረረ መምጣትና የሽብር ድርጊቶች መስፋፋት፣ በሌሎቹ ድርጅቶችም መካከል የነበረው መጠራጠር አድጎ እስከ መጠፋፋት መደረሱ በመጨረሻ ደርግ ብቸኛው የሥልጣን ባለቤት ሆኖ ለዓመታት እንዲቆይ አድርጎታል። ስለዚህ ሥልጣንን አጋርቶ ሀገራዊ መንግሥትን የማጽናት አካሄድ ከሸፈ።

ደርግ ሥልጣኑን የሚገዳደሩ ብቻ ሳይሆን በኃይል ከሥልጣን ለማስወገድ የተነሡ በርካታ ኃይሎች ከበቡት። በመጨረሻም ኢህአዴግ ድል ቀንቶት አዲስ አበባ ሲገባ አብረውት ታግለው የመጡና ሰላማዊ ፖለቲካን እንመርጣለን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰባስበው ነበር።

ዶክተር የሺጥላ ወንድሜነህ ይሄንን ወቅት የተወሰነ ሥልጣን የማጋራት ጅምር የታየበት ነበር ይላሉ። ኢሕአዴግ በሚመራው በዚህ የሽግግር እንቅስቃሴ የታጠቁና ያልታጠቁ የፖለቲካ ኃይሎች ተወካዮችና ታዋቂ ግለሰቦችን ያቀፈ 87 ተሳታፊዎች የተሳተፉበት ምክር ቤት ተቋቁሞ ነበር። ከዚህም 32 ያህሉ ኢሕአዴግ ድርጅቶች የያዙት ሲሆኑ



**ተፎካካሪ ፓርቲዎች የተካተቱበት አዲሱ የአስፈጻሚዎች ቃለ መሓላ ሥነሥርዓት**

ከሌሎቹም ተሳታፊዎች በአመዛኙ ለኢሕአዴግ የማይጎረብጡ አካላት የያዙት ቦታ ነበር። ይህም እንደ ደርግ ሁሉ ለሽግግር ጊዜ እንዲያጅቡ ተፈልጎ የተጋበዙ ወይስ ኢሕአዴግ የምር በጊዜያዊው የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ልዩ ሐሳብ ያላቸውን ወገኖች ለማካተት ቁርጠኝነት ስለነበረው የሚለው የብዙዎች ጥያቄ ነበር።

ይህ ምክር ቤት ያልተመረጠውን ኢሕአዴግ የሚመራውን አስፈጻሚ ለመደገፍ ተቋቋመ። በዚህ ባልተመረጠና በጊዜያዊው መንግሥት ፕሬዚዳንት መለስና በጠቅላይ ሚኒስትሩ ታምራት ላይኔ የተመረጡ የካቢኔ አባላትን ሥራ ይደግፍ ነበር። በዚህ የታሪክ አጋጣሚ በተቋቋመው የፖለቲካ ድርጅት ተወካዮች፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ድርጅቶች በተወከሉበት ምክር ቤት ከነበረው የተለያዩ ወገኖች የሥልጣን ተሳትፎ በተጨማሪ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በአስፈጻሚው አካል ውስጥ ተካቶ ሥራዎችን እንዲመራ መሰየሙም የተለየ ሥልጣን የማጋራት ጅምር ነበር። ከኦነግ ዶክተር ዲማ ነገዎ በማስታወቂያ ሚኒስትርነት፣ አቶ ኢብሳ ጉተማ በትምህርት ሚኒስትርነት፣ አቶ አህመድ ሁሴን በንግድ ሚኒስቴርነት፣ አቶ ዘገየ አስፋው በግብርና ሚኒስትርነት እንዲሠሩ ተመደበው ነበር። በኋላም ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በትምህርት ሚኒስቴርንት፣ ሌሎችም ኢሕአፓ ከነበሩና ለኢሕአዴግ መራር ጥላቻ ካልነበራቸው ሰዎች ለአስፈጻሚነት የታጩ ነበሩ።

የተቋቋመ የሽግግር መንግሥት በጦርነቱ የተመሰቃቀሉ ነገሮችን የማስተካከልና ሕዝብን የማረጋጋት ሥራዎችን፣ የሕገ መንግሥት ማርቀቅ ሂደቶችን ሲመራ ቆይቷል። በዚህ የሥልጣን ማጋራት ተስፋ ተጥሎበት የነበረው አካሄድ ግን ዓመት እንኳን ሳይሞላው ኦነግ እንዲሰደድ በማድረግ ከሸፈ። ኦነግ እና ከሽግግር መንግሥት ምሥረታው ስምንት ወራት በኋላ የተቋቋመው መኢሕድ በሂደት በክልሎች ሊቋቋሙ ለታሰቡት ምክር ቤቶች ተሳትፎ ለማድረግ ለሚደረገው ምርጫ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ የገጠማቸው ወከባና ጥቃት ከሂደቱ ራሳቸውን እንዲያገሉ አስገድዶ ነበር። ስለዚህም ኢሕአዴግ ሥልጣን ለማጋራት አሳይቷል የተባለው አዝማሚያ ከጅምሩ ችግር አጋጥሞታል።

በኋላም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከጸደቀ በኋላ በተካሄዱ ምርጫዎች በፌዴራሉ ባለው የተወካዮች ምክር ቤት በሕግ አውጪነት በሕግ አስፈጻሚነት የሚገኙ የሥልጣን ቦታዎችን በማጋራት ረገድ የነበረው መንግሥት ጅምር እንጂ በጊዜው የሚያድግ ለውጦች አልታዩም። በተቻለ መጠን በተካሄዱ ተከታታይ ምርጫዎች በተወካዮች ምክር ቤት የሚሳተፉ በሕዝብ የተመረጡ በጣት የሚቆጠሩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ኃይሎች መሳተፍ ችለዋል። ሕግ አውጪው አንዱ የመንግሥት ሥልጣን ማጋሪያ በመሆኑ በዚህ ረገድ ከቀድሞው ሥርዓት በተሻለ ገጽታው ቢለወጥም ሥርዓቱ ለማስመሰል በሚደረግ የዲሞክራሲ ሂደት የተሞላ መሆኑን ራሱን አጋለጠ እንጂ ተስፋ አልሰጠም።

ዶክተር የሺጥላ ወንድሜነህ በኢትዮጵያ ሥልጣን የማጋራት ልምምዶች ጠፍተው ሳይሆን ለጊዜው ያለው የሥልጣን አጋሪው ዓላማ ምንድነው የሚለው ነው። የተጀመረው የማይቀጥለው፣ የበቀለው የማያድገው በዚያ ምክንያት መሆኑን ያስረዳሉ።

ኢሕአዴግም ከሕግ አውጪው በመለስ በአስፈጻሚው የመንግሥት አካል ከኢሕአዴግና አጋሮቹ ከሚላቸው በራሱ ካድሬዎች ከሚዘወሩ ድርጅቶች በቀር ሌሎች ዝር የማይሉበት መዋቅር ነበር። በሕግ አውጪው አካልም ቢሆን መደረግ ያለበት ነገር እየመነመነ ኢሕአዴግ መቶ በመቶ የምክር ቤት ወንበርን በመቆጣጠር ሥልጣኑን መያዙን ታይቷል።

ይህ ሁኔታ ግን ለሚመራው የመንግሥት አካልም ሆነ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ሆኖ አልተገኘም። ኢሕአዴግ ከራሱ መዋቅር፣ ከሕዝቡ፣ ከተቃዋሚዎች የፖለቲካ ትግል ለውጥ እንዲያመጣ ሲገደድ በ2010 በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ የሚመራ አዲስ አካሄድ ለመከተል ቃል ገብቶ ሥልጣን ቀጠለ። ኢሕአዴግ በዚህ የለውጥ ሂደት የግንባሩ ቁልፍ ሚና የነበረው ሕወሓት ተጽእኖውን እንዲያጣ በማድረግ ድርጅታዊ ውሕደት ለመፍጠርና ሀገራዊ አንድነትን ለማጠናከር መርኅ አድርጎ ሲነሣ ሕወሓት ከድርጅቱ አኩርፎ ለመውጣትና ዋነኛው የዐቢይ አህመድ መግሥት ተገዳዳሪ ሆኖ ተገኘ። በፌደራል መንግሥቱ ሥልጣን ይዘው የነበሩ የሕወሓት ሰዎችና የምክር ቤት አባላትም በዐመጽ ኃላፊነታቸውን ለቀው መቀሌ ገብተዋል።

በዐቢይ አሕምድ የሚመራው መንግሥት ሌሎች ተቃዋሚዎችን ሥልጣን የማጋራት ፍላጎት እንዳለው ማሳየት የጀመረው ከ2013 ምርጫ በፊት ነበር። በተለያዩ ከፍተኛ የመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ በዳይሬክተርነትና በቦርድ አባልነት በማሳተፍ ልምምዱን ጀምሯል። ለዚህም የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር ሊቀ መንበር ዶክተር አረጋዊ በርሔ፣ ለሶሕዴፓ ሊቀመንበር ለፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ ለአብኑ ጣሂር ሞሐመድ፣ ለኦፌኮ ሊቀመንበር ለፕሮፌሰር መረራ ጉዲና ተሰጥቷቸው የነበረውን ኃላፊነት በምሳሌነት ማንሣት ይቻላል።

ይሁን እንጂ ሕወሓት ከዚያም አልፎ ሥርዓት አልበኝነትንና ሕገ ወጥነትን ግጭትን በማስፋፋት በመቀጠሉ ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር ወደ ጦርነት ገባ። መንግሥት በ2013 ዓ.ም ሀገራዊ ምርጫ አድርጎም መንግሥት በማቋቋም ሥልጣንን አጋርቶ መንግሥት የማደላደል ፍላጎት እንዳለው ፍንጭ ሰጠ። ይህም ተስፋ ሲደረግ የነበረ አካሄድ ስለሆነ ሕዝቡ በተስፋ ወደ ምርጫው ተሳተፈ። የምርጫው ውጤት ውሕዱ ፓርቲ ብልጽግና የተሸነፈበት ሲሆን በተቻለ መጠን በምርጫው የተሳተፉ ተቃዋሚዎችም የምርጫውን ውጤት በአዎንታ የተቀበሉበት የተሻለ ምዕራፍ ሆኖ ተገኘ። በምክር ቤት አሸንፈው የገቡ ተቃዋሚዎች በሕግ አውጪው ለመሳተፍ መቻላቸው አዲስ ምዕራፍ ባይሆንም ከምርጫ በኋላ ግን አዲሱ መንግሥት የፖለቲካ ተፎካካሪዎቹን በአስፈጻሚነት በየደረጃው ለማሳተፍ የሰጠውን ተስፋ እውን ማድረግ ችሏል።

በዚህም በፌዴራል መንግሥት የአስፈጻሚ የመንግሥት መዋቅር ኦነግ፣ ኢዜማ እና አብንን ለማሳታፍ ያደረገውን ጥረት ተስፋ ሰጪ ሆኖ ተመዝግቧል። ይንንም በየክልሉ ምክር ቤቶች ከገቡ ተቃዋሚዎች በተጨማሪ በክልል መንግሥታትም አስፈጻሚ ሆነው ተቃዋሚዎች እንዲገቡ በሁሉም ምርጫ በተደረገባቸው ክልሎች ጥረት መደረጉ ነገሩን አዲስ ምዕራፍ የሚያሰኘው ነበር። በኦሮሚያ ክልል ኦነግ፣ በአማራ ክልል አዴሃንና አብን፣ በአዲስ አበባ አስተዳዳር ኢዜማና አብን፣ በሶማሌ ክልል ኦብነግ፣ በደቡብ ክልል ኢዜማ፣ ሶሕዴፓ፣ ነእፓ በቤኒሻንጉልም በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሥልጣን ለማጋራት ተችሏል።

ከዚህ አንጻር አስተያየት እንዲሰጡ የጋበዝናቸው ዶክተር የሺጥላ ነገሩን በአዎንታ አይተውት ዘላቂነት ላለው አካሄድና አዲስ ምዕራፍነቱን ለማጽናት የፖለቲካ ምኅዳሩን የምር ማስፋቱ የተሻለ ይሆናል ብለው ይመክራሉ።

እኛም በመንግሥትና በተፎካካሪዎች መካከል ያለው መቀራረብ በብሔራዊ እርቀ ሰላም የበለጠ እንደሚያብብ ተስፋ እያደረግን የተጀመረው ይቀጥል እንላለን።



# የሳይበር ምኅዳሩን ያለ ስጋትና ያለ ጥቃት!

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

የሳይበር ምኅዳር ሁሉን አቀፍ መሆን ለዓለማችን ብሎም ሀገራችን አያሌ መልካም እድሎችን ይዞ የመምጣቱን ያህል በተቃራኒው ደግሞ ለሀገራት ሉዓላዊነትና ለሕዝቦች ደኅንነት የስጋት ምንጭ እየሆነ እንደመጣ ይነገራል። ዓለም በሳይበር ምኅዳር ምክንያት አንድ እየሆነችበት ባለችበት በዚህ ጊዜ ቴክኖሎጂው የሚሰጠውን መልካም እድል ተጠቅሞ የስጋት ምንጮችን ለመቀነስ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ግንዛቤን መያዝ እንደሚያሻ የሳይበር ደኅንነት ባለሙያዎች አጥብቀው ያሳስባሉ። ባለፈው ጥቅምት ወር በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ18ተኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ "የሳይበር ደኅንነት የጋራ ኃላፊነት ነው! እንወቅ! እንጠንቀቅ!" በሚል መሪ ቃል የተከበረው የሳይበር ደኅንነት ዋነኛ ዓላማም ግንዛቤን ማስረጽ ነበር። ለመሆኑ "የሳይበር ምኅዳር" ምን ማለት ነው? የሳይበር ጥቃት ሲባልስ? ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ የሚባሉት የተለዩ አካላትስ እነማን ናቸው? ግለሰቦችስ የሳይበር ጥቃት ሊደርስባቸው ይችላል ወይ? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን በማንሣት ዘመን መጽሔት በኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ የሳይበር ደኅንነት ንቃተ ኅሊናና ባሕል ግንባታ ማዕከል ኃላፊ አቶ ቢኒያም ማስረሻን፣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ቡድን መሪ እንዲሁም በጅማ ዩኒቨርሲቲ፣ የሲስኮ ኔትዎርኪንግ አካዳሚ በመምህርነትና በሥራ አስኪያጅነት እያገለገሉ የሚገኙትን አቶ ዘሪሁን በፍቃዱንና በሳይበር ደኅንነት ላይ የሚሠራው የThe Secured Tech company መሥራችና ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን ኢንጂነር ፋሪስ ሙሀመድን አነጋግራለች።

**ከ40 ከመቶ እስከ 60 ከመቶ ያህሉ የሳይበር ጥቃት በኢሜይል አማካኝነት የሚደርስ ነው። የኢሜይል የይለፍ ቃልን ጠንካራ በማድረግና ኢሜይላችንን ከተጠቀምን በኋላ በመዝጋት ወይም ክፍት ባለመተው ራሳችንን ከሳይበር ጥቃት መጠበቅ እንችላለን**



**አቶ ቢኒያም ማስረሻ**

## የሳይበር ምኅዳር ምንነት

ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱም ባለሙያዎች እንደሚስማሙበት የሳይበር ምኅዳር የሰው ልጅ የእርስ በእርስ ግንኙነቱ ማደግ፣ የመሠረተ ልማት መስፋፋትና የመረጃ ፍላጎት የፈጠረው ቴክኖሎጂ ሲሆን፣ ብዙዎች እንደሚያስቡት ትላልቅ ተቋማትን ብቻ የሚመለከት ሳይሆን ማንኛውም ከስልክ ጀምሮ ወደ ኢንተርኔት ሥርዓት የሚገባውን እያንዳንዱን ግለሰብ ጭምር የሚመለከት ነው። ማንኛውም በኮምፒውተር ወይም በኢንተርኔት የሚያልፍ እንቅስቃሴ በሳይበር ምኅዳር ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ ሲሆን፣ ኮምፒውተሮችን፣ ስልኮችንና ሌሎች መሰል መሣሪያዎችን የሚያገናኘው ምናባዊ ድር (web) ደግሞ ሳይበር (Cyber) ይሰኛል።

## የሳይበር ደኅንነት መጠበቂያ መሠረቶች

እንደ አቶ ቢኒያም ገለጻ የመረጃ ምስጢራዊነት፣ ምሉዕነትና ተደራሽነት ሦስቱ የሳይበር ደኅንነት መጠበቂያ መሠረታዊ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ የመረጃ ምስጢራዊነት (Confidentiality) የምንለው አንድን መረጃ ሊያየው ከሚገባው ሰው ውጪ እንዳያየው መጠበቅ ወይም ከሌላ ፈቃድ ከሌለው አካል ወይም በርባሪ መሰወርን የሚገልጽ ነው። ይህም ምስጢራዊውን መረጃ ሌላ ያልተፈቀደለት አካል እንዳያገኘውና ለሌላ ዓላማም እንዳይጠቀምበት ያደርገዋል። የመረጃ ምሉዕነት (Integrity) ስንል ደግሞ መረጃዎች ፈቃድ በሌላቸው አካላት እጅ ሳይገቡ፣ ይዘታቸው ሳይጨምር ሳይቀንስ፣ ትክክለኛነታቸውን እንደጠበቁ እንዲገኙ ማድረግ ሲሆን፣ በሦስተኛነት የተቀመጠው የመረጃ ተደራሽነት (Availability) አንድ መረጃ ወይም ዳታ በተፈለገበት ፍጥነትና ሰዓት ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ በመፍጠር ይገለጻል።

## የሳይበር ጥቃት ምንነት

አቶ ዘሪሁን "የሳይበር ጥቃትን" ከዘራፊ ሽፍታ ጋር በማነጻጸር በምሳሌ ያስረዳሉ፡- እርሳቸው እንዳሉት፣ በድሮ ጊዜ አንድ ሰው ከአንድ ቦታ ተነስቶ ወደ ሌላ ቦታ ሲንቀሳቀስ ዘራፊ ሽፍቶች ያስቸግሩት፤ የያዘውንም ይዘርፉት እንደነበረ ሁሉ፤ በኢንተርኔት አማካኝነት ካለንበት ቦታ ተነሥተን እንደ ጎግል፣ ዩቲዩብና ጂሜይል ያሉ በርካታ ሰርቨሮችን ለማግኘት በምንሞክርበት ወይም የሳይበር ምኅዳር ውስጥ በምንገባበት ጊዜ በመሐል በመረጃ ጠላፊዎች መረጃ ሊሰረቅብን ይችላል። ከመረጃ ስርቆትም ባለፈ ጠላፊዎቹ የእኛን መልእክት ይዘት በመቀየር፣ እኛን መስለው የመረጃ ልውውጡን ለተለያየ ዓላማ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ይህ ዓይነቱን ስርቆት የሳይበር ጥቃት ብለን እንጠራዋለን።

የሳይበር ጥቃት ሲባል የሳይበር ወንጀለኞች የግለሰብን ወይም የድርጅትን ኮምፒውተር ወይም ሲስተም ሰብረው በመግባት የድርጅቱን፣ የባለድርሻ አካላትን አሊያም የሠራተኛውን የግል መረጃ ለተለያዩ ጥቅሞች የሚያውሉበት ሁኔታ ነው ያሉን ደግሞ ኢንጂነር ፋሪስ ናቸው። ኢንጂነሩ የሳይበር ጥቃት ብዙ ዓይነት መልክ እንዳለውም ይናገራሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ ትላልቅ ተቋማትን ዒላማ አድርጎ ገንዘብ ለመስረቅ ወይም የፖለቲካ አጀንዳን ለማስፈጸምና የፖለቲካ ኪሳራን ለማድረስ ዓላማ ከሚደረገው የሳይበር ጥቃት በተጨማሪ፣ ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የፌስ ቡክ አድራሻው የይለፍ ቃል ተሰርቆ ከእርሱ እውቅና ውጪ በፌስቡክ ገጹ ላይ ፎቶ አሊያም ሌላ እርሱን የማይመለከት መልእክት ቢለጠፍበት ይህንን የሳይበር ጥቃት እንለዋለን።

ሌላው ከሳይበር ጥቃት ጋር ተያያዥነት ያለው "የሳይበር ትንኮሳ" ሲሆን፣ ይህም አብዛኛውን ጊዜ አብረው የቆዩ ባልና ሚስት ወይም ፍቅረኛሞች ሲጣሉ በተለይም በሴቷ ስም የፌስ ቡክ አካውንት በመክፈት በሰላሙ ጊዜ እጃቸው የገቡ ፎቶዎችን



አቶ ዘሪሁን በፍቃዱ

በመጠቀም የሚደረግ ስም የማጥፋትና የማበላሸት ተግባር ወይም እንደ ፌስቡክ፣ ቲክቶክ፣ ዋትስአፕ፣ ኢንስታግራምና ቴሌግራም የመሳሰሉ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን በመጠቀም አሉታዊና ሐሰተኛ ይዘት ያላቸውን መልእክቶች መላክና መለጠፍ፣ የግልና ሚስጥራዊ መረጃዎችን ሆን ብሎ የሰዎችን ሥነ ልቡና ለመጉዳት ማሰራጨት ነው።

## ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ አካላትና አጋላጭ ሁኔታዎች

አቶ ቢኒያም እንዳሉት፣ ሌሎች ባለሙያዎችም እንደሚጋሩት ማንኛውም ወደ ሳይበር ምኅዳሩ የገባ ግለሰብም ሆነ ተቋም ወይም ከስልክ ጀምሮ ኮምፒውተርና ውስብስብ የሆኑ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም ሁሉ በየትኛውም ጊዜ ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ነው። አንዳንድ ሰው ከግንዛቤ ማነስ እኔ ምንም የምደብቀው ነገር የለም፤ የማዘዋውረው ገንዘብ የለኝም ምን አስጨነቀኝ በሚል የተሳሳተ አረዳድ ይዘናጋል፤ ነገር ግን፣ ግለሰቦችም ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ከመሆናቸውም ባሻገር በእነርሱ የይለፍ ቃል፣ የስልክና የኮምፒውተር አጠቃቀም ግዴለሽነት የተነሣ የሳይበር አጥቂዎች የእነዚህን ሰዎች መሣሪያና አድራሻ፣ ሌሎች ሰዎችንና ኮምፒውተሮችን ለማጥቃት መግቢያ አድርገው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ፤ ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪ ለወንጀለኞች መሣሪያ ከመሆንም ባሻገር የሕግ ተጠያቂነትንም ያስከትላል።

መንግሥታት፣ የቴክኖሎጂ ድርጅቶች፣ የተደራጁ ወንጀለኞችና ከተቋም የተሰናበቱና በሥራ ላይ ያሉ የውስጥ ሠራተኞች ዋነኞቹ የሳይበር ጥቃት ፈጻሚዎች ሲሆኑ፣ ከእነዚህ አብዛኛው የሳይበር ጥቃት ገንዘብን ዒላማ ባደረጉ የተደራጁ የሳይበር ጥቃት አድራሾች የሚደርስ ነው። እነዚህ ቡድኖች ለዓላማቸው መሳካት ገንዘብ ላይ የሚሠሩ ተቋማትንና የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚ ግለሰቦችን ዒላማ ያደርጋሉ። የአንድ ተቋም የቀደሙም ይሁን የውስጥ ሠራተኞች ለበቀል ዓላማ የተቋሙን መረጃ አሳልፎ በመስጠት ለሳይበር ጥቃት ሊያጋልጡ ይችላሉ። ሌላውና በዓለም ሀገራት በብዛት የሚፈፀመው የሳይበር ጥቃት የፖለቲካ ዓላማ ያለው ነው። ይህ በአብዛኛው በጦርነት ወቅት የሚፈፀምና እንደ ቴሌ፣ መብራት ኃይል፣ የትራንስፖርት አውታር ያሉ ቁልፍ የሀገራት መሠረተ ልማቶች ላይ የሚያነጣጥር የሳይበር ጥቃት ነው።

ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የአንድን ሀገር የፋጠራ ሥራ ለመሰለልና ለመስረቅ፣ የኮምፒውተር ሥርዓትን ለማውደም፣ የፖለቲካ አቋምንና ሃይማኖታዊ አስተሳሰቦችን ለማራመድና የአንድ ተቋም የኮምፒውተር ኔትወርክ እንዳይሠራ በማድረግ እገሌን አጠቃን ለማለት ወይም ዝና ማትረፍን ዓላማ በማድረግ የሳይበር ጥቃት ሊፈፀም እንደሚችልም አቶ ቢንያም ይገልጻሉ።

አቶ ዘሪሁን በበኩላቸው፣ ተንቀሳቃሽ ስልካችን ወይም ኮምፒውተራችን በእጃችን ላይ እያለ እኛ በማናውቀው ሁኔታ ሌሎች በሚጠቀሙበት ጊዜ ሳይበር ጥቃት ደረሰ ማለት ነው ይላሉ። በርካታ ለሳይበር ጥቃት አጋላጭ ሁኔታዎች ቢኖሩም በቀላሉ ሊያጋልጡን የሚችሉ ናቸው ያሏቸውንም በዝርዝር ያስረዳሉ። ቀዳሚውና ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው ያሉት ለሳይበር ጥቃት አጋላጭ ሁኔታ ስለ ሳይበር ምኅዳር በቂ ግንዛቤን አለመያዝ ሲሆን፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ከስልካችንና ኮምፒውተሮቻችን ጀምሮ በኢንተርኔት አማካኝነት ለምንጠቀማቸውን እንደ ኢሜይል፣ ፌስቡክ፣ ኢንስታግራም የመሳሰሉ ማኅበራዊ መገናኛዎች ጠንካራ የይለፍ ቃል አለመጠቀምና እነዚህን መገናኛዎች በስልኮቻችን አሊያም በኮምፒውተሮቻችን ከፍተን ከተጠቀምን በኋላ በተገቢ ሁኔታ ዘግተን አለመውጣት፣ ለሳይበር አጥቂዎች ቀላልና ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርላቸው ያስረዳሉ።

ኢንጂነር ፋሪስ ደግሞ፣ የሚከተሉትን በመተግበር ራስን ብሎም ሌሎችን ከሳይበር ጥቃት መከላከል እንደሚቻል ያስረዳሉ። ልክ እንደ አቶ ዘሪሁን ሁሉ ሳይበርን በተመለከተ ተገቢ ግንዛቤን መያዝ ቀዳሚው ተግባር እንደሆነ የተናገሩት ኢንጂነሩ ጠንካራ የይለፍ ቃሎችን በመጠቀም እንዲሁም የይለፍ ቃልን በየጊዜው በመቀያየር፣ ደኅንነታቸው ያልተጠበቁ ድረ ገፆችን ከመንብኘት በመቆጠብ፣ አድራሻቸው በግልጽ ከማይታወቁ አካውንቶች የሚላኩ ሊንኮችና አባሪዎችን (Attachments) ባለመክፈትና የምንጠቀማቸውን ሶፍትዌሮች በየጊዜው በማደስ (update) የምንጠቀማቸውን የመገናኛ መሣሪያዎች ከስርቆት በመጠበቅ ራስን ከሳይበር ጥቃት መከላከል እንደሚቻል ያስገነዝባሉ።

## የሳይበር ጥቃት ጉዳት እስከምን ይደርሳል?

በአሜሪካ በዓመት 60 ከመቶ የሚሆኑ ትንንሽ ድርጅቶች በሳይበር ወንጀል ምክንያት ከሥራ ውጪ እንደሚሆኑ የጠቀሱት ኢንጂነር ፋሪስ አንድ ድርጅት ላይ የሳይበር ጥቃት ደረሰ ቢባል ደንበኞች በድርጅቱ ላይ ያላቸው እምነት እንዲወርድ ከማድረግ ጀምሮ ከፍተኛ የፋይናንስ ኪሳራን እንደሚያስከትል ይናገራሉ።

ባለሙያዎቹ እንደሚሉት፣ ሀገርን የሚያንቀሳቅሱ ከፍተኛ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚፈፀም ጥቃት የሚያስከትለው ሀገራዊ ቀውስ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ለምሳሌ በሀገራችን ቁልፍ የሚባሉ ባንክ፣ ቴሌና የኃይል ማመንጫ ዓይነት መሠረተ ልማቶች ላይ ጥቃት ቢደርስ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ቀውስን ያስከትላሉ፤ ቀውሱ የሁሉንም ቤት የሚያንኳኳም ጭምር ይሆናል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢራን ኒውክሊየር ማበልጸጊያ የኮምፒውተር መረጃ ላይ እስራኤል ያደረሰችውን የሳይበር ጥቃት በማሳያነት የጠቀሱት አቶ ቢኒያም፣ የኮምፒውተር መረጃዎችን አጥፊ ሶፍትዌር በፍላሽ ላይ በማዘጋጀት ብቻ፣ ፍላሹ ኮምፒውተር ላይ በሚሰካበት ጊዜ የኮምፒውተሮችን መረጃ እንዲያጠፋ በማድረግ ኢራን ለ10 ዓመታት ስትሠራበት የነበረውን የኒውክሊየር ማበልፀጊያ ሥርዓት እንዳጠፋና 10 ዓመታትን ወደኋላ እንደመለሳት ይናገራሉ። አያይዘውም ጥቃቱ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የሥነ ልቡና ኪሳራን እንዳስከተለ ያክላሉ። በቅርቡም በአሜሪካ የነዳጅ አቅርቦት ሰንሰለታቸው ላይ የደረሰውን የሳይበር ጥቃት ያነሡት አቶ ቢኒያም፣ የኮምፒውተሮች እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ እንዲቆም በማድረግ በተፈጸመው በዚህ የሳይበር ጥቃት፣ በአሜሪካ በሁሉም ከተሞች የነዳጅ አቅርቦትን እንዲቆም እንዳደረገውና ለሁለት ቀናት ያህል የሀገሪቷን ኢኮኖሚ እንደረበሸው ያወሳሉ።

በሀገራችንም በርካታ የመሠረተ ልማት ተቋማቶቻችን ላይ የተቃጡ የሳይበር ጥቃቶች ዓላማቸውን አሳክተው ቢሆንና ባይከሸፉ ኖሮ ከፍተኛ ሀገራዊ ቀውሶችን ሊያስከትሉብን እንደነበርም አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።

አቶ ዘሪሁንም፣ የሳይበር ጥቃት በቀላሉ አንድ የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚ ወደ ሚፈልገው ሰው ሊልከው የነበረው ገንዘብ በመሐል ተጠልፎ ወደ ሌላ ሰው የባንክ አካውንት እንዲገባ ቢደረግበትና ቢሰረቅ፤ ላኪው እንደላከ ነው የሚያውቀው፣ ተቀባዩ ጋር ግን የደረሰ ነገር የለም፤ እንዲህ ዓይነት የሳይበር ጥቃት ሊያስከትል ከሚችለው

ወደ ገፅ 20 ዞሯል

ከገፅ 17 የዞረ



ኢንጂነር ፋሪስ ሙሀመድ

ግለሰባዊና ማኅበራዊ ቀውስ ጀምሮ በሀገር ደረጃ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱ ተቋማት ቢጠቁ የአንድ ሀገርን ህልውና ጥያቄ ውስጥ የሚከት ቀውስን ሊያስከትሉ ይችላሉ ብለዋል። አያይዘውም አሁን አሁን በሀገራት መካከል ያለው ጦርነት እንደ ድሮው በመሣሪያና በጦር ሳይሆን በአብዛኛው በሳይበር አማካኝነት በመሆኑ በሀገር ደረጃ ራሳችንን ከሳይበር ጦርነት (Ciber War) ለመጠበቅ ወይም ለመመከት ዝግጁ መሆን እንደሚገባን ያሳስባሉ።

## የሳይበር ደኅንነትን እንዴት መጠበቅ እንችላለን?

የሳይበር ደኅንነትን መጠበቅ የአንድ ሰው ወይም የአንድ ድርጅት ብቻ ኃላፊነት እንዳልሆነ ኢንጂነር ፋሪስ አስምረው ይናገራሉ። አያይዘውም፣ ምግብ በየዕለቱ እንደምንበላው ሁሉ ወይም ዛሬ ስለበላን ለነገ አያስፈልገንም እንደማንለው ሁሉ የሳይበር ምኅዳር መልኩ በየዕለቱ የሚቀያየር እንደመሆኑ ደኅንነቱን የመጠበቁም ተግባር አንዴ ተሠርቶ የሚያልቅ ሳይሆን በየዕለቱ የሚከወን ሂደት መሆኑን ማወቅ ያሻል ይላሉ።

እንደ ኢንጂነር ፋሪስ ገለጻ፣ ከስልክ ጀምሮ የተለያዩ የኢንተርኔት እንቅስቃሴዎችን የሚያደርግ ግለሰብም ሆነ ተቋም ራሱን ከሳይበር ጥቃት ለመከላከል ጥልቅ የሆነ መከላከያ ያስፈልገዋል። ይህ ማለት፣ አንድ ሰው የቤቱን ደኅንነት ለመጠበቅ የግቢ አጥር፣ የግቢውን በር፣ የመኖሪያ ቤቱን በር ይዘጋል። ከዚያ መስኮቱን ይዘጋል፤ የተለየ እቃ ያለበት ክፍልም ካለ በደንብ አድርጎ ይዘጋል። ልክ እንዲሁ ተገቢና ሊገመቱ የማይችሉ የይለፍ ቃላትን በመጠቀም መረጃዎቻችንን በሚገባ በመደበቅ፣ ለስርቆትና ለጠለፋ እንዳይመቹ በማድረግ የሳይበር ጥቃትን መከላከልና ማክሸፍ ይቻላል።

ሁሉም ሰው ራሱን ከየትኛውም ወንጀል ለመከላከል ጥረት እንደሚያደርገው ወይም ራሳችንን ከበሽታ ለመጠበቅ የምናደርጋቸው መከላከያዎች እንዳሉ ሁሉ፣ ሁሉም አካል ራሱን ከሳይበር ጥቃት መከላከል አለበት ያሉን ደግሞ አቶ ቢኒያም ናቸው። ከ40 ከመቶ እስከ 60 ከመቶ ያህሉ የሳይበር ጥቃት በኢሜይል አማካኝነት የሚደርስ እንደሆነ የሚናገሩት አቶ ቢኒያም በቀላሉ የኢሜይል የይለፍ ቃልን ጠንካራ በማድረግና ኢሜይላችንን ከተጠቀምን በኋላ በመዝጋት ወይም ክፍት ባለመተው ራሳችንን ከሳይበር ጥቃት መጠበቅ እንደምንችል ያስረዳሉ። እንደ እርሳቸው ሀሳብ፣ ሁሉም ሰው ግንዛቤው ኖሮት ራሱን ካልጠበቀ፣ ተቋማትም በከፍተኛ ንቃት ኃላፊነት ወስደው ራሳቸውን ካልጠበቁ የሳይበር ጥቃትን በአንድ ተቋም ብቻ መከላከል በፍጹም የሚቻል አይደለም። ለዚህ ደግሞ ተቋማት የየራሳቸው የሳይበር ጥቃትን መከላከል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ሊታጠቁ፣ ለሠራተኞቻቸውም ምን ዓይነት የሳይበር ጥቃት ሊደርስና እንዴት ያለ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ወቅቱን የጠበቀ ስልጠና ሊሰጡ ይገባል። በዚህ መልኩ ተቋማትም ግለሰቦችም የየራሳቸውን ኃላፊነት ሲወጡ የሳይበር ደኅንነት የጋራ ኃላፊነት ይሆናል።

የሳይበር ወንጀለኞች አንድ ቀዳዳ ብቻ ነው የሚያስፈልጋቸው ያሉት ኢንጂነር ፋሪስ፣ እኛ ግን ራሳችንን ከሳይበር ወንጀለኞች ለመጠበቅ መቶ ያህሉን ቀዳዳ መሸፈን እንደሚጠበቅብን ያሳስባሉ። ሁሉም የኢንተርኔትና የማኅበራዊ መገናኛዎችን የሚጠቀም ሰው ለአንዱ አካውንት የተጠቀመውን የይለፍ ቃል ለሌላው ባለመጠቀም፤ ለምሳሌ ለፌስ ቡክ የተጠቀመውን የይለፍ ቃል ለኢሜይል አካውንቱና ለሌሎችም ባለመጠቀም በትንሹ ራሱን ከሳይበር ጥቃት መከላከል እንደሚችል ያስረዳሉ።

አቶ ዘሪሁንም ልክ እንደ ሌሎቹ ባለሙያዎች ሁሉ ትናንሽ መዘናጋቶች ትላልቅ ችግሮችን ይዘው ሊመጡ ይችላሉና ምንጊዜም ንቁ ልንሆን እንደሚገባ ያስገነዝባሉ። ራሳችንን ከሳይበር ጥቃት ስንጠብቅ ከራሳችን አልፈን ሌሎችን ብሎም የተቋማችንን መረጃና ገጽ ከሳይበር ጥቃት እየጠበቅን እንደሆነም ልናውቅ ይገባልም ብለዋል።

## የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ምን እያከናወነ ነው?

ኤጀንሲው የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራትን የማስተባበርና ንቃተ ኅሊናንም የማጎልበት ኃላፊነት አለበት ያሉት አቶ ቢኒያም፣ ከዚህ አንጻር ሰፊ ሥራ እየሠራ እንዳለም ይናገራሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ ኤጀንሲው ከሳይበር ጥቃት አኳያ ተቋማት ያሉበትን ቁመና እንዲያውቁት፣ እንዴትስ መከላከል አለባቸው የሚለውንም እንዲረዱት ሥልጠና የመስጠት፣ ቴክኖሎጂን የማካተት፣ የአሠራር ሥርዓት ፖሊሲዎችን የማማከርና ጥቃት ከደረሰም በኋላ በ933 የጥሪ ማዕከል በሚደርሰው ሪፖርት መሠረት ጥቃት በተሰነዘረበት ሥፍራ በመገኘት ችግሩን በፍጥነት ችግሩን የመፍታት ወይም ጥቃቱን የመመከት ሥራ ይሠራል። ይህንን የሚሠሩ ሠራተኞችም ቅዳሜና እሑድን ጨምሮ 24 ሰዓት ዝግጁ ሆነው ይጠባበቃሉ። ይህ ለሁሉም አካል የሚሰጥ አገልግሎት ቢሆንም በይበልጥ ጥቃት ቢደርስባቸው ሀገር ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ቁልፍ የመሠረተ ልማት ተቋማት ላይ ዓይኑን ሳይነቅል ይሠራል።

ኤጀንሲው 2008 ላይ 214 ያህል በትላልቅ ተቋማት ላይ የተቃጡ ጥቃቶችን ማክሸፍ ችሏል፣ በ2009፣ 479 ጥቃቶችን መከላከል ችሏል፣ ይህም የጥቃቱ መጠን በአንድ ዓመት ውስጥ ከእጥፍ በላይ እንደጨመረ ያሳያል፤ በ2010 ዓ.ም 576 ጥቃቶችን ማክሸፍ ችሏል፤ ይህ ማለት ወደ 35 ከመቶ ያህል ጭማሪ አለው። በ2011 ዓ.ም 791 ጥቃቶች ከሽፈዋል፣ በ2012 ዓ.ም 1087 ጥቃቶችን ማክሸፍ ችሏል። ባሳለፍነው 2013 ዓ.ም ደግሞ 2800 እንደ ሀገር ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ጥቃቶችን ማክሸፍ ችሏል። ይህ መረጃ የሳይበር ጥቃት በምን ያህል ፍጥነት እየጨመረ እንደመጣ ያሳየናል ያሉት አቶ ቢኒያም ጥቃቱ እየበዛ የመምጣቱን ያህል የተቋማችን ጥቃትን የመመከት ዝግጁነትና አቅምም በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል ብለዋል።

በአጠቃላይ ሲታይ ለሀገር እድገትና ብልጽግና የሳይበሩ ምኅዳር መስፋፋት ወሳኝ ሆኖ ሳለ በብዙ ፈተናዎች የተከበበ መሆኑ የታወቀ ነው። በመሆኑም ጥቅሙን በተረዳንበት ልክ ከሚመጡበት ማሰናከያዎች የመጠበቅ ተግባሩም ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ መረዳት አስፈላጊ ይሆናል።

በዚህ ዓምድ ስር የሚስተናገዱ ጽሑፎች የፀሐፊውን አመለካከት እንጂ የዝግጅት ክፍሉን አቋም አይወክሉም።

# የምሁሩ ሚና ምን ቢሆን ይሻላል?



**ደሳለኝ ሥዩም**

ችግራችን ሥረ ብዙ ነው። ዓይነተ ብዙ ነው። ክቡድ ነው። ሸክሙ ከዚህ አንስተን እዚህ እናደርሰዋለን የማንለውን ዝክንትል የያዘ ነው። ያለብን በአንድ አዳር ልናስተካክለው፣ ልንበጣጥሰው፣ ልናፈራርሰው የማንችለው የተውተበተበ የችግር ድር ነው። ችግርን ከሥር ከሥሩ አልፈታንምና በችግር ላይ ችግር ተደርቦ ዛሬ የተሸከምነውን እዳ አሸከመን።

የትምህርት ሥርዓት ሲንሸዋረር ዝም ስላልን አሁን የተማረውና ወረቀት የገዛው በአንድ ገበታ መቀመጥ ጀመሩ። የተማረ የሚባለው አልፎ አልፎ ብቻ ድምፁን ለማሰማት ሲሞክር ወረቀት የገዛው ደግሞ ከሚዲያ ባለሙያዊነት እስከ ሕግና ፖሊሲ አውጪነት ተቆልሎ የምናይበት አጋጣሚ ሰፍቷል። (ወረቀት የገዛችሁ ባለሙያዎችና ባለሥልጣኖች ስሕተታችሁን በውስጥ እመኑልኝ፣ ቀለል ያለ ቅጣት ይጠብቃችኋል፤ ያለበለዚያ በአደባባይ ትዋረዳላችሁ የሚለው የመንግሥት ጥሪ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን አይደል?)

መከላከያው የአንድ መንደር ካድሬዎች መፈንጫ ሲሆን፣ ምንም ባለማድረጋችን አርበኛ እና ባንዳ በአንድ ዩኒፎርም ሥር ሆነው ለማየት ተገደድን። ድፍን አንድ ዓመት ያስቆጠረውና በዘመናት መኻል አንዴ ብቅ የሚለው ታላቁ ክህደት በመከላከያ ላይ መፈጸሙ አሁን ድረስ ላልተጠናቀቀው ጦርነት ትልቁ ሰበብ ነው። ይሄም እንደ ላይኛው ነው፤ የአርበኞች ቤት መሆን ሲገባው የባንዶች ቤት ጭምር ሆኖ እንዲሠራ ሲደረግ ዘረኞች ቤቱን ለመበከል የሄዱበትን ርቀት አውቀን ያሰማነው ድምፅ አናሳ መሆኑ ነበር። (አሁንም እንኳ ስለመንቃታችን ማንም እርግጠኛ መሆን የሚችል አይመስለም። በዚህ ጦርነት እንኳ የውጭ ሀገር ምስሎች ተቀናብረው በጠላቶች ሲለቀቁ ‹አዎ ልክ ነው› ብለን አምነን የምንሸበረውን ያህል የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የሚሰጡትን ትዕዛዝ፣ የሚያስመዘግቡትን ድልና የሚሰጡትን መረጃ ላለመቀበል ሲያቅለሸልሸን እንታያለን)።

በተመደብንበት ቦታ ሥርተን ከማሥራት ይልቅ የውሸት ሪፖርት ሲጻፍ እያየን፣ እንድንጽፍ ስንገደድም አንዳች ነገር ትንፍሽ ባለማለታችን ዛሬ ያልተመረተ ተመረተ ሲባል፣ የተገደለ አልተገደለም ሲባል፣ የታሠረ አልታሠረም ሲባል ብቻ ሳይሆን የተሳደበ ክብር ተሰጥቶት ፓርላማ ሲገባ አየን። ከዚህም ከፍቷል፤ የመንግሥትና ዜጋ ጉዳዮች ብቻ ሳይሆኑ የባልና ሚስት፣ የወላጅና ልጅ፣ የልጅና የወላጅ ጉዳዮቻችን ሳይቀሩ በሐሰተኛ ሪፖርቶች እንዲስተካከሉልን የምንፈልግ እየበዛን ነው። ልጅ ያልዋለበትን ሪፖርት ሲያደርግ ወላጆችም እርስ በእርስ ያልዋሉበትን ሪፖርት ያደርጋሉ።

> **የማናውቀውን ነገር ተምረነዋል ብለን እናወራለን። ጠንካራ ጠያቂ ሲገጥመን ‹ያው ወረቀቱን ልያዘው ብዬ› እንላለን። ተምረን ሥራ አጣን ብለን ለማማረር የሚቀድመን የለም**

ሕክምና፣ ምሕንድስና፣ የሕግ ትምህርት ሁሉ እንደ ካድሬነት በዘመቻ (በኮታ) ሲሰጡ ትንፍሽ ባለማለታችን ወይም የረባ ለውጥ ለማምጣት ባለመሥራታችን ዛሬ ለነፍሰ ጡር የሬሳ ማድረቂያ መርፌ የሚወጋ ሐኪም፣ ጋሪ ሲሄድበት የሚያረገርግ ድልድይ የሚሠራ መሐንዲስ፣ ፍትሕን ሳይሆን ፓርቲን የሚያስቀድም ዐቃቢ ሕግን የምናይበት ሁነት ተፈጠረ። ዛሬ እላይ ያሉ መሪዎቻችን ምንም ያህል ቅን ቢሆኑ፣ ምንም ያህል ሀገር ለማበልጸግ ሕዝብ ለማሻገር ቢነሱ ረጅም ዘመናትን ደንብሸን ያደነበሸናቸው የበታች አመራሮች ያለጉቦ እንዳያገለግሉ፣ ያለመታያ ፍትሕን እንዳይደርሱባት፣ ያለ ጉርሻ የተሻለ አገልግሎትን እንዳይሰጡ አድርገን ሠርተናቸዋል። ሐኪም ቤት ሄደን ብንሰለፍ፣ ፍርድ ቤት ሄደን ብንገተር፣ መብታችን የሆነውን የቀበሌ መታወቂያ ለማግኘት ስድስት ወራት ብንንቃቃ፣ ትናንት አዲስ ብለን ያገኘነው ቤት ዛሬ ውስጡ ፍሳሽ በፍሳሽ ቢሆን የእኛው ውጤት!

መጠበቅን ስንለማመድ ተው እንጂ የሚለን መካሪ አጥተን የማይመጣውን ስንጠብቅ፣ ለማናወቀው ሰፊ ጊዜያችንን ስንሰዋ ጠባቂነት እያሳሳቀ ወስዶን ጫት ቤት እና አረቂ ቤት ከመረን። አሁን መውጣት ተሳነን፣ ሀገር ተወሮ ከመቆጨትና ከመነሳት ይልቅ ቁጭ ብሎ ጫት ያበሰበሰው ጥርስን እያንገለጠጡ ወሬ መሰለቅ ድርሻችን ሲሆን አየን። ሲርበን መንግሥት እንዲደርስልን እንመኛለን እንጅ ወጣ ብለን የወንዝ ዳርቻ ላይ ድንች ወይ ጎመን ስለመዝራት አናስብም። የትምህርት ውጤታችን ቢያሽቆለቁል ጾታችንን፣ ጎሳችንን አለዚያም ሃይማኖታችንን መታያ አድርገን መንግሥት ‹‹አስተያየት›› እንዲያደርግልን እንጠይቃለን፣ እንጠብቃለን። ጥንቃቄ አድርጉ ስንባል አሻፈረኝ ብለን ባመጣነው በሽታ ስንጎሳቆል መንግሥት ካልደረሰልን ብለን እንጠይቃለን፤ እንጠብቃለን።

ይህ ሁሉ ሲደራረብ የመጣ ችግራችን ነው። አንድ ቀን ብቻ የተሠራ አይደለም። ለዘመናት የተሻገረ ነው። ተነስተን ለውጥ ከማምጣት ይልቅ የሆነ አካል መጥቶ ለውጡን እንዲሰጠን እንጠብቃለን፤ ሀሞታችን ፈስሷል። ዐሥር አምራቾች ያመረቱትን አንድ ሺህ ሆነን እንደልለዋን። በድለላ ስም እናጭበረብራለን፤ ባዬ በሰማ ጥቅም እንጠይቃለን። ያገኘነውን ዲናር ይዘን አረቂ ቤት እንወተፋለን፤ ደግሞ ነገ በስልክ ስለምንደልለው እናስባለን እንጅ ተነስተን ስለማምረት አናስብም።

የማናውቀውን ነገር ተምረነዋል ብለን እናወራለን። ጠንካራ ጠያቂ ሲገጥመን ‹ያው ወረቀቱን ልያዘው ብዬ› እንላለን። ተምረን ሥራ አጣን ብለን ለማማረር የሚቀድመን የለም። በዓመት ውስጥ ሦስት ቀን ክፍል ውስጥ ገብተን ሠላሳ ቀን ለጓኞቻችን ‹‹አቴንዳንስ›› አስፈርመን፣ ዐሥራ ዘጠኝ የተገለበጠ ወረቀት ላይ ስማችንን አስጽፈን፣ ከስልካችን ላይ መልስ ገልብጠን ‹‹ተፈትነን› ‹የተማርን› እኛ ሥራ ጠፋ፣ መንግሥት ሥራ አልሰጠንም እንነሳ እና መንገድ እንዝጋ፣ ፌስ ቡክ ላይ ጫጫታ እናስነሳ ብለን እንዶልታለን። አዎ ችግራችን ብዙ ነው።

የዕለት ከዕለት ሕይወታችንን በቅጡ ለመምራት እንቸገራለን። የማናውቃው ቢበዛም ቅሉ ‹‹አውቀዋለሁ›› ብለን ለመናገር የድፍረት ችግር የለብንም። ያለንበትን ሕይወት ማሸነፍ አቅቶን ብንንገዳገድም ቅሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ለመተቸት የሞራል ችግር የለብንም። ትዳራችንን በቅጡ ለማቆም የተቸገርን፣ በብድር ሰቆቃ ውስጥ ተዘፍቀን ሱሳችንን ለማስታገስ የምንታትር ሆነን የከንቲባዋን ‹‹የአፈጻጸም ብቃት›› አበሻቅጦ ለመጣል እምብዛም አናቅማማም። በብድር ላይ ብድር ከምረን፣ ፊታችንን በብዙ ኮፍያና መነጽር ደብቀን ከሰፈር እየወጣን፣ አምሽተን እየገባን ራሳችንን የምንሸውድ እዳው ካልተከፈለው የአረቄ ብርጭቆ ፊት ለፊት ቁጭ ብለን የኢትዮጵያን ፖለቲካ በፌስ ቡክ ልንመራ እንታትራለን።

ስለዚህ ሁሉ መፍትሔ እንሻለን። እንደምንገምተው የመፍትሔ ምንጩ ደግሞ ‹‹ምሁሩ›› ነው። ይህ ምሁር የሚባለው በትልቁ ምስል ሀገርን ከድህነት፣ ሕዝብን ከችጋር ከርሃብና ከሰቀቀን አላቅቆ በምድር ላይ ላሉ ፍጡራን ሁሉ ጤናን፣ ሰላምን እና ረፍትን ማጎናጸፍ ትልቁ አደራው ነው ይባላል። በትንሹ ምስል ደግሞ አለባበሱ፣ አነጋገሩ፣ አኗኗርና የህይወት ዘይቤው ማራኪነት እና አርአያነት ያለው ለሚያየው፣ ለሚያዳምጠው እና ለሚያነበው መረጋጋትን የሚሰጥ ለተቸገሩም መፍትሔ የሚያመላክት እንዲሆን ይጠበቃል።

ምሁሩ ባደጉት ሀገራት ምን ሚና ነበረው?

**ምሁር ሲባል የራሱን የኢኮኖሚ ጎን፣ የፖለቲካ ጎን፣ የሃይማኖት ጎን ወዘተ... እያሰበ ኪሱን ለመሙላት ሳይሆን የሚሠራው በጭንቅ እና በማኅበረሰብ መሃል በንጽሕና ቆሞ ማኅበራዊ ጣጣዎችን የሚፋለም ነው**

ምሁሩ ለበለጸጉት ማኅበረሰቦች ምን አድርጎላቸው ነበር? ምሁሩ ዴሞክራሲያዊ በሆኑ አስተሳሰቦች ላይ ምን እጅ ነበረው? ምሁሩ በሚያድግ ሀገር ውስጥ ምን ቦታ አለው? ምሁሩ ፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ በነገሠበት ሥፍራ ምን ያድርግ? ምሁሩ ርሃብ፣ ግጭት፣ ተንኮል በነገሠበት ማኅበረሰብ ውስጥስ ምን ሚና ይኑረው?

አስቀድሞ ምሁርነትን ከገለልተኝነት፣ ከወገንተኝነት እና ከአሳቢነት አንጻር እንየው። ለመሆኑ ምሁር መቆም ያለበት ከሥርዓት ጋር ወይስ ከእውነት ጋር? አስቅድሞ ይሄንን መመለስ አንገብጋቢ ይሆናል። ነገር ግን ‹‹ምሁር›› ከሚለው ቃል ጋር ብዙዎቻችን ቤተኛ የሆንን ይምሰለን እንጅ በትርጉም ደረጃ ቃሉ የጠለቀ በመሆኑ የምናውቀው እየመሰለን የማናውቀው መሆናችንን የምንገነዘበው ቆይተን ነው።

ምሁር የሆነውን እና ያልሆነውን ለመለየት የምንቸገረውም ለዚህ ይመስለኛል። ለምሁሩ የሚገባውን ሁሉ ምሁር ለመሰለው ስንሰጥ የምንታይበትም ሰበብ ከዚህ ብዙ የሚርቅ አይደለም። የምሁር ትርጓሜ ምን ያህል አሻሚ እንደሆነ እንደሚከተለው እንይ። ከፍ ሲል እንዳልኩት አንደኛው መገለጫ ‹‹ገለልተኝነት›› ነው ብለን እንነሳ። ነገር ግን ገለልተኝነት ደግሞ በራሱ አሻሚ ነው።

የቃሉ አሻሚነት የሚመነጨው ሰው ከመሆን ላይ ነው። እያንዳንዱ ሰው በሚኖርበት ማኅበረሰብ ውስጥ ጥቅም፣ ፍላጎት፣ ምኞት፣ ያለው በመሆኑ እነዚህን ሁሉ ለማሟላት ደግሞ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች ይኖሩታል። በእነዚህ ተግባቦቶች (መስተጋብሮች) የሚኖር ሰው ደግሞ በሙያህ ገለልተኛ ሁን ቢባል ምን ያህል ያስኬዳል ነው?

እነዚህ እውነታዎች እንዳሉ ሆነው ዋልዶ ኤመርሰን ደግሞ ምሁር ለምሁርነቱ መቆም አለበት ይላል። ይህን ለማለት ያነሳሳውን ምክንያት ሲገልጽ ኤመርሰን ምሁርነት ማለት የኅብረተሰቡ የማስተዋያ ዓይን፣ ማገናዘቢያ ጭንቅላት ማውጠንጠኛ አዕምሮ በመሆኑ ነው። ምሁሩ የበራለትን ሁሉ እያበራ ማኅበራዊ ጠንቆችን ከማኅበረሰቡ ይመነጥራል።

ስለዚህ ምሁር ሲባል የራሱን የኢኮኖሚ ጎን፣ የፖለቲካ ጎን፣ የሃይማኖት ጎን ወዘተ... እያሰበ ኪሱን ለመሙላት ሳይሆን የሚሠራው በጭንቅ እና በማኅበረሰብ መሃል በንጽሕና ቆሞ ማኅበራዊ ጣጣዎችን የሚፋለም ነው።

የራልፍ ዋልዶ ኤመርሰን እይታ በእርግጥ ለብቻው የሚቆም አይደለም፤ ይልቁንም ጥበብን ለጥበብ (Art for art sake) ከሚለው የቆየ ፍልስፍና ጋር የሚጃመል እንጅ።

ይሄም ይባል እንጅ ኅብረተሰብ ደግሞ ለምሁር የተመቸ ሜዳ ሆኖ የተገኘበት የዓለም ታሪክ ብዙም የለም። የእውቀትን አባቶች በሄምሎይክ መርዝ የገደለ፣ ፊዚዝቶችን በስቅላት የቀጣ፣ ፈላስፎችን በእሳት ያቃጠለ፣ አሳቢዎችን በመጥረቢያ ያስፈለጠ መሆኑ የዚህ ዓለም አንድ ብቻ ሳይሆን ሁነኛ ታሪክ ሆኖ የተመዘገበ ሀቅ ነው።

ምሁሩ ፊት ለፊት ካለው ጨለማ ባሻገር ያለውን ብርሃን ስለሚያይ ጨለማ ላይ ብቻ በሚያተኩረው ማኅበረሰብ ጥርጣሬ ውስጥ ይወድቃል። ይፈራል። ይነቀፋል። ‹‹መናፍቅ›› ተብሎ ይታማል። ይወገራልም። ይህም የሚሆነው ኅብረተሰቡ ጨካኝ ስለሆነ ሳይሆን ይልቁንም የትኛውም ማኅበረሰብ ጨለማ አፍቃሪ እና ለብርሃን ፍቅር እምብዛም ያልታደለ መንጋ ስለሚበዛበት ነው።

ስለዚህም ነው ምሁርነት ከገለልተኝነት እና ከወገንተኝነት ተጻራሪ አቋሞች መሃል ገብቶ የሚፈተተው። በአንድ በኩል ወገንተኛ ይሁን የሚባለው ምሁር በሌላ በኩል ገለልተኛ ይሁን ይባላል። ለሙያው በመታመን ኅብረተሰብ ይጠቅማል ብሎ ሐሳብ የሚያመነጭ ሰው ያ፤ ሐሳብ ተግባራዊ እንዳይሆን ከሚያግዱት አሠራሮችና እውነቶች ገለልተኛ ሊሆን የሚችለውን ያህል ያንን ሃሳብ ወደ መሬት አውርዶ ማኅበራዊ ጠንቆችን ሊያስወግድልኝ ይችላል ብሎ ከሚያስበው አሠራር ወይም ተቋም ጋር ወገንተኛ ቢሆን የሚለው አዎንታዊ መከራከሪያ የመሆኑን ያህል ‹ለሆዱ› የወገነ ወይም የተገለለ እንደሆነ ልክ በመንደርደሪያችን እንዳልነው ዘመናትን የሚሻገር የትውልድ ፈተና ሲመጣ መጋፈጥ ያልቻለ ሐሳዊ ‹ምሁር› ተብሎ የሚመዘገብ ይሆናል።

ስለዚህ ሐሳብ ገለልተኛም ወገንተኛ አይደለም፣ እንዲያው ብቻ ሐሳብ ነው በሚል ነጥብ መስማማት የቻልን እንደሆነ ይሄንን ጽሑፍ እንቀጥል። ነገር ግን እንዲህም ማለት ይገባናል። ምሁሩ ሐሳብ የሚያመነጭ ከሆነ ከአንድ ኅብረተሰብ ክፍል ጋር መወገን የለበትም፤ መወገን ያለበት ይልቁንም ከእውነት ጋር ነው። ይሄ ምን ማለት ነው? አንድ ሥፍራ የተወለደ ኢትዮጵያዊ የአካባቢውን ወይም በዘመኑ አጠራር የጎሳውን ችግር አጠና እንበል፣ ከዚያ ለመፍታት ተነሳ። ይህን ችግር ለመፍታት ሲል ግን ከዚህ ጎሳ ጋር ወግኖ የቆመ እንደሆነ ምሁር አይሆንም፤ ከእውነት ጋር አልቆመምና። እውነትስ እዚህ ሥፍራ የቷ ናት? ያ፣ ጎሳ ብቻውን የሚቆም ሊሆን አይችልም፤ በአንድ ሰው ብቻም ሊሰጠው የሚችለው መፍትሔ አይኖርም። ቢያንስ ‹ጎሳ› መሆኑ እንዲታወቅለት ሌሎች ጎሳዎች መኖር እና መቀጠል አለባቸው። ስለዚህ ይህ ‹‹ምሁር›› የሚያመጣው የመፍትሔ ሐሳብ አካታች እንጅ ወገንተኝነት ያለበት ከሆነ የከሸፈ ይሆናል።

ደግሞ ሌላ ምሳሌ ማንሳት እንችላለን፤ በገዥው ፓርቲ እና በተቃዋሚዎቹ መካከል የጦፈ ክርክር የተነሳ እንዲሆን በሕዝብ እንዲወደድ ብሎ ገዥውን የተቃወመ እንደሆነ ወይም ኪሴ እንዲደልብ ብሎ ገዥውን የደገፈ እንደሆነ ምሁርነቱ እምብዛም ነው፤ አድሏዊ ይሆናል። ከዚህ ‹‹ምሁር›› የሚጠበቀው በሁለት ተሟጋቾች መሃል መቆም ያለባትን ‹እውነት› በአመክንዮ ተንትኖ ማሳየት እና ይህችን እውነት ሁሉም እንዲያውቋት ማድረግ ነው።

ይሄንን ማድረግ የቻለ እንደሆነ እውነት ሁሌም ከፊት እንድትቆም ማድረግ ይችላል። ተከራካሪዎች ጊዜያዊያን ናቸው። ዛሬ የተከራከሩቱ ብቻ ሳይሆን በአፈሙዝ የተፈላለጉቱ ነገን አይኖሩም፤ ሁለቱም ያልፋሉ። ሀገር፣ ሕዝብና እውነት ግን ይቀጥላሉ። ያችን እውነት የሚያስተዋውቃት፣ የሚጠብቃትና የሚያስጠብቃት ደግሞ ምሁሩ ነው።

ስለዚህ ምሁራን ከእውነት ጋር እንዲቆሙ ሁሌም ይጠየቃሉ። ከእውነት ጋር መቆም የቻሉት ምሁራን አናሳ መሆናቸው ሀገራችን ላለፉት ዘመናት የመጣችበትን አቀበትና ቁልቁለት አልፋ አሁን ያለችበት ዘርፈ ብዙ ችግር ውስጥ የወደቀች እንድትሆን በር ከፍቷል። በዚህ ችግር አስተዋጽኦ ካላቸው ወገኖች ምሁሩ ስሙ ይነሳል። ምክንያቱም ከእውነት ጋር አልቆመም ነበርና፤ ቆሞማ ቢሆን ኖሮ አሁን ያለንበት ዘርፈ ብዙ ችግር ቢያንስ ዘርፈ ጥቂት በሆነ ነበር።

አሁንም ምሁሩ ብዙ ድርሻ ያለበት ይመስላል። ለሚዲያ ፍጆታ ብቻ ቃላትን የሚያሰማምር ከሆነ ሐሳዊ ምሁር መሆኑን ይወቀው። ትናንት ከገዥው ፓርቲ ጋር እንደቆመው ሁሉ ዛሬም ከገዥው ፓርቲ ጎን ለለጠፍ ያለም እንደሆነ ሐሳዊ ምሁር ነው። ትናንት ገንዘብ ለማካማበት ዝምታን በመምረጡ ሀገር እንዲህ ያለ ችግር ውስጥ መዘፈቋን ሳይረዳ ዛሬም ባለህበት ሂድን የሚያዜም ካለ ከምሁርነት ይልቅ ለድንቁርና የቀረበ መሆኑን ይወቀው። በዚህና በዚያ ብሎ ሀገርን ማስቀደም ድርሻው መሆኑን ያልተረዳ እንደሆነ አሁንም ‹‹ምሁርነት›› ከችግር ያልተላቀቀ ነው!

በዚህ ዓምድ ስር የሚስተናገዱ ጽሑፎች የፀሐፊውን አመለካከት እንጂ የዝግጅት ክፍሉን አቋም አይወክሉም።

# አመል ያወጣል ከመሐል

**ቶኩማ ሮባ**

የልጅነት የጨዋታ ጊዜዬን ሳስታውስ ከማይረሱኝ አጋጣሚዎች አንዱ የጨሎ ረብሻ ነው። ከጨሎ በዕድሜ በወራት ብንበላለጥ ነው። እኩያ ነን። ያለአቅሙ ራሱን እንደ አለቃ የሚቆጥር አምባገነን ሕፃን ነበር።

ጨሎ ከቤቱ ወጥቶ ከመንደሩ ልጆችጋ ለመጫወት ከፍተኛ ጉጉት አለው። እናቱ እቴማንቺ ወጥቶ፣ ተጣልቶ ይመጣል ብለው ስለሚሰጉ ከቤት ባይወጣባቸው ይመርጣሉ። የጨሎ ጩኸት ግን የእትዬ እቴምአንቺን አንጀት ስለሚረብሸው «በል ሄደህ» ተጫወት ይሉታል። ገና ከአፋቸው «ሂድ» የሚለውን ቃል ሳይጨርሱ የቤታቸውን የቆርቆሮ በር በርግዶ ይወጣል። የከፈተውን በር ሳይዘጋ እየጮኸ ከእኛ መሐል ይገባል።

ጨሎ እንደመጣ ሁሉንም የናፈቀ ሆኖ ይቀርባል። እየተጠመጠመ ይስመናል። ትንሽ ቆይቶ ግን ጨሎ የጭቃ ጅራፉን:- ክፉ አመሉን ያወጣል። ከጓደኞቹ መካከል ያማረ መጫወቻ የያዘውን አይቶ «ስጠኝ!» ብሎ ይጮኻል፤ ለመስጠት ያልፈቀደ ሕፃን ካለ በሕፃኑ ጨሎ ጩኸትና ጉልበት መጫወቻውን ይጥላል። የፈረደበት ሕፃን ያለቅሳል። ጨሎ ከጓደኞቹ የሚቀማው መጫወቻ ሁሉ የራሱ እንደሆነ ያህል ያስባል። የወሰደውን መጫወቻ እንዴት እንደሚጫወትበት እንኳን አያውቅም፤ የተነጠቀው ሕፃን መነጠቁን ለምዶ ተረጋግቶ ይጫወታል። ጨሎ ግን የሌሎችን መጫወቻ እስኪወላልቅ ይጫወትበታል። ወዲያውኑ ይሰለቸዋል። ከዚያ የሌላ ሕፃን መጫወቻ ያያል እንደለመደው ነጥቆ ይጫወታል።

ሌላ የደመቀ ጨዋታ የጀመርን ሕፃናት ካለን ጨሎ እራሱን የጨዋታው አንበል ካልሆነ ደስታ አይሰጠውም። መሃል ይገባል። የውድድር ጨዋታ ከሆነ ያፍራል። የታፈረባቸው ጓደኞቹ ከእርሱ ሸሽተን ሌላ ጨዋታ ስንጀመር ተከትሎ ይመጣል። ጓደኞቻችን የጨሎ አምባገነንነት ሲበዛባቸው በቡድን ሆነው ይደበድቡታል። መትተውት መጮኽ ሲጀምር ወደየቤታቸው ይበተናሉ።

የጨሎ ጩኸት ሀገሩን ያዳርሳል። በተለይ ከቆሰለ ከደማ መንደሩ ሁሉ በጩኸቱ ይታወካል። የፈረደባቸው እናቱ እትዬ እቴማንቺ አርጩማያቸውን ይዘው ይወጣሉ። መሐል ገብቶ ሲያጫውት የነበረ ልጃቸው ብቻውን ሜዳ ላይ ሲጮኽ ያገኙታል። ጨሎ የመቱትን ሁሉ በስም እየጠራ ለእናቱ ይከሳል። እቴማንቺ በየቤቱ እየመጡ አርጩሜያቸውን አሹለው ለየሕፃኑ ወላጅ ሁሉ አቤቱታ ያቀርባሉ። አንዳንዶቹ ወላጆች የጨሎን ክፉ አመል ስለሚያውቁ ከእቴማንቺ ጋር እሰጥ አገባ ይገባሉ። እትዬ እቴማንቺ በየቀኑ በየሳምንቱ የልጅ አቤቱታ ማሰማት ሰለቻቸው። ስለዚህም ጨሎ በጮኸ ቁጥር አርጩሜያቸውን እርሱው ላይ ይጨርሱ ጀምር። በየቀኑ ከመንደሩ ሕፃን ሁሉጋ አምበል ሆኖ ሲጫወት የነበረው ጨሎ በወር እንኳን ከቤት መውጣት ተከልክሎ ከቤቱ በራፍ ላይ ቆሞ የደመቀ የእኛን ጨዋታ ለማየት ይገደድ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ታዲያ አያቴ ጨሎን ከመጫወት ተከልክሎ ከቤታቸው የቆርቆሮ በር አጠገብ ቆሞ በርቀት ስሞቻችን ሲጣራ ሲያዩ «አዬ አመል ያወጣል ከመሐል አሉ» ብለው ይተርቱበታል።

ዛሬ አድጌ፣ ጎልምሼ የአያቴን አባባል የሰማሁበት ጊዜ ወደኋላ ረጅም ቢሆንም አባባሉን ትርጉም ፍጹም የተረዳሁበት ጊዜ ወደ ኋላ አጭር ነው። «ዕድሜ ለሕወሓት» በጣም ነው የገባኝ። በ1960- እስከ 1970ዎቹ ዳር ዳሩን ሲል የነበረው የሕወሓት አንጋች ፖለቲካ «ዕድሜ ለደርግ» መዝረክርክ እያለ ኦነግና ኢሕአዴንን አጃቢ አድርጎ መሐሉን ሲቆጣጠር «በሆታ ግባ በእልልታ» ያሉት ባልንጀሬዎቹ ኦነግና ኢህዴን ለአመሉ ብፅዕና ለተግባሩ ቅድስና ጥርጣሬ አልነበራቸውም። በፖለቲካው ጨዋታ አብረውት ሊጫወቱ ተሰይመው ነበር።

ሕወሓት በ1983 ዓ.ም ግንቦት ወር አራት ኪሎ ሲደርስ ንጉሥም ጳጳስም ሆኖ ብፁዕ መባሉን ቀጠለ፤ የምርም የመሃሉን ጨዋታ ተጫዋችም መሪም ሆኖ የአዲስ ዘመን ብሥራት ነጋሪ ሆነ። ኢሕዴን አሕዴድ፣ ብአዴን፣ ደኢህዴን እየሆነ በሕወሓት ሲሸነሸን እንደተወለደ እንዳደገ አራት ኪሎ የደረሰውን ሕወሓትን ግን የሸነሸነው አልነበረም። እርሱ በልክና በወሰናቸው አጃቢዎቹን ሲያሰማራ እርሱ መሃል ሆኖ አንጋሽና ቀዳሽም ነበር። ቦታ ቦታ ይዘው ዳር ዳሩን እንዲጫወቱ የተደረጉት የግንባሩ ድርጅቶች የግንባራቸውን ማእከል የሕወሓትን ፊሽካ ሳይሰሙ ምንም እንቅስቃሴ የሚያደርጉ አልነበሩም።

ሕወሓት የበለጠ መሃሉን የሚያስይዘው ሌላ ተጨማሪ አጃቢ ከባቢ ለማሰለፍ አሁንም አላረፈም። እርሱ የመሃሉ መሐል ሆኖ «አጋር» የተባሉ የበዪ ተመልካች ኢትዮጵያውያንን እርሱን የከበበው ንብርብር ቅርፊት አደረጋቸው። የብጽእና ውሃ ልክ አድርጎ ራሱን በማሳሰብ ሌሎቹንም «ያመነ ይድናል» ብለው እንዲሰለፉ አደረጋቸው።

ኦነግ በተቻለ መጠን መሃሉን መጋራት ይፈልግ ነበር። የሕወሓት ትከሻ ሰፊ ስለነበር ኦነግ ተጋፍቶ መሃል መግባት አልሆነለትም። በተሰጠው መስመር ተወስኖ በሕወሓት ሜዳ መጫወቱን ቀጠለ። ያቺንም በሕወሓት የተወሰነችለትን መጫወቻ እንደ ልቡ ሊጫወትባት እንዳልቻለ የተረዳው ኦነግ የሕወሓትን አመል መጠርጠር ያዘ፤ «ብፁዕ» ሲለው የነበረው ሕወሓት የቀበሮ ባህታዊ ሆነበት። አልያዝ፣ አልጨበጥ አለው። የኦነግ ምኞትና ትልም እንደጉም እየበነነ የሕወሓትን መሃልነት የተቀበለው ኦህዴድ ወደዳር አሽንቀጥሮ ሲያወጣው ከመሃል ብቻ ሳይሆን ከጨዋታ ውጪ ለመሆን ተገደደ። በዚህ ጊዜ ግን በዳይ ሆኖ የተሳለው ኦነግ ነበር። «ተከዳሁ፣ ሕግ ተጣሰ፣ ታመጸብኝ» ያለው ሕወሓት ኢሕአዴግ ነበር። ነገሩ «አንቺው ታመጪው አንቺው ታሮጪው» ሆኖ በትዝብት ታለፈ።

የመሃል ዳኛውም፣ የመስመር ዳኛውም ሕወሓት በሆነበት ጨዋታ ኦነግ መሐል የሚገባበትን አዲስ የጨዋታ ሜዳ በኃይል ለመፍጠር የሚቆፍረው መሬት ፍሊጋ በየጫካው ተሰገሰገ።

ሕወሓት በከፍተኛ የማስመሰል ጨዋታ እንዲህ መሃል መሃሉን ራሱን አደላድሎ ቢያስቀምጥም በአዲስ ዐውድ ውስጥ አዲስ አመል መያዝ ግን አልሆነለትም። በምርጫም ይሁን በቅርጫ መሃሉን የመያዝ ፍላጎት አላቸው የሚላቸውን ሁሉ በየተራ እየዘረረ ዓመታትን ተሻገረ። ሕወሓትን ከመሃል የሚያስወጣ የመሰለውን የሃይማኖት ወገን፣ የንግድ ድርጅት፣ የፖለቲካ ኃይል፣ ታዋቂ ሰው ሁሉ ተራግጦ ሰበረ። ተደላደለ። ነገር ግን ክፉ አመል አለበትና የሰበረውን ያደቃል፤ በሞተው ላይ ይተኩሳል። የወደቀውን ይረግጣል፤ ስደተኛውን ያድናል።

ሕወሓት ግን መደላደልን አያውቅም «ድመት መነኩሳ አመሏን አትረሳ» እየሆነበት አሙቀው አድምቀው እያጨበጨቡ መሃል የሚያስጨፍሩትን አጃቢዎቹን መራገጥ ቀጠለ። ፈረስ የሚጋልብበትን የምኞት ኮርቻውን ኢሕአዴግን መዘንጠል ቀጠለ፤ ፈጥና የምትጋለብ ፈረሱን ሀገራቱን በሰከንድ በደቂቃ በእሾሕ አለንጋው መዠለጥ ቀጠለ። ወይ አመል!

በአለንጋው አቆሰላት፤ ጌጧን ሁሉ አረገፈው፤ መንገዷን ሁሉ አስጠፋት፤ አስበረገጋት፤ ከዕለት ዕለት አከሳት፤ አቅም አነሳት።

ስለዚህም ዳር ዳር ሆነው የሚያጫውቱት የኢሕአዴግ ክንፎችና አጋሮች ትከሻቸው ደማ ቆሰለ ሕወሓትን ሊሸከሙት አልቻሉም። ተባብረው ከመሃል ጨዋታ ማስወጣት ፈለጉ፣ አለሙ፣ አቀዱ፣ ተራመዱ፣ ደረሱ፤ ችለውም ዳር አወጡት።

ሕወሓት ግን «የፈሲታ ተቆጢታ» ሆነ። «በጥላቻ፣ በዘረኝነት የተፈጸመብኝ መገፋት ነው» አለ። ጩኸቱን አቀለጠው። ጓደኛዬ ጨሎ ከመሃል ጨዋታው ሲወጣ እናቱን እትዬ እቴማንቺን ይጠራ እንደነበር ሕወሓትም መሃል መልሰው ሊያስገቡት ይችላሉ ያላቸውን የፌዴራሊስት ኃይሎች ማሰባሰብ ቢሞክርም የእነርሱ አርጩሜ አባልና አጋሮቹን ተሰብስበው እንዲያጫውቱት ሊያደርግ አልቻለም።

ስለዚህም ሕወሓት በአባልና አጋሮቹ ላይ ድንጋይ መወርወር መፈንከትና ማቁሰል ጀመረ። ዜጎች አፈናቃይ፣ የግጭት ምንጭ፣ የሁከት ጠማቂ፣ የቀጠናው አሸባሪ ለመሆን ወሰነ። ጨሎው ሕወሓት ራሱ ባጠፋው ሌሎችን መክሰስ ቀጠለ። ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል ተተረተበት።

ጨሎው ሕወሓት ድንጋይ ውርወራና ጩኸቱ ሲበዛ የሀገሩ ዜጎች ሁሉ ተባብረው ዘመቱበት። መቁሰልና መድማት ጀመረ። ክንዳቸውን መቋቋም አልቻለም። ሮጦ እየጮኸ ከዋሻው ገባ። ጩኸቱን ቀጠለ። ሲ.ኤን.ኤን፣ ሮይተርስ፣ ቢቢሲ..... የዚህ ጩኸት አስተጋቢዎች ናቸው።

የልጃቸውን አመል ያላወቁት እትዬ እቴማንቺ ልጃቸውን ከመቅጣት ከማረም ይልቅ የመንደሩን ሕፃናት ሁሉ እንደሚከሱት የሕወሓት የክፋት ሐሳብ ወላጆች ምዕራባውያን ሕወሓት ለምን ተነካ ብለው ክስና አቤቱታቸውን አቅልጠውታል። የማዕቀብ አርጩሜ ይዘው የኢትዮጵያ ሰዎችን ያስፈራራሉ። ይህ ግን ሕወሓትን ወደ መሃል ሊመልስ አልቻለም፤ አይችልምም።

ሕወሓትን ከመሃል ያስወጣው፤ ዳርም የጣለው፣ የኢትዮጵያውያን ጭፍን ጥላቻ አይደለም። ዘረኝነትም አይደለም። አድልዎም አይደለም። የጨቋኝነት ፍላጎትም አይደለም። ይሄ ሁሉ አመል የሕወሓት እና የጀሌዎቹ እንጂ የሌሎች ኢትዮጵያውያን አይደልም። ከመሃል ያስወጣውም ይሄው የዘረኝነት፣ የጨቋኝነት፣ የአድልዎ፣ የሌብነትና የጥላቻ አመል ነው። ክፉ አመል ነው። ክፉ አመል እንኳን ከማሃል ከዳርም ለመቆም አያበቃም። አመል ያወጣል ከመሐል።

# አካል ጉዳተኞችን እኩል ተጠቃሚ ያላደረገው የትምህርት ስርዓት

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

“ልዩ ፍላጎት ሥርዓተ ትምህርት” ከሌሎች ተማሪዎች የተለየ ትኩረትና ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች የሚሰጥ ትምህርት ነው። በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የአእምሮ እድገት ውስንነትና የአእምሮ እድገት መዛባት ያጋጠማቸው፣ አይነ ስውራን፣ መስማት የተሳናቸውና ማንኛውም ዓይነት የአካል ጉዳት ያላቸው እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆችና ከእነርሱ በተለየ፣ የመማር ወይም የሚሰጣቸውን ትምህርት የመቀበል ችግር ያለባቸውና የተለየ ተሰጥዖ ያላቸው አሊያም ትምህርት በመቀበል አቅማቸው ከሌላው ተማሪ የፈጠኑ ተማሪዎች ይካተታሉ። በሀገራችን በተለይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልክ እንደ ጉዳት አልባው ተማሪ በትምህርት ገበታ ላይ ለመገኘት ከፍተኛ ተግዳሮት ይገጥማቸዋል፤ ለተማሪዎቹ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢ ካለመፈጠሩና አስፈላጊ መሳሪያዎችም ካለመሟላታቸው የተነሳ፤ በበርካታ ትምህርት ቤቶች ዘንድ እነዚህን ተማሪዎች ተቀብሎ የማስተማር ፍላጎትም አናሳ በመሆኑ ሳቢያ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት በተገቢ እድሜያቸው ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር እኩል በትምህርት ገበታ ላይ ለመገኘት ይቸገራሉ፤ ይህ ችግር በንጽጽር ከመዲናችን አዲስ አበባ ወጣ ባሉ ከተሞችና የገጠር መንደሮች ይብሳል። የትምህርት ሚኒስቴር መረጃም እንደሚያመለክተው በሀገራችን አምስት ሚሊየን ህጻናት የልዩ ፍላጎት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም ከእነዚህ ውስጥ ትምህርት ማግኘት የቻሉት ıı ከመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው።

በትምህርት ሚኒስቴር፣ በልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቡድን መሪ አቶ ዓለማየሁ ወ/ቂርቆስ፣ የልዩ ፍላጎት ሥርዓተ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል ተብለው የተለዩ ተማሪዎች ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሊያሰኛቸው የቻለው፣ በመደበኛነት የሚሰጠው ትምህርት ለእነርሱ ፍላጎትና የትምህርት አቀባበል ምቹ ባለመሆኑና የሚሰጠውን ትምህርት በአግባቡ እንዲከታተሉ የአጭር ወይም የረጅም ጊዜ ድጋፍና ክትትል እንዲሁም፣ መርጃ መሳሪያዎች የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው እንደሆነና ልጆቹ አስፈላጊው ድጋፍና ክትትል ተደርጎላቸው ትምህርት በአግባቡ ሲያገኙ፣ በእድሜያቸው ልክ አስፈላጊውን እውቀት እያገኙ ከደረጃ ወደ ደረጃ እያደጉ እንዲሄዱ እንደሚያስችላቸው ይገልጻሉ፤ አያይዘውም፣ እነዚህ ልጆች በሚፈልጉት ልክ ድጋፍ ካልተደረገላቸው የምንፈልጋቸው ዓይነት ልጆችን ማፍራት አንችልም ይላሉ፤ አክለውም፣ ይህ የትምህርት ሥርዓቱ ሃላፊነት እንደሆነም አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ።



**በትምህርት ሚኒስቴር፣ በልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቡድን መሪ አቶ ዓለማየሁ ወ/ቂርቆስ**

ቀደም ባሉ ጊዜያት የልዩ ፍላጎት ትምህርት ለብቻ ይሰጥ እንደነበር ያወሱት አቶ አለማየሁ፣ አሁን ግን በአካቶ ትምህርት ሥርዓት ስር እንዳለን በመጥቀስ፣ በዚህ የትምህርት ስርዓት አካል ጉዳተኛ ልጆች በአካባቢያቸው ባሉ ትምህርት ቤቶች፣ ድጋፍ እየተደረገላቸው፣ ከጉዳት አልባ ልጆች ጋር በአንድ ክፍል የሚማሩበት ሥርዓት እንደሆነ ይገልጻሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ በአካቶ ትምህርት ሥርዓት ከትምህርት ቅጥር ጊቢው፣ ከውሃ መጠጫው ከሽንት ቤቱ አንስቶ፣ የማስተማር ዘዴው፣ የትምህርቱ ይዘት፣ የመማር ማስተማሪያ መሳሪያዎችና የፈተና አሰጣጡ ለልጆቹ ተስማሚ እንዲሆን ይደረጋል ወይም ትምህርት ቤቱ ከልጁ ፍላጎት ጋር ራሱን ያስማማል። ነገር ግን፣ ይህ በጽሑፍ እንደሰፈረው በተግባር ብዙም የሚታይ አይደለም።

አካል ጉዳተኞችና ትምህርትን በተመለከተ ሁሉም በኃላፊነት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሰራ ሕገ መንግሥቱ ራሱ ትምህርትን በተመለከተ አስገዳጅ ድንጋጌን አላስቀመጠም ያሉት አቶ አለማየሁ፣ ለዚህም ከፍተኛ ፍርድ ቤት የህጻናት መብት ስምምነት ከወጣ በኋላ የኢትዮጵያ ፖሊሲዎች ምን ይላሉ? በሚል በı998 ዓ.ም ያጠናውን ጥናት በማስረጃነት ይጠቅሳሉ። ሕገ መንግሥቱ ስለ ትምህርት የሚያነሳው በሶስት አንቀጾች (በአንቀጽ36፣ 4ı እና 90) ብቻ እንደሆነ አቶ አለማየሁ ያነሳሉ፣ እንደ እርሳቸው ሐሳብ፣ በእነዚህ አንቀጾች ውስጥ “ትምህርት መብት ነው” የሚል ድንጋጌ የለም፤ በተመሳሳይም አንቀጽ 4ı ንዑስ አንቀጽ አምስት ለአካል ጉዳተኞችና አረጋውያን አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍ ይደረግላቸዋል በሚል አገላለጽ፤ ጉዳዩ አስገዳጅ ዓይነት እንዳልሆነ ያስቀምጣል፤ ይህም የትኛውም አካል የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ ግዴታዬ ነው ብሎ እንዳይዘው ያደርገዋል። ጎረቤታችን ኬንያ ትምህርትን የተመለከቱ ብቻ በትንሹ ı5 አንቀጾች በሕገ መንግሥቷ እንዳካተተች የጠቀሱት አቶ አለማየሁ፣ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ሀገርን የሚያሳድግ ትምህርት መሆኑን በሚገባ በመረዳታቸውና ትኩረት በመስጠታቸው እንደሆነ ይናገራሉ። እርሳቸው እንዳሉትም፣ ሀገርን ያለ ትምህርት ማሳደግ ስለማይቻል ትምህርትን በተመለከተ፤ ትምህርት ለሁሉም መብት መሆኑ በሕገ መንግሥቱ ተብራርቶ መገለጽ አለበት።

የአካል ጉዳተኛ ልጆች ከቤት ወጥተው ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ለማስቻል በየክልሉ በየአመቱ፣ ı5ሺ ዶላር የሚያወጡ መሳሪያዎች



አቶ ደምሴ ገብሬ

**በርካታ እናቶች አካል ጉዳተኛ ልጆቻቸውን ለማስተማር የትምህርት ቤት ደጃፍ ላይ እንባቸውን ያፈሳሉ፤ እነዚህ አካል ጉዳተኛ ልጆች ያሏቸው እናቶች ደግሞ አብዛኞቹ ባሎቻቸው ትተዋቸው ሄደው ብቻቸውን ለልጆቻቸው ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው**



ተማሪ ብርሃኑ ምናሴ



ወ/ሮ ሐይማኖት ወንድማገኝ

የተሟሉላቸው 200 የሚጠጉ የድጋፍ መስጫ ማዕከላት እየተገነቡ እንደሆነ የገለጹት አቶ አለማየሁ፣ ዋነኛው ችግር በማኅበረሰቡም ሆነ በትምህርት ቤቶች ዘንድ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ከፍተኛ የግንዛቤ ችግር መኖሩ እንደሆነ ይናገራሉ። የግንዛቤ ችግሩ ባይኖር አካል ጉዳተኛ ተማሪ ሲመጣ ተቀብሎ ወረዳውን እንዲህ ዓይነት ተማሪ መጥቷል ምን ላድርግ ብሎ መጠየቅ ይችላል፤ ከወረዳውም ሆነ ከክልሉም ቁርጠኝነት ያስፈልጋል። እነዚህ ልጆች ልክ እንደ ሌላው ልጅ በቂ ነው የሚያስብል ባይሆንም በጀት ተመድቦላቸዋል ያሉት አቶ አለማየሁ የግንዛቤ ችግር፣ ለልዩ ፍላጎት ሲሆን በጀት ማጣት፣ የትምህርት ሥርዓቱ ተለማጭ አለመሆንና የአጋዥ መሳሪያዎች አለመሟላት፣ የልጆቹን ችግርና ተሰጥዖ መለያ ማዕከላት አለመኖርና ሌሎችም በርካታ ችግሮች ቢኖሩም ፣ ከትምህርት ቤት ጀምሮ እስከ ክልል ያሉ አካላት ቢደጋገፉና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ቢዘረጋ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ይላሉ።

መምህር ክንዴ መኮንን፣ የብሔራዊ ኢትዮጵያ አፀደ ህጻናትና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ መምህር ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፣ በሀገራችን አካል ጉዳተኞችን የተመለከቱ በርካታ ሕጎችና መመሪያዎች ቢኖሩም፣ አፈጻጸሙ በግለሰቦች መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሣሌ ማንኛውም የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ገና ትምህርት ቤት ሲሄድ፣ ልክ ጉዳት አልባው ተማሪ፤ ወላጅ አምጥተህ፣ ተመዝግበህ፣ መጽሐፍ ውሰድ እንደሚባለው ብሬይል የሚያስፈልገው ተማሪም ብሬይል ተሰጥቶት፣ የምልክት ቋንቋ የሚያስፈልገውም በምልክት ቋንቋ ለመማር ተመቻችቶለት እኩል ትምህርት መጀመር ቢገባውም፣ በተግባር ግን ይህ ሲሆን አይታይም። በጣም ጥቂቶች ካልሆኑ በስተቀር ብዙዎች ይህን ለማሳካት ጥረት አያደርጉም። ከዚህም በተጨማሪ፣ የትምህርት ቤት መንገዶችና ቅጥር ግቢዎች አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ አድርገው ባለመሰራታቸው ለአካል ጉዳተኞች አይመቹም ያሉት መምህር ክንዴ አንዳንድ መንገዶችና የትምህርት ቤት አካባቢዎች፣ እንኳን ለአይነ ስውር፣ አይናማውንም ለአደጋ የሚያጋልጡ እንደሆኑ ይናገራሉ።

በትምህርት ቤቶች ቅጥር ግቢ ውስጥ አዳዲስ ህንጻዎች በሚገነቡበት ጊዜ ለአካል ጉዳተኞች ተዳፋታዊ መወጣጫ እንዲሰራ ሲጠየቅ፣ ትምህርት ቢሮ ለዚህ በጀት አልመደበለትም፤ በጀት የለም የሚል ምላሽ እንደሚሰጥ የጠቀሱት መምህር ክንዴ፣ ፈቃደኛ ግለሰቦች ካልሆኑ በስተቀር አብዛኛው የትምህርት ቤት ማኅበረሰብ ለልዩ ፍላጎት ያለው አመለካከት አነስተኛ መሆኑንና ልጆቹንም ተቀብሎ ለማስተማር ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ይናገራሉ። የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆችም አንዱ ትምህርት ቤት እምቢ ሲባሉ፣ ሌላው ጋር ሞክረው ይማራሉ እንጂ፣ ልክ እንደ ሌላው ልጅ በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ወይም እነርሱ በፈለጉበት ትምህርት ቤት ገብተው መማር ከባድ እንደሆነ ይገልጻሉ።

በተለይ ከመጽሐፍ ጋር ተያይዞ መደበኛውን የመማሪያ መጽሐፍ ለአይነ ስውር ተማሪዎች ተብሎ ታስቦ አብሮ እንደማይዘጋጅ ያነሱት መምህር ክንዴ፣ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ብቻ ግዴታ እንደሆነ አውቀው ሲያስጽፉ፣ አብዛኞቹ ግዴታ መሆኑን ካለማወቃቸው የተነሳ የእርዳታ ድርጅቶች እስኪረዱን ጠብቁ የሚሉም እንዳሉ ይጠቅሳሉ። አያይዘውም፣ እርሳቸው የጠቀሷቸውንና ሌሎችም ከልዩ ፍላጎትና ከአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ጋር የተያያዙ ችግሮችን በተመለከተ በየጊዜው ምን መደረግ አለበት? በሚለው ላይ የተለያዩ ተቋማት ስብሰባ እንደሚቀመጡ በማስታወስ ነገር ግን፣ የተባለው ሁሉ ተግባር ላይ እንደማይውልና ትንሽ ጅማሮም ሲኖር ብዙ ርቀት እንደማይጓዝ ተናግረዋል።

ተማሪ ብርሃኑ ምናሴ፣ በዳግማዊ ምኒልክ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን፣ እስከ 9ነኛ ክፍል በሻሸመኔ ከተማ እንደተማረ የሚናገረው ተማሪ ብርሃኑ በትምህርት ቤት የነበረው ቆይታ መልካም እንደነበርና አሁንም ከትምህርት አሰጣጡ ጀምሮ በመምህራኖቹ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች የሚያደርጉት ድጋፍ መልካም እንደሆነ ተናግሮ ነገር ግን፣ የመማሪያ መጻሕፍት ለዓይነ ስውራን ተማሪዎች በብሬል ማግኘት ከባድ እንደሆነ ጠቁሟል፤ ከዚህም በተጨማሪ በብሬል የሚይዟቸውን






ወ/ሮ ሀና ፍራንኮ

ማስታወሻዎች በእጅ ተነበው የሚዘለቁ ባለመሆናቸው የድምጽ መቅረጫ ቴፕሪከርደሮች ትኩረት ተሰጥቶት እንዲኖርን ቢደረግ ጥሩ ነው ብሏል።

በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ አካል ጉዳተኞችን ምንም የማይችሉ አድርጎ የማሰብ ዝንባሌ ይታያል ያለው ተማሪ ብርሀኑ፣ በዚህ አስተሳሰብ ሳቢያ በተለይ ከከተማ ውጪ ያሉ አካል ጉዳተኞች ትምህርት እያገኙ እንዳልሆነ በርካቶችም በወጣትነት እድሜያቸው ልመና ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ በመግለጽ፣ እነዚህን ልጆች ወደ ትምህርት ገበታ እንዲመጡ ማድረግ ከግለሰብ ሕይወት ጀምሮ ቤተሰብንም ሐገርንም መለወጥ እንደሆነ ተረድቶ፣ አካል ጉዳተኞች ከእክል አልባው ያላነሰ፣ እንዲያውም የተሻለ ትምህርት የመቀበል አቅም እንዳላቸው ተገንዝቦ ማገዝ ይገባል የሚል መልዕክት አስተላልፏል።

ሌላዋ ያነጋገርናት ወ/ሮ ሐይማኖት ወንድማገኝ፣ የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪ ስትሆን፣ የሰባት ዓመት የአካል ጉዳተኛ ልጇን ለማስመዝገብ ወደ አንድ የመንግሥት ትምህርት ቤት በሄደችበት ጊዜ፣ አካል ጉዳተኛ መሆኗን ስትናገር "አታስመዝግቢያት ትምህርት ሲጀመር ይዘሻት ነይ" የሚል ምላሽ እንደተሰጣትና ትምህርት ሲጀመር ልጇን ይዛ ስትሄድ ግን፣ እንደዚህ ዓይነት ጉዳይ አንቀበልም የሚል ምላሽ እንደሰጧት ትናገራለች። "እኔ አብሪያት እቆያለሁ፣ ሽንት ቤት በሚያስፈልጋት ጊዜም እኔ አለሁ" ብትልም "አይቻልም"" የሚል ምላሽ ሰጥተው እንደመለሷት የምትናገረው ወ/ሮ ሐይማኖት፣ ማኅበረሰቡም ሆነ ትምህርት ቤቶች ለአካል ጉዳተኛ ያላቸው አመለካከት ሞራልን የሚጎዳ ነው ትላለች፣ ሌላ ትምህርት ቤት ስሄድም "ሞልቷል" ብለው መልሰውኛል ብላለች።

በየመገናኛ ብዙኃኑ አካል ጉዳተኛ ልጆቻችሁን አትደብቁ፣ አውጡ፣ አስተምሩ፣ ህክምና ውሰዱ ይባላል፣ ነገር ግን ህክምና ስንወስድ መንገድ ይዘጋብናል የምትለው ወ/ሮ ሀይማኖት፣ ልጆቻችንን ለማዝናናት እንኳ ይዘናቸው ስንወጣ ሰዉ እንደተለየ ፍጥረት ነው የሚያያቸው በማለት ቅሬታዋን ትገልጻለች፣ በተለይ ልጇን እያዩ ከንፈር የሚመጡት ነገር በጣም ያመኛል ያለችው ወ/ሮ ሐይማኖት፣ በየመገናኛ ብዙኃኑ ስለ አካል ጉዳተኝነት በርካታ አስተማሪ ነገር ቢነገርም፣ የተማሪ የሚባለው የማኅበረሰብ ክፍል እንኳ አስተሳሰቡ ገና አልተለወጠም፣ ስለሆነም ሰፊ ስራ መስራት ያስፈልጋል ትላለች።

አቶ ደምሴ ገብሬ ደግሞ፣ በተሽከርካሪ ወንበር የሚንቀሳቀስ የ4 ኣመት ልጇን ትምህርት ቤት ማስገባት ያልቻለችን እናት ለማገዝ ህጻኑን ወደ ትምህርት ቤት ይዘው በሄዱበት ጊዜ አሳዛኝ ምላሽ እንደገጠማቸው ያስታውሳሉ፣ አቶ ደምስ እንዳሉት፣ ህጻኑ፣ እኩያ ጓደኛው ትምህርት ቤት ሲሄድ እርሱ ቤት ውስጥ በመቅረቱ አኩርፎ ለሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ሳይተኛ በማደሩ፣ እናቱ ልጁ የሆነውን ስትነግራቸው፣ በራሳቸው ፈቃደኝነት ልጁን ወደ ትምህርት ቤት ቢወስዱትም፣ በቦርድ ነው የሚወሰነው በሚል፣ ሁለት ቀጠሮዎችን ከሰጧቸው በኋላ፣ ልጁ የሚንቀሳቀሰው በዊልቸር በመሆኑ አስተማሪዎቻችን ላይ ጫና እንፈጥራለን፣ ተማሪዎች በሚወጡ በሚገቡበት ጊዜ ማን እያወጣ ያስገባዋል? የሚል ምላሽ ተሰጥቷቸዋል። ልጁን ለሚያወጣና ለሚያስገባ ሰው ተጨማሪ ክፍያ ልከፈል ቢሉም "በፍፁም አንችልም" የሚል ምላሽ እንደተሰጣቸው ይናገራሉ።

አቶ ደምስ እንዳሉት፣ በቢሾፍቱ ከተማ አንድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤት ያለ ሲሆን፣ ይህ ትምህርት ቤት ለአይነስውራንና የመስማት ችግር ያለባቸውን እንጂ፣ ሌላ አካል ጉዳት ያለበትን ልጅ የሚቀበል አይደለም። እውነታውም፣ እንዲህ ዓይነት ልጆች ከጉዳት አልባው ተማሪ ጋር ተቀላቅለው መማር የሚችሉ፣ ነገር ግን የተለየ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ናቸው ያሉት አቶ ደምስ፣ አያይዘውም፣ በየቤቱ ያሉ አካል ጉዳተኛ ልጆች በተለይም ወላጆቻቸው የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን አሟልተው ማስተማር የማይችሏቸውን ልጆች ተቀብሎ የሚያስተምር ትምህርት ቤት በቢሾፍቱ ከተማ መገንባት እንደሚገባውና ለዚህም፣ ከበጎ ፈቃደኛ ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የተቻላቸውን ጥረት እያደረጉ እንደሚገኙ ገልጸውልናል።


በዚሁ በቢሾፍቱ ከተማ አድኣ ወረዳ፣ የ"ራዕይ ትውልድ የአካል ጉዳተኞች ማህበር" መስራችና ሥራ አስኪያጅ ወ/ሮ ሀና ፍራንኮ በበኩላቸው፣ በከተማው በርካታ አካል ጉዳተኞች ትምህርት ለማግኘት እንደሚቸገሩ ገልጸው፣ ማኅበሩ አካል ጉዳት ያለባቸውንና ትምህርት ቤቶች አንቀበልም ያሏቸውን ልጆች የትምህርት ድጋፍ በማሟላት ትምህርት እንዲያገኙ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝና አገልግሎት መስጠት ከጀመረበት ከአምስት ዓመታት በፊት ጀምሮ በርካታ አካል ጉዳተኛ ልጆችን ከተደበቁበት ያወጣና የትምህርት መርጃ መሳሪያ የሚያስፈልጋቸውንም በማገዝ ለቁም ነገር እንዳደረሰ ይናገራሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፣ በርካታ እናቶች አካል ጉዳተኛ ልጆቻቸውን ለማስተማር የትምህርት ቤት ደጃፍ ላይ እንባቸውን ያፈሳሉ፣ እነዚህ አካል ጉዳተኛ ልጆች ያሏቸው እናቶች ደግሞ አብዛኞቹ ባሎቻቸው ትተዋቸው ሄደው ብቻቸውን ለልጆቻቸው ዋጋ የሚከፍሉ ናቸው። በርካታ እናቶችም ልጆቻቸውን ያለ ደጋፊ ተሸክመው በመዞር ለከፍተኛ የጤና ችግር ይዳረጋሉ። እነዚህ ልጆች በተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ በሆነ ስህተት ለአካል ጉዳተኝነት የተዳረጉ እንጂ እንደማንኛውም ዜጋ ሀገሪቱ ካላት ሀብት እኩል የመጠቀም፣ እንደ እክል አልባው ልጅ ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር መብት ያላቸው ናቸው የሚሉት ወ/ሮ ሀና፣ ነገር ግን ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ ብዙዎች እንደ እድሜ እኩዮቻቸው ትምህርት ቤት ውሎ መግባትና መማር እየናፈቃቸው በአልጋ ላይ እንደታሰሩ እድሜያቸው ያልፋል በማለት በቁጭት ይናገራሉ።

አሁንም በርካታ እናቶች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለማስገባት ከፍተኛ ዋጋ እንደሚከፍሉ ያነሱት ወ/ሮ ሀና፣ እነዚህን እናቶች ለማሳረፍ ልጆቹንም ከተጠሙት ትምህርትና ከእኩዮቻቸው ጋር ለማገናኘት መንግሥት፣ አቅሙ ያላቸው ተቋማትና ግለሰቦች በያገባኛል መንፈስ፣ አካል ጉዳተኝነት ነገ እኔም ቤት ላለመግባቱ ዋስትና የለኝም በሚል ስሜት የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

# ‹‹የበደለኝ ሥርዓት እንጂ አገሬ ወይም ሕዝብ አይደለም››

**- ዶክተር ፍቅሩ ማሩ**



ስሜነህ ደስታ

**የዚህ እትም የፈለግ ዓምድ እንግዳችን ዶክተር ፍቅሩ ማሩ ናቸው። ሥራ የጀመሩት በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በኢትዮጵያ አየር ኃይል የተዋጊ ጀት አብራሪ በመሆን ነው። በደርግ ዘመን በፖለቲካ አስተሳሰባቸው ምክንያት ለስደት ተዳርገው ለበርካታ ዓመታት በውጭ አገር ኖረዋል። በዘመነ ኢህአዴግ ወደ አገራቸው ተመልሰው በሕክምና ሙያ ኢትዮጵያን ለማገዝ ብዙ ጥረት አድርገዋል። የነበረው ሥርዓት በኋላ በነጻ የተሰናበቱባቸውን ሁለት ክሶች መስርቶባቸው አምስት ዓመታትን በወህኒ ቤት አሳልፈዋል። ከእስር እንደተፈቱ ወደ ውጭ አገር ያመሩት ዶክተር ፍቅሩ ፣ ከሁለት ሳምንት ቆይታ በኋላ ‹‹የበደለኝ ሥርዓት እንጂ አገሬ ወይም ሕዝብ አይደለም›› በማለት ከፍተኛ የልብ ስፔሻሊስቶችን የያዘ ቡድን እየመሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ኢትዮጵያውያን የልብ ታካሚዎች ሕክምና እንዲያገኙ አድርገዋል። ከእኒህ አገር ወዳድ ጋር ሕይወታቸውን እና ወቅታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያደረግነውን ቆይታ ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበነዋል። መልካም ንባብ!**

ዶክተር ፍቅሩ ማሩ በአዲስ አበባ ከተማ ፈረንሳይ ለጋሲዮን አካባቢ በሚገኘው ጉራራ የተባለ ቦታ በ1943 ዓ.ም. ተወለዱ። ለቤተሰባቸው አምስተኛ ልጅ ናቸው። የክቡር ዘበኛ ሳጅን የነበሩት አባታቸው ኮሪያ ዘምተዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በቀድሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (ቀ.ኃ.ስ) በአሁኑ ኮከበ ጽባሕ እስከ ሰባተኛ ክፍል ተከታትለዋል። ከሰባተኛ ክፍል በኋላ ታላቅ ወንድማቸው ለሥራ ወደ አሰላ ሲሄዱ ወንድማቸውን ተከትለው በመሄድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ አሰላ ራስ ዳርጌ ትምህርት ቤት ተምረዋል። አሰላ እያሉ ጀት በሰማይ ላይ ሲበር ሲመለከቱ በጣም ይማረኩ ስለነበረ የጀት አውሮፕላን ማብረር ምኞት ነበረቸው። ምኞቸውን እውን ለማድረግ በ1962 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አየር ኃይል ጀት አውሮፕላን ለማብረር ስልጠና ለመውሰድ ከተመለመሉ 27 ወጣቶች አንዱ መሆን ችለዋል። ስልጠናው ከባድ ስለነበረ ከሃያ ሰባት ሰልጣኞች እሳቸውን ጨምሮ አምስቱ ብቻ አጠናቀው በምክትል መቶ አለቃ ማዕረግ ተመርቀዋል። በአየር ኃይሉ ኃላፊዎች ያላቸው ብቃት ታይቶ ከድምጽ ፍጥነት አንድ ነጥብ ስድስት በላይ የሚፈጥነውንና በወቅቱ ከፍተኛ የነበረውን የሱፐር ሶኒክ F-5 የጦር ጀት ለማብረር ሰልጥነው በአግባቡ በማጠናቀቃቸው ከአስተማሪዎቻቸው ጋር አብረው እስከማብረር ደርሰዋል።

ዶክተር ፍቅሩ ስለኢትዮጵያ አየር ኃይል ሲናገሩ ብዙዎቹ የአውሮፓ አገራት አየር ኃይል ከማቋቋማቸው በፊት በ1936 ዓ.ም. የተቋቋመና በወቅቱ በዓለም ላይ የተደነቀ ተቋም እንደነበረ ይናገራሉ። ከውጭ አገራት ከምስራቅ አፍሪካ እንዲሁም ናይጄሪያን ከመሳሰሉ አገራት ሰልጣኞች ወደ ኢትዮጵያ አየር ኃይል በመምጣት ይሰለጥኑ እንደነበረም ያስታውሳሉ።

በንጉሱ የመጨረሻ ዘመን መቶ አለቃ የነበሩት የጦር ጀት አብራሪ እንግዳችን በአየር ኃይል ውስጥ የተነሳውን አመጽ (አብዮት) ካነሳሱት ውስጥ አንዱ ነበሩ። በኋላም አራት ኪሎ በነበረው ደርግ እና በአየር ኃይሉ መካከል አገናኝ በነበረው ንዑስ ደርግ ውስጥ በአገናኝነት አስተባብረዋል። በዚህ ወቅት ሶማሊያ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ክፍተት በመጠቀም የስለላ አውሮፕላን በመላክ በኢትዮጵያ አየር ክልል ላይ እንዲንቀሳቀስ ማድረጓን ተከትሎ ሁለት ጀቶች ተነስተው አውሮፕላኑን በማስገደድ ኢትዮጵያ መሬት ላይ እንዲያርፍና በቁጥጥር ሥር እንዲውል ካስተባበሩት ሰዎች አንዱ ነበሩ። በየትኛውም ጊዜ የውስጥ ክፍተት ሲኖር የውጭ ኃይሎች ሊያጠቁን መሞከራቸው አይቀርም ፤ ስለሆነም በማንኛውም ጊዜ በውስጣችን የሚኖረውን ክፍተት በተቻለ መጠን በውይይት መፍታት ብልህነት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል ይላሉ።

በአየር ኃይል ንዑስ ደርግ ውስጥ የአስተባባሪነት ሚና የነበራቸው በወቅቱ መቶ አለቃ የነበሩት እንግዳችን ወታደር ሥልጣኑን መያዝ የለበትም ሕዝባዊ መንግስት መቋቋም አለበት የሚል አቋም ነበራቸው። እሳቸው የወሰዱትን አቋም የሚያራምዱ ጓደኞቻቸውን ደርግ ሲያስር እንዲሁም በአደባባይ ሲረሸን ሲመለከቱ በጎንደር በኩል ጠፍተው በሱዳን




**የጦር ጀት አብራሪ በነበሩ ጊዜ**

አድርገው ሲውድን ገቡ።

በሱዳን የስደት ቆይታቸው ጋራዥ ውስጥ የመኪና ጠጋኝ በመሆን ዘጠኝ ወራት ከሠሩ በኋላ በውጭ አገር ሰዎች እገዛ ወደ ስዊድን አምርተዋል። ስዊድን ከሄዱ በኋላ ፖስታ ቤት ሠርተዋል፤ ካፍቴሪያ ከፍተው ሠርተዋል፤ አዛውንቶችን ተንከባክበዋል እንዲሁም ሬሳ መሸከም እና ሌሎች ሥራዎችንም ሠርተዋል። ሐኪም ብሆን የተለያዩ አገራት በመሄድ ልሠራ እችላለሁ ፣ የሥራ ዋስትናም አገኛለሁ በሚል ሀሳብ በመጨረሻ የሕክምና ትምህርት ተምረዋል። የሕክምና ትምህርት ሲማሩ ትዳር መስርተው ስለነበረ ልጅ የማሳደግ ኃላፊነትም ነበረባቸው። ተደራራቢ ኃላፊነት ስለነበረባቸው በወቅቱ ከባድ ጊዜ አሳልፈዋል። ይሁን እንጂ ትምህርታቸውን በተገቢው ሁኔታ በመማር ማጠናቀቅ ችለዋል። ከመጀመሪያው የአጠቃላይ ሕክምና ትምህርት በኋላም በትምህርታቸው ገፍተው የውስጥ ደዌ ሕክምና ስፔሻሊስት እና የልብ ስፔሻሊስት መሆን ችለዋል።

የሁለት ዘርፍ ስፔሻሊስቱ ዶክተር ፍቅሩ ትዳር የመሠረቱት የሕክምና ባለሙያ ከሆኑት ዶክተር መሠረት መንግሥቱ ጋር ነበር። ጥንዶቹ ዶክተሮች ሁለት ሴት ልጆችን አፍርተዋል። ፍቅርተ ፍቅሩ የአይቲ ኢንጅነር ስትሆን ሌላኛዋ ልጃቸው ሠላማዊት ፍቅሩ የአጠቃላይ ሕክምና ትምህርቷን ጨርሳ ዶክተር ሆናለች። በአሁኑ ወቅትም የአባቷን ፈለግ በመከተል የውስጥ ደዌና የልብ ስፔሻሊስት ለመሆን እየሠራች ነው። ሁለቱም ልጆቻቸው ትዳር መሥርተው እያንዳንዳቸው ሁለት ልጆችን ወልደው የአራት ልጆች አያት አድርገዋቸዋል።

ዶክተር ፍቅሩ በስደት ሱዳን ከገቡ በኋላ ደርግን በመቃወም የተለያዩ ሥራዎች ሠርተዋል። በስዊድንም በኢሕአፓ አመራር ውስጥ ገብተው በአውሮፓ ደረጃ በፖለቲካው ተሳትፈዋል። በመጀመሪያ በተማሪዎች ማህበር ቀጥሎም ኢሕአፓ ራሱን ይፋ ባወጣበት ወቅት በፓርቲው የአውሮፓ ክንፍ ተሳታፊ ነበሩ። ከገጠር ወደ ከተማ የሚለውን የትግሉን አካሄድ ይደግፉ ስለነበር የኢሕአፓ ወታደራዊ ክንፍ በመደገፍ አብዮቱን ለማስቀጠል ጥረት አድርገዋል።

ከወያኔ ጋር በነበረ የትጥቅ ትግል ሻቢያ ወያኔን በመደገፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ሰራዊትን በኃይል ስላጠቁት በሕይወት የተረፉት ወደ ሱዳን መሰደዳቸውን በኃዘንና በቁጭት ያስታውሳሉ። ዶክተር ፍቅሩ ስለነበረው ትግል ሲያስረዱ ‹‹ የደርግን ሥርዓት እንደምንቃወመውና እንደምንታገለው ያህል የመገንጠል ሀሳብ የሚያራምዱትንም እንቃወም ነበር። ደርግ ወድቆ ኢህአዴግ ሥልጣን ሲይዝም አገሪቷን ወደብ አልባ ማድረጉን አምርረን ስንቃወምና ስንታገል ነበር። በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያዊ ሶስተኛ ዜጋ ነው የሆነው። ሻቢያና ወያኔ ናቸው አገሪቷን እንዳሻቸው ሲያስተዳድሩ የነበሩት። ሁለቱ አካላት በፈጠሩት ልዩነት ጦርነት ተጀምሮ በወያኔ አሸናፊነት ሲገባደድ ያን ጊዜ ነው ኢትዮጵያውያን ወደ ሁለተኛ ዜግነት የመጣነው ›› ይላሉ።

ዶክተር ፍቅሩ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኤች አይ ቪ ኤድስ ኮንፍረንስ በ1991 ዓ.ም. አዲስ አበባ ሲደረግ ከስዊድን መጥተው ነበር። በኢትዮጵያ ያለውን የሕክምና ሁኔታ ሲመለከቱ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የልብና ልብ ነክ ሐኪም አንድ ብቻ መሆኑን ይገነዘባሉ። በዚህ ጊዜ በፖለቲካው በኩል ታግለው የሚያታግሉና የተሻለ ሥራ የሚሠሩ ብዙ ሰዎች ስላሉ የፖለቲካ ተሳትፏቸውን በማቆም በሙያቸው ኢትዮጵያን መርዳት እንደሚገባቸው በማመን የጥቁር አንበሳ ወዳጆች ማህበርን አቋቁመው የተለያዩ ቁሳቁሶች ከስዊድን አገር በመላክ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልን መርዳት ጀመሩ።

በመቀጠልም የዛሬ አስራ ሰባት ዓመት 85 በመቶ የውጭ ኢንቨስትመንት በማምጣት 15 በመቶ የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን በማሳተፍ አዲስ የልብ ሕክምና ማዕከልን በአዲስ አበባ በመመሥረት የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ። የሕክምና ማዕከሉ የተመሰረተበት ዋና ዓላማ ፈረንጆች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በእርዳታም ሆነ በሌላ መንገድ ከፍተኛ የልብ ሕክምና አገልግሎት ሲሰጡ የእውቀት ሽግግር እንዲኖር በማድረግ ቴክኖሎጂው ኢትዮጵያ እንዲቀር ለማድረግ በሚል ነው። እስካሁን ሰባት ሐኪሞች በከፍተኛ ደረጃ ሰልጥነዋል ፤ ወደ ፊትም ሌሎችን ለማሰልጠን ዕቅድ ተይዟል። በኢትዮጵያ ውስጥ ሌላ ቦታ የማይሰጡ ሕክምናዎች በማዕከሉ ብቻ ይሰጣሉ። ይህ በቂ እንዳልሆነና ከዚህም በላይ መሥራት እንደሚቻል ዶክተር ፍቅሩ ይናገራሉ። በኪራይ ቤት ውስጥ ሆነው በማያፈናፍን ሁኔታ የልብ ሕክምናው እንደሚሠራም ይገልጻሉ። ይህን የተጣበበ አሠራር የሚያሻሽል ከሃያ እስከ ሰላሳ ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ፕሮጀክት በመቅረጽ ሀብትና ዕውቀት አሰባስበው የጨረሱ ቢሆንም መሬት ለማግኘት ያደረጉት ከሁለት ዓመት በላይ ያስቆጠረ ጥረት እስከ አሁን ፍሬ እንዳላፈራ በኃዘን ይናገራሉ። የመሥራት ችሎታ እያለ በተጣበበ ሁኔታ ሕክምናውን መስጠት ስለማይቻል ፤ ሰፋ ለማድረግ ሲባል ከኪራይ ቤት ወደ ኪራይ ቤት ለመሄድ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለመሥራት ያላቸውን ትልቅ ህልም እውን ለማድረግ ሀብትና ዕውቀት አሰባስበው የሚቀራቸው ተደራሽ የሆነ መሬት አዲስ አበባ ውስጥ ማግኘት ነው። ልብ ለአራት ደቂቃ በተለያየ ምክንያት ከቆመ አንድ ሰው ይሞታል። አንድ ሰው ልቡን ታሞ በአንድና በሁለት ሰዓት ውስጥ ወደ ማዕከሉ ካልደረሰ የመዳን ዕድሉ በ80 በመቶ ዝቅ ይላል። አንድ ታማሚ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከመጣ 95 በመቶ የመዳን ዕድል አለው። የልብ ሕመም ጊዜ የማይሰጥ በሽታ ስለሆነ ለማዳን እንዲሁም ዘላቂ የሆነ የሕመምና በሽታ ይዞ እንዳይሄድ ለማድረግ ተደራሽ የሆነ ቦታ ማግኘት ያስፈልጋል የሚሉት ዶክተር ፍቅሩ ይሄን ለማስገንዘብ ያደረጉትን ጥረት ሲናገሩ ‹‹የሚመለከታቸውን ለማስረዳት በተደጋጋሚ

ሞክረናል ፤ ውጤት ግን አላገኘንም። አዲስ የልብ ሕክምና ማዕከል አሁን ያለው አቋም በሰለጠኑ ሐኪሞችና በዘመናዊ መሣሪያዎቹ የሚሰጣቸው ሕክምናዎች በአውሮፓ ደረጃ እንደሚሰጡት ደህንነታቸውና ስታንደርዳቸውን የጠበቁ ናቸው። ሁለት የአፍሪካ አገሮች ይሄን የተደራጀ ተቋም አይተው ‹50 በሙቶ ኢንቨስትመንቱን ሸፍነን ተደራሽ የሆነ መሬት በነጻ እንሰጣለን› በማለት ከኢትዮጵያ ተነቅሎ እንዲሄድ በስዊድን መንግሥት በኩል ጥያቄ አቅርበዋል። እኔ አገሬን አልበድልም በማለት ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ እየለፋሁና እየታገልኩኝ እገኛለሁ። አሁንም ቢሆን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለምሥራቅ አፍሪካ የሚያገለግለው ይህ ተቋም ከእጃችን እንዳይወጣ መሬት የሚሰጡ ተቋማት ሁኔታውን ተገንዝበው ዐይናቸውን እና ጆራቸውን ከፍተው ያድምጡ እላለሁ። ሌሎችም ሁኔታው የሚፈቅድላቸው አካላት ከአቅማችን በላይ የሆነ ሁኔታ ተፈጥሮ ተቋሙ ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ መሬት ለሚሰጡት ተቋማት ያስረዱልን» በማለት ሆስፒታሉን ለመሥራት ተደራሽ መሬት የሚገኝበት መንገድ እንዲመቻችላቸው አጥብቀው ይጠይቃሉ።

ዶክተር ፍቅሩ በዘመነ ኢህአዴግ አምስት ዓመት ታስረዋል። ለእስር የዳረጋቸው ጉዳይ ቀረጥ ያልተከፈለበት የሕክምና ቁሳቁስ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚል ነበር። ቁሳቁሶቹ ለልብ ሕክምና እገዛ ለማድረግ የመጡ ጓንትና ፕላስቲኮች መሆናቸውን በወቅቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ለነበሩት ዶክተር ቴዎድሮስ አድሃኖም ቀርበው አስረድተዋል። ዶክተር ቴዎድሮስም ለእነ አቶ መላኩ ፈንታ ነግረውላቸው ክሳቸው ተቋርጧል። ከዓመታት በኋላ "ክሱ የተቋረጠው ለእነ አቶ መላኩ ጉቦ በመክፈል ነው" በሚል ክስ ተመሥርቶባቸው ለእስር ተዳርገዋል። ዶክተር ቴዎድሮስ ክሱ የተቋረጠው በእሳቸው አሳሳቢነት እንደሆነ እያወቁ ለሕሊናቸው ሲሉ እውነቱን ያልመሰከሩላቸው «በመሰረታዊነት በጣም ጨካኝና ክፉ ሰው ስለሆኑ ነው» ብለው ያምናሉ። ከዚህ በተጨማሪ ዶክተር ቴዎድሮስ ላቅ ያለ የሕክምና ስፔሻሊስቶች ለኢትዮጵያ አያስፈልጓትም፤ በጤና ጣቢያ ደረጃ ያሉት ይበቋታል በሚል ለስፔሻሊስት ሐኪሞች ከፍተኛ ጥላቻ እንዳላቸው ይገልጻሉ። ይሄ አስተሳሰብ ደግሞ ኢትዮጵያ እንዳታድግ የሚፈልጉት የነጮች አስተሳሰብ ነው። ስለሆነም ጥቁሮች ላቅ ያለ ትምህርት አያስፈልጋትም የሚለውን የነጮች አስተሳሰብን ለማስፈጸም ተግቶ የሚሠራ ነው በማለት ያስረዳሉ።

አያይዘውም «አሁን ያለበትን የዓለም የጤና ድርጅት መሪነት ቦታን ከፀባዩና ከተስማሚነቱ አንጻር ማግኘት አልነበረበትም። እንኳን ይህ ከፍተኛ ቦታ ከዚያም በታች ቢሆን የሚገባው ሰው አይደለም። የነጮቹን አስተሳሰብ አራማጅ ስለሆነ ነው ቦታውን ሊያገኝ የቻለው። ለ27 ዓመት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ጋር ሲያሰቃይ መኖሩ ሳይበቃው ፣ 50 ዓመት ኢትዮጵያን ወደ ኋላ ጎትቶ ያደኸየውን አሸባሪውን ወያኔን መልሶ ለማምጣት ያለበትን የኃላፊነት ደረጃና ተቋም በመጠቀም የሚያደርገው



በእስር ጊዜ

ተግባር የድሮ ሥራውን የሚያጠናክር ነው። ወደ ውስጥ ብዙ አልገባም እንጂ በሚያደርገው ተግባር እንደ ኢትዮጵያዊ የማፍርበት ሰው ነው» በማለት ይገልጻሉ።

ዶክተር ቴዎድሮስ የሚደግፉት አሸባሪው ወያኔ በመከላከያ ሠራዊት ላይ የከፈተው ጥቃት፣ እንዲሁም በአማራና አፋር ሕዝብ ላይ ሆነ ሌላው አካባቢ የሚያደርሰው ስቃይና እንግልት አዲስ ነገር እንዳልሆነ ዶክተር ፍቅሩ ይናገራሉ። አሁን በጅምላ አደረገው እንጂ ቀደም ሲል ሜካ በትጥቅ ትግል በነበረበት ጊዜ ጀምሮ በራሱ ሕዝብ ላይ እንዲሁም አብረው ለትግል የተሳተፉትን አባላቶቹን በጭካኔ ሜካ ውስጥ ከአንገታቸው በታች እየቀበረ የማሰቃየትና የመግደል ታሪክ እንዳለው ይገልጻሉ። ሲመሠረት ጀምሮ ተኮትኩቶ ያደገውም ግፍና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ስለሆነ ማሰቃየትና መግደልን መፍትሔ አድርጎ የሚጠቀም ቡድን መሆኑን ያስታውሳሉ። አሁን እያደረጉ ያሉት አሰቃቂ ድርጊት የናዚዎችንም ሆነ የሌሎችን አሰቃቂ ታሪክ ያነበቡ ቢሆንም የአሸባሪው ወያኔ አሰቃቂ ድርጊት ግን የሚያህል ተፈልጎ እንደማይገኝ፤ ይህም ከአፈጣጠራቸውና ከባህሪያቸው እንደሚመነጭ እንዲሁም ከጥፋትና ከጭካኔ ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን በትግል ወቅት ከሚያውቁት ባህሪያቸው በመነሳት ያስረዳሉ።

አሁን ስላለው ሁኔታ ሲናገሩም «ቀደም ሲል የነበሩትን የወታደራዊ አሰላለፍ ሁኔታዎች በማየት አሁን ያሉትን ነገሮች ተመልክቼ እንደወታደር ስገመግመው ዶክተር ዐቢይ የወያኔን እንቅስቃሴ ገተው አሁን ለተደረሰው ደረጃ ማድረሳቸው በጣም የሚደነቅ ተግባር ነው። ወደ ፊት ደግሞ ዛሬ የሞቱት እና የታሰሩት እንዳሉ ሆነው እነ ጌታቸውና ደብረጽዮን መያዛቸውና መደምሰሳቸው የማይቀር ነው። እነሱ ከተደመሰሱ በኋላ ይግባውም፣ አይግባውም አስተሳሰባቸውን ተቀብሎ የሚከተላቸው ሕብረተሰብን እንዴት መቀየር እንደሚገባ በውጭ ያሉ ወገኖች ሀገር ውስጥ ካሉት ጋር በመቀናጀት የሌሎችንም አገሮች ተሞክሮ በመመልከት ትምህርት በመውሰድ ከፍተኛ ጥናት በማድረግ መፍትሔ ሊደረግለት የሚገባ ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል እያደረገ ያለውን ተግባር ሳንቸኩል በትዕግስት በመጠበቅ ሁላችንም ተረድተን ልናግዝ ይገባል። ምክንያቱም ሙሉ መረጃ ያለው መከላከያ ጋር ነው። እርስ በእርሳቸው ተከፋፍለው ወይም በሌላ መንገድ ብዙ ጥፋት ሳይደርስ እጅ እንዲሰጡ የማድረግ ዘዴም ይኖራል። ንግስት ጣይቱ ከጣሊያን ጋር በነበረ ጦርነት በአንድ ወቅት ‹ውጊያ ከማድረግ ይልቅ ከብቦ በመያዝ ግንኙነት በማቋረጥ ውሃ እንዳያገኙ ማድረግ› የሚል ምክር አቅርበው ተግባራዊ ሆኖ የተገኘው ድል የሚታወቅ ነው። ስለሆነም መንግሥትንም ሆነ መከላከያን ለመውቀስ መቸኮል አይገባም» በማለት ሀሳባቸውን ከሰጡ በኋላ የአካሄድ አቅጣጫ ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም ትዕግስት በማድረግ የመንግሥትና የመከላከያን ተግባር መከታተል እንደሚገባ ገልጸዋል።

ዶክተር ፍቅሩ ከ45 ዓመታት በላይ ከነጮች ጋር ኖረዋል። ስለ አውሮፓውያን እና አሜሪካውያን ባህሪ በሕክምና ማህበር ውስጥ በተግባር በመሳተፍ ጠንቅቀው ያወቃሉ። ስለባህሪያቸው ሲናገሩ በአንደኛ ደረጃ የአፍሪካ አህጉር ሁል ጊዜ ለእነሱ ተግባር የሚሆን ግብዓትና ጥሬ እቃ እንዲሰጥ ማድረግ እንደሚፈልጉ ይጠቅሳሉ። ሁለተኛ ፍላጎታቸው አፍሪካውያንን ከሌሎች ኃያላን መንግሥታት ጋር በሚያደርጉት ፉክክር ታዛዥ በማድረግ በቁጥጥራቸው ስር ውስጥ ለማዋልና ለማስተዳደር ይተጋሉ። ስለሆነም እነዚህን ሁለት ዓላማዎች የሚያስፈጽምላቸው ተባባሪ መንግሥት እስካገኙ ድረስ ይደግፋሉ በማለት ዋነኛ የሚባሉትን ባህሪዎቻቸውን ያስቀምጣሉ። በመቀጠልም፤ «ዶክተር ዐቢይ በኖቤል ሽልማት ላይ ያደረጉትን ንግግር በማዳመጥ ሽልማቱን የምትሰጠው ተወካይ ‹የምናገረው ነገር አሳጣኸኝ!› ነው ያለችው። ይሄ ሁሉ አድናቆት በእኛ ጭን ላይ አስቀምጠን የፈለግነውን ጉዳይ ሊያስፈጽምልን ይችላል የሚል ከፍተኛ እምነት የተካሄደ ነው። ዶክተር ዐቢይ ግን ነጮች ያላሰቡትን እና የማይፈልጉት ነገር ነው ያደረጉት። ‹ከማንም የውጭ ተጽዕኖ በመላቀቅ በነጻነት ሕዝቤን አምኜ የአገሬን ጥቅም ከሚያስጠብቅልኝ መንግሥት ይሁን ተቋም ጋር እተባበራለሁ፤ የማያስጠብቅ ከሆነ አልተባበርም› በማለት በተግባር መፈጸም ጀመሩ። ይህን በማድረጋቸውም አክርረውና አምረው ጠሏቸው። አሁንም ‹እርዳታ እናቆመዋለን፣ ማዕቀብ እንጥላለን› ብለው ማስፈራሪያና ዛቻ የሚያደርጉት ዶክተር ዐቢይን አብዛኛው ሕዝብ ስለደገፋቸው ፍላጎታቸው እንዲፈጸም ሊያስገድዱ የሚችሉት የመጨረሻ አማራጫቸው አሸባሪው ወያኔን አዲስ አበባ ማምጣት ሳይሆን እንደ ፖለቲካ

## ዶክተር ፍቅሩ የውጭ አገራትን ድጋፍ ለማግኘት መሪዎች ላይ ብቻ ማተኮር እንደማይገባ፣ የአውሮፓም ሆነ የአሜሪካ መሪዎች የሕዝባቸውን ድምጽ (ቁጣ) የሚሰሙ ስለሆነ ትኩረታችን ታክስ ከፋዩ ሕዝብ ላይም መሆን እንዳለበት ያሳስባሉ

ቡድን መደራደሪያ እንዲሆን ማቆም ነው። ይሄን ተግባር ለማስፈጸምና የኢትዮጵያን መንግሥት ለማንበርከክ የሚችሉትን ያህል ያደርጋሉ፤ እስከ ደም ጠብታ ድረስም ይታገላሉ። ይሄን ለመግታት ኢትዮጵያውያን ተባብረን መሥራት ይጠበቅብናል» በማለት ነጮች ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም በሰብዓዊ እርዳታ ሥም ብዙ ነገር ለማድረግ እንደሚጥሩ ያሳስባሉ።

ነጮቹ በሚያደርጉት ዛቻ መደናገጥ እንደማይገባ ሲያስረዱ፣ አንዱ ዛቻቸው “የኢኮኖሚ እቀባ እናደርጋለን” የሚል መሆኑን ገልጸው ኢትዮጵያ ስለምታስፈልጋቸው ላያደርጉት እንደሚችሉ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ። ቢያደርጉትም ይሄን ያህል የኢትዮጵያን ሁኔታ እንደማያናጋ ምሳሌ በመስጠት ሲያስረዱ የአሜሪካ እርዳታ ሰጪ ኃላፊ ስትናገር “የኢትዮጵያን ሰባት በመቶ ሕዝብ የምንመግበው እኛ ነን ብላለች” በማለት ጠቅሰው እሷ ያለችውን ይዘው መቶ ሚሊዮን ሕዝብ ነን ብለን ብንል አስር ሰው ለአንድ ሰው እርዳታ ቢያደርግ የአሜሪካ ምጽዋት አያስፈልገንም። ይሄን በተግባር ማሳየት ብንጀምር ኢትዮጵያን ማጣት የማይፈልጉበት ምክንያቶች ብዙ ስለሆኑ ጥንካሬያችንን እና ችግራችንን በራሳችን መፍታት መጀመራችንን ዐይተው ተመልሰው ወደ እኛ እንደሚመጡ ከባህሪያቸው በመነሳት እርግጠኛ ናቸው።


የራስን ችግር በራስ ለመፍታት በሚል ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ በቅንጅት ብዙ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ የሚጠቅሱት ዶክተር ፍቅሩ የዲያስፖራው ማሕበረሰብ እየሠራ ያለው ሥራ ቢኖርም በቂ እንዳልሆነ ይናገራሉ። ችግሮችን በራስ አቅም ለመፍታት የዲያስፖራው አባላት ሊያደርጉ የሚገባውን ተግባራት ሲገልጹ «ሶስት ሚሊዮን ዲያስፖራ አለ ይባላል። እያንዳንዱ አንድ መቶ ዶላር በወር ቢያዋጣ ሶስት መቶ ሚሊዮን ዶላር አገር ውስጥ ይገባል። ከሶስት ሚሊዮን ዲያስፖራ አንድ ሚሊዮኑ ብቻ አንድ መቶ ዶላር በወር ቢያዋጣ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር አገር ውስጥ ይገባል። ገንዘቡ አገር ውስጥ ሲገባ ብዙ ነገር ይሠራል። ይሄን ለማስፈጸም ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ በቅንጅት ማድረግ ይጠይቃል። ሁለትና ሶስት ዓመት ሊርበን ይችላል፤ እንደ አገር መቶ ዓመት ከመራብ ሶስት ዓመት ተርበን ዘጠና ሰባት ዓመት ለዘላቂነት ጠግበን ብንኖር ይሻላል። በደንብ ተቀናጅተን ከሠራን ተባብረን ይሄን የመከራና የችግር ጊዜ በዘላቂነት እንወጠዋለን» በማለት ያስረዳሉ።

በገንዘብ የሚደረግ ድጋፍ ዋነኛው እንደሆነ ጠቅሰው ሌላው ድጋፍ ሁለተኛና ሶስተኛ መሆኑን ይገልጻሉ። ፍላጎቱና ዓላማውን ተከትሎ ተነሳሽነቱ ከመጣ የህዳሴ ግድቡን በዲያስፖራ አባላት ብቻ ማጠናቀቅ ይቻላል ብለው ያምናሉ። ግድቡ ከድህነት ለመውጣት ከሚረዱ ነገሮች አንዱ መሆኑን፣ ግድቡ ሲጠናቀቅ በኢትዮጵያ ውስጥ መሠረታዊ ለውጥ እንደሚመጣ እንዲሁም ለምስራቅ አፍሪካ አገሮች ለውጥ ይዞ እንደሚመጣ ጠቅሰው ግብጽ አምርራ ግድቡ እንዳይሠራ የምትታገለን አንዱ ምክንያት እሷ የምትሸጠውን የኤሌትሪክ ኃይል ኢትዮጵያ መሸጥ ስለምትጀምር በኢኮኖሚ ዝቅ እንደምትል ስምታውቀው መሆኑን ይናገራሉ።

ዶክተር ፍቅሩ የውጭ አገራትን ድጋፍ ለማግኘት መሪዎች ላይ ብቻ ማተኮር እንደማይገባ፣ የአውሮፓም ሆነ የአሜሪካ መሪዎች የሕዝባቸውን ድምጽ (ቁጣ) የሚሰሙ ስለሆነ ትኩረታችን ታክስ ከፋዩ ሕዝብ ላይም መሆን እንዳለበት ያሳስባሉ። ታክስ ለሚከፍለው ሕዝብ ያለውን በደል በማሳወቅና በማስረዳት ለኢትዮጵያ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባ መንግሥታቸውን እንዲያሳስቡና ጫና እንዲፈጥሩ ማድረግ አንደኛው የትኩረት አቅጣጫ መሆን እንደሚገባው ይገልጻሉ። በእስር ላይ በነበሩበት ወቅት በእሳቸው ላይ ተደራራቢ በደል ሲደርስ ስዊድን አገር ስለተከናወነው እንቅስቃሴ ሲናገሩ «በእኔ መታሰር ጉዳይ ላይ ታክስ የሚከፍለው ሕዝብ ባደረገው መነሳሳትና ተጋድሎ መንግሥት ላይ ጫና በመፍጠር የስዊድን መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ከኢትዮጵያ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር በመነጋገር ብዙ ነገር ሊደረግ ችሏል። እንዲህ አይነት ተግባራት ለማከናወን የኢትዮጵያ መንግሥት የመከላከያውን እና የደህንነት ተቋሙን በተሻለ መልኩ በአዲስ መልክ አጥርቶ እንዳደራጀው ሁሉ ዲፕሎማሲው ውስጥ ተሰግስገው ያሉትን የአሸባሪው ወያኔ ደጋፊዎችን ከሕዝቡ ጋር በመመካከር ማጥራት ይኖርበታል» በማለት የዲፕሎማሲው ተቋም ሊፈተሽና ሊስተካከል እንደሚገባ ምክረ ሀሳብ ይሰጣሉ።

የኢትዮጵያን የሶስት ዓመቱን የለውጥ አጀማመርና ሂደትን ሲያስረዱ ምናልባት ቻይና ውስጥ ታይቶ ሊሆን ይችላል እንጂ ሌላ ቦታ ታይቶ እንደማያውቅ ይናገራሉ። ይህ የለውጥ ሂደት እመርታ ያሳያል እንጂ አንዳችም መቀልበስ ይደርስበታል ብለው እንደማያስቡና አንዳንድ ቦታ ከተገቢው በላይ የፈጠነበት ሁኔታ እንዳለ ይገልጻሉ። በአጠቃላይ የለውጡ ሂደት ሲታይ የሚፈለገውን ያህል በቂ እንዳልሆነ ፣ ሥር ነቀል ለውጥ የሚያስፈልጋቸው ቦታዎች እንዳሉም ያሳስባሉ። ለእነዚህ ጉድለቶች ምክንያቶቹ ሲነሱ ክህሎቱና አቅሙ ሁሉ የተዘጋጀ ነበር ወይ ? ብሎ በመጠየቅ በአግባቡ ምላሽ ማግኘት እንደሚገባ እንዲሁም ያሉትን ችግሮች ማጉላትና ማናፈስ ሳይሆን ከሚመለከተው ተቋም ጋር በመሆን ዕውቀት ባለው ሁኔታ ማስረዳትና እንዲስተካከል መታገል ከሁሉም ዜጋ እንሚጠበቅ ያስገነዝባሉ።

ዶክተር ፍቅሩ ስለስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ አስተያየታቸውን ሲሰጡ «ምርጫው ከዲሞክራሲያዊነቱ አንጻር ሲታይ ኢትዮጵያ ውስጥ ተደርጎ የማይታወቅ ነው። አውሮፓም አሜሪካም ውስጥ ምርጫን በተመለከተ ተከታትያለሁ። እነሱ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተደረገ ብለው ከሚያወድሷቸው አገሮች ጋር አሁን በኢትዮጵያ የተደረገው ምርጫ ባይበልጥ እንኳን አይተናነስም። እንደእኔ አረዳድ በግልጽ ለመነጋገር ሕዝቡ የብልጽግናን ፓርቲ መረጠ አልልም። ብዙ ሰዎች ጠይቄአለሁ ‹ዶክተር ዐቢይን መርጬ መጣሁ› ነው የሚሉት። እኔ እስር ቤት ሆኜ ዶክተር ዐቢይ ፓርላማ ያደረጉትን የመጀመሪያ ንግግር አድምጬ እግዚአብሔር ሙሴን ለእስራኤል እንደላከው ሁሉ ዶክተር ዐቢይን ለኢትዮጵያ ልኮላታል ብዬ ጮክ ብዬ ተናግሬአለሁ። በንግግር ብቻ ሳይሆን በተግባር በዚህ አጭር ጊዜ ብዙ ሥራ በመሥራት አሳይተዋል። በሚሠሯቸው ሥራዎች ውስጥ ችግር




ካሳተሙት መጽሐፍ ጋር

ሊኖር ይችላል፤ እንደማንኛውም ሰው ሊሳሳቱ ይችላሉ። የሚያስተካክሉበትን መንገድ ማሳየትና ማገዝ ከሁላችንም ይጠበቃል። የብልጽግና ፓርቲ አባላት ደግሞ የዶክተር ዐቢይ ደጋፊና ረዳት መሆን አለባቸው። ብልጽግና ፓርቲ አሸንፏል ብሎ መሞኘት አይገባም። የፓርቲ ነገር ቢሆን ኖሮ በተፎካካሪነት ያሉት ብዙ ድምጽ ያገኙ ነበር። ሕዝቡ ዶክተር ዐቢይ ላይ እምነት አለው። ብልጽግና ፓርቲ የሚሠራው ስህተት ሁሉ መስተካከል ካልታየበት ‹ዶክተር ዐቢይ ነው የሠሩት› ብሎ በመቀየም ዛሬ እንደመረጠው ሁሉ ነገ ሕዝቡ ሊቀጣ ይችላል። ስለሆነም የብልጽግና ፓርቲ አመራር በከፍተኛ ደረጃ አስበው መምራትና ማስተዳደር ይገባቸዋል» በማለት ያሳስባሉ።

ዶክተር ፍቅሩ አዲስ የተመረጠው መንግሥት ይሠራቸዋል ብለው የሚጠብቁት ዋና ተግባራትን ሲናገሩ «ከዚህ መንግሥት የምጠብቀው አንዱ ትልቅ ጉዳይ የኢኮኖሚ ተግዳሮት የሚባሉትን ጉምሩክ፣ ገቢዎች እና የታክስ ስርዓቱ እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች ያሉት ማነቆዎች እንዲፈታ ነው። ምክንያቱም የኢኮኖሚ ተግዳሮት ካልተፈታ የኢኮኖሚ እድገት የሚባለው አይመጣም። ኢኮኖሚው ካላደገ ደግሞ ፖለቲካውን ተሸክሞ መሄድ አይኖርም። ሌላው የምጠብቀው ትልቅ ጉዳይ ለሃያ እና ሰላሳ ዓመታት በዘቀጠ የትምህርት ሥርዓት ስለታለፈ በተለይ ወጣቱን በትምህርትና ስልጠና ትኩረት ሰጥቶ የማደስ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ ሌላው ትልቅ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ደኅንነቱ መጠበቅ አለበት። በአሸባሪው ወያኔ ጊዜ እንደነበረው የቡድን መብት ወይም የፓርቲ መብት እየተባለ የሚሄድ ከሆነ የግለሰብ መብት እስከተረገጠ ድረስ ደኅንነት አይኖርም። መንግሥት የግል መብት ሳያረጋግጥ የቡድን መብት ያረጋግጣል ከተባለ መፈናፈኛ አይኖርም። ስለዚህ እያንዳንዱ የዜግነት መብቱ እንዲጠበቅለት በማድረግ ግለሰቡም መብቱን እንዲያስጠብቅ ተባባሪ ማድረግ ይገባል። የፍትሕ አካላት ደግሞ መብቱ እንዲከበርለት ኢጋዦች ይሆናሉ» በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

እንግዳችን ከሁሉም በላይ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት በሰሜን በኩል ያለው ስቃይና እንግልት እንዲሁም ጥፋት መቆም አለበት ብለው እንደሚያምኑ ይናገራሉ። የሰሜኑ ችግር ሲቀረፍ በሌሎች አካባቢም ያሉ ችግሮች አብረው እንደሚቀረፉ ይገልጻሉ። ስለሆነም የአሸባሪው ወያኔ ጉዳይ በወታደራዊም ሆነ በሌላ መልኩ በአጭር ጊዜ ከተጠናቀቀ በእሱ ድጋፍ የሚተነፍሱና የሚንቀሳቀሱ እንደ ሸኔ አይነቶቹ ምንጫቸው ስለሚደርቅና ስለሚዘጋ የእነሱም ጉዳይ በዚያው እንደሚጠናቀቅ ይገልጻሉ። በመንግሥት ውስጥ ተሰግስገው ያሉ ለአሸባሪው ወያኔ የሚደግፉትም መጋረጃው ስለሚገለጥ መጋለጣቸው እንደማይቀር ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ አሜሪካ ለአፍሪካ አገራት ከሰጠችው ከቀረጥ ነጻ ንግድ ማበረታቻ ዕድል (አጎዋ) ተጠቃሚነት እንድትወጣ ግፊት ለሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን አስተያየት ሲሰጡ በእስር በነበሩ ጊዜ ተደጋጋሚ በደል ቢፈጸምባቸውም (በቅድሚያ ከተከሰሱበት በተጨማሪ እሳቸው ሆስፒታል ተኝተው በነበሩበት ወቅት እስር ቤቱ በመቃጠሉ እሳቸው ቃጠሎውን አስተባብረዋል በሚል ሌላ ክስ ተመስርቶባቸው በዚህም በደል ደርሶባቸው ነበር) እሳቸው ላይ በደረሰው በደል የተነሳ የስዊድን መንግሥት ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን እርዳታ አንድም ሳንቲም ቢሆን እንዳያቋርጥ በልጃቸው በኩል በተደጋጋሚ ሲጠይቁና ሲያሳስቡ እንደነበረ በማስታወስ ይጀምራሉ። በመቀጠልም ለኢትዮጵያ የሚሰጥ ዕርዳታ በተለይ ውጪ ያሉት ዲያስፖራዎች ለመንግሥት ባለስሥልጣናት የሚደርስ ይመስላቸዋል ፤ ዕርዳታ ሲቀር የሚራበው፣ የሚሰቃየው፣ እንዲሁም ችግሩን የሚሸከመው ዕርዳታው የሚደርሰው ወገን ነው። ስለዚህ ዕርዳታ እንዲቀር የሚደረግ የትግል ዘዴ መንግሥት ከያዘው አቋም አንድ ሴንቲሜትር ወደ ኋላ የሚያደርገው እንዳልሆነ ይናገራሉ። አጎዋን በተመለከተ የአሜሪካ መንግሥት የፈቀደው ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ትናንሽ አምራቾች እንዲጠቀሙ ታስቦ አብዛኛውን መካከለኛና ደሃ ሕዝቦች የሚጠቀሙበት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ዶክተር ዐቢይ ወይም ሚኒስትሮች የሚጠቀሙበት አይደለም። ስለሆነም አጎዋ ቢቀር መንግሥትን የሚጎዳ እንዳልሆነ ተገንዝበን በተለይ ውጭ ያሉ ዲያስፖራዎች ዜግነታቸውን ተጠቅመው ለአሜሪካ ሕዝብ፣ ለሴኔት እና ለኮንግረስ ሰዎች ድሃው ሕዝብ ተጎጂ እንደሚሆን ማሳወቅ ይገባቸዋል ብለዋል።

ዶክተር ፍቅሩ ከእስር ከተፈቱ በኋላ «የበደለኝ ሥርዓት እንጂ አገሬ ወይም ሕዝብ አይደለም» በማለት ከሁለት ሳምንት የውጭ አገር ቆይታ በኋላ እሳቸው የተሳተፉበት ከፍተኛ የልብ ስፔሻሊስቶች ቡድን እየመሩ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ኢትዮጵያውያን የልብ ሕመምተኞች እገዛ እንዲያገኙ አድርገዋል። እሳቸው የዚህን ያህል ጥረት የሚያደርጉ ቢሆንም በተለይ ዩቲዩብ ከፍተው ተደራጅተው ሰበር ዜና እያሉ የኢትዮጵያ ሕዝብን መከራ እንዲቀጥል የሚያደርጉ አካላት መኖራቸውን በመጥቀስ አስተያየት ሲሰጡ «ለኢትዮጵያውያን በጣም አበክሬ የምናገረው እባካችሁ የእነዚህን አካላት ዩቲዩብ ምንም አይነት ሰበር ዜና አለ ቢሉ አትክፈቱ። የምትከፍቱ ከሆነ የእነሱን ተመልካች ቁጥር ስለምታብዙ ስፖንሰር የሚያደርጋቸው አካል ብዙ ሰው ይከታተላቸዋል በሚል ገንዘብ ስለሚሰጣቸው ወሬ እየፈጠሩ ይቀጥላሉ። በመክፈት አናብዛቸው፤ ዝም በማለት እንቅጣቸው እላለሁ። ስለኢትዮጵያ በጎ የሚያስቡትን በመከታተል መርጦ መረጃ ማግኘት ይቻላል» በማለት ስለሚዲያ አጠቃቀም የሚታየው ልምድ መስተካከል እንደሚገባው አበክረው ይመክራሉ።

በእስር ላይ በነበሩ ጊዜ በድብቅ ማስታወሻ እያስወጡ እንዲቀመጥ ሲያስደርጉ ቆይተው ከእስር ከተፈቱ በኋላ ስዊድን ከሚገኝ ጋዜጠኛ ጋር በመተባበር በስዊድን ቋንቋ “አምስት ዓመት በእስር” የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍ አሳትመዋል። ብዙ አንባቢ ስላገኘ ወደ ፊልም ሊቀየር እንደሆነ እንዲሁም ወደ እንግሊዘኛና አማርኛ ተተርጉሞ በቅርቡ አንባቢ እጅ እንደሚደርስ ነግረውናል። ከዚህ በተጨማሪ አዲስ የልብ ሕክምና ማዕከልና እህት ድርጅቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ልብና ልብነክ የሆኑ በሽታዎችን ከማገዝ አንጻር ምን አይነት አገልግሎት እንደሰጡ እንዲሁም ሐኪሞች እንዴት እንደሰለጠኑ በመጽሐፍና በፊልም የማሳየት ዕቅድ አላቸው።

በመጨረሻም ኢትዮጵያ ብለው ለተነሱት ዕድሜና ጤና እንዲሰጣቸው በመመኘት ስለኢትዮጵያ የሚታያቸው ተስፋ ብቻ አለመሆኑን እና ሕዝቡ ከዚህ አስቸጋሪ ኑሮ ወጥቶ አገሩን ጠንካራ የአፍሪካ መሪ አገር እንደሚያደርጋት እርግጠኛ መሆናቸውን ይገልጻሉ። «ከሕዝቡም ሆነ ከሌላው ወገን የማየው ከእነጉድለቱ እየተሄደበት ያለው አካሄድ በትክክለኛው መስመር ላይ እንደሆነና ከፍተኛ ደረጃ የሚያደርስ መሆኑን እንዳይ አድርጎኛል። ለዚህ መስመር ቀጣይነት ከእኔቤተሰቤ በዕውቀትም ሆነ በገንዘብ አስተዋጽኦ አደርጋለሁ» ሲሉም ለኢትዮጵያ መጪው ጊዜ ብሩህ እንደሆነ ይናገራሉ።



# የተዘነጋው የፑሽኪን ሐውልት



**በሥነ-ራእይ ሥራ መሪ ብርሃኑ ሽብሩ**

የአስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሩሲያውያን ረቂቅ ሥነ-ጽሑፍ ከሳችና የዘመናዊ ሥነ-ጽሑፍ ቋንቋ ፈልሳፊ ታላቁ የጥበብ ሰው አሌክሳንደር ሰርጌቪች ፑሽኪን የተወለደው እ.ኤ.አ. ሐሙስ ሰኔ 6 ቀን 1799 ዓ.ም ነው። ትውልዱ ከዘመኑ ባላባቶች እና ምሁራን ቤተሰብ ነበር። በ12 ዓመቱም በፔተርስቡርግ ከተማ አጠገብ በዛርስኮይ ሴሎ ውስጥ በሚገኘው በተከበረው የመሳፍንት ልጆች ትምህርት ቤት ገብቷል። በ15 ዓመቱ ግጥሞችን መጻፍ የጀመረው ፑሽኪን በ18 ዓመቱ የ12ኛ ክፍል ትምህርቱን አጠናቋል። በሩሲያ ቋንቋና ግጥሞች ላይ አስተውሎት እንዲያዳብር እና የሩሲያን ባሕላዊ ልማዶች ፣ እምነቶች፣ አፈ-ታሪኮች፣ አገርኛ ተረቶች እና ዜማዎች በመረዳት ጥበባዊ ምናቡ እንዲሰፋ ያስቻሉት ገጠር በገባርነት ይኖሩ የነበሩት የሦስት ልጆች እናት ወይዘሮ አሪና ሮዲኦኖቭ እና ሞግዚቱ ነበሩ።

አሌክሳንደር ፑሽኪን ለወይዘሮ አሪና እ.ኤ.አ. በ1856 በጻፈው «ሞግዚቴ» ግጥሙ አክብሮቱን ገልጦላቸዋል። ዛሬ ወይዘሮ አሪና ሮዲኦኖቭና ፑሽኪን ለሩሲያ አገርኛ ጥበብ ዕድገት ለዋሉት ውለታ «የሩሲያ ምግዚት» የሚል ታሪካዊ ስያሜ ተሰጥቷቸው ሐውልቶች ቆመውላቸዋል ፤ እና አደባባዮች ተሰይመውላቸዋል።

በትምህርት ቤት ዘመኑ ለታላላቅ ሰዎች፣ አገረ ገዢዎች፣ የንጉሡ አገልጋዮች እና ደራሲያች ይዘጋጅ በነበረው የልጆች ክህሎት ማቅረቢያ የትርኢት መርሐግብር ላይ ይሳተፍ ነበር። የሰብአዊ ነጻነት ጥልቅ ሃሳብ የዘለቀበትን እና በምናብ ንዝረት የመጠቀ እሳቤ የሚገለጥበትን የፈጠራ ጽሑፍ ሀተታውን እንዲሁም የመድረክ ዕይታውን እና የትረካውን ወግ ልቆ መገኘት የትምህርት ቤት ጓደኞቹና መምህራኖቹ ይመሰክሩለታል።

በልጅነቱ በቤታቸው በነበረው የአባቱ ግዙፍ ቤተመጽሐፍት በፈረንሳይ ቋንቋዎች የተጻፉ መጽሐፎች የሞሉበት ስለነበርና በመሳፍንቱም ዘንድ የተለመደው መነጋገሪያ ቋንቋም ፈረንሳይኛ ስለነበር ፑሽኪን በፈረንሳይኛ ቋንቋ ንባብ ፣ ንግግር እና ጽሑፍ ብቃቱ የተነገረለት ነበር።

የዚያን ዘመኑ ፑሽኪን የልጅ አዋቂነቱንና የወደፊት ታላቅነቱን በግለታሪክ ድራማ የኪነጥበብ ወግ በሩሲያ የሥነ-ጥበብ ራዕይ (ፊልም) ተዘጋጅቶ ለመጀመሪያ ጊዜ እ.ኤ.አ. እሮብ የካቲት 10 ቀን 1937 ዓ.ም በፔተርስቡርግ ለሕዝብ ቀርቧል። «የገጣሚው ወጣትነት» በሚል ርዕስ የተሰናዳውና 85 ደቂቃዎች የሚረዝመው ጥቁርና ነጭ ተንቀሳቃሽ ሥዕል በአብራም ናሮድቸስኪ (1906-2000 እ.ኤ.አ.) አዘጋጅነት በሌን ፊልም ኢንዱስትሪ የተመረተ ነው። ስራው በፑሽኪን 100ኛ የሙት ዓመት ላይ መቅረቡ መነሻ ሆኖ እስከዛሬም የፑሽኪን የጥበብ ሥራዎች ታሪካዊ ወግ በተንቀሳቃሽ ምስሎች እየተሠሩ ይገኛሉ።

በሩሲያ ሥነ-ጽሑፍ ረጃጅምና አጫጭር ተውኔታዊ ግጥሞች ፣ ሙዚቃዎች ፣ ኦፔራ እና ባሌት ውዝዋዜዎች በምርምር የተሳተፉ ከሁሉም አህጉራት የተወጣጡ ባለሙያዎች በፑሽኪን ሥነ-ግጥሞች ልሳኖቻቸውን አሟስተዋል። እንደምሳሌ ፑሽኪን እ.ኤ.አ. 1829 ጽፎት በ1830 ለሕትመት የበቃው ከአስር መስመሮች የማይበልጠው «አፈቅርዎት ነበር» የተሰኘ ግጥሙ የፑሽኪን ሐውልቶች በቆሙባቸው አገራት፤ በተለይ የኪነ-ጥበባት ደቀመዛሙርት፤ በተመስጦ መድረክ የሥነ-ግጥም ድምጻቸውን የሚያፍታቱበት የወጣት ትውልድ የክላሲካል ሥራዎች ከበሬታ ማስተዋያ ሥጦታ ሆኖ ይኖራል። ለዚህ ግጥም የ19ኛው ክፍለ ዘመን የሩሲያ ክላሲካል ሙዚቃ ደራሲ እና አዘጋጅ ሞክሼው አሌክሳንደር ሴርጌቪች ዳርጎሚዥስኪ (1813-1869 እ.ኤ.አ.) እ.ኤ.አ. በ1830ዎቹ መጀመሪያ ሙዚቃዊ ድርሰት ፈጥሮለት ለትውልድ ይተላለፍ ዘንድ አዘጋጅቶለታል።

በፑሽኪን ረገኘም ግጥሞች ላይ በመመስረት ታላላቅ የሙዚቃና ኦፔራ ደራሲዎች እና አዘጋጆች በቴያትር አስገራሚ ትርዒቶች ያቀርቡ ነበር። እስከዛሬም በዓለም ኦፔራዎች የሚያስተጋቡት «የቭጌኒ ኦኔጊን» በታላቁ የሙዚቃ ክላሲክ ደራሲ ኢሊየች ቻይኮቭስኪ (1840-1890 እ.ኤ.አ.) ሥራዎች እንደ አብነት ሆኖ እ.ኤ.አ. ከ1878 ጀምሮ በኦፔራዎች የሚጠቀስ ነው። እ.ኤ.አ. በ1830 ፑሽኪን የጻፈው ታሪካዊ ተውኔት «ቦሪስ ጎዱኖቭ» በክላሲካል ሙዚቃ ደራሲው ሞደስት ሙሰርግስኪ (1839-1881 እ.ኤ.አ.) ለኦፔራ እና ለባሌት ተጽፎ እ.ኤ.አ. በ1874 ለሕዝብ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በዘመናት ሽግግር በየጊዜው ለትውልድ እየቀረበ ያለ ነው።

የ«ቦሪስ ጎዱኖቭ» ተውኔት፤ ኦፔራ እና ባሌት እ.ኤ.አ. በ1954 በሥነ-ራዕይ ጥበብ ሥራ መሪዋ ቬራ መሪዎ ስትሮየቫ ()1903-1991 እ.ኤ.አ.) ባለ 110 ደቂቃ ርዝመት ያለው ተንቀሳቃሽ ሥዕል ለመጀመሪያ ጊዜ ተሠርቶ ከቀረበ በኋላም ይኸው የፑሽኪን ታሪካዊ ድራማ ጽሑፍ «ቦሪስ ጎዳኖቭ» እ.ኤ.አ. በ1986 በሥነ-ራዕይ ሥራ መሪነት፣ በጽሐፊነት እና በመሪ ተዋናይነት ሴርጌ ባንዳርቹክ (እ.ኤ.አ. 1920-1994) ባለ 141 ደቂቃ ርዝመት ሥነ -ራዕይ አዘጋጅተው አቅርበውታል። ዛሬም በአሌክሳንደር ፑሽኪን ትረካዎች ላይ



መሠረተ ተውኔት እየተጻፈባቸው በሥዕለ ድምፅ (ቴሌቪዥን) የሚቀርቡ ሥራዎች እንደቀጠሉ ናቸው።

ፑሽኪን ትምህርቱን ባጠናቀቀበት ዘመን በፔተርስቡርግ ከተማ እንደ ወጉ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ እየሠራ አገሩን አገልግሏል። በርካታ ግጥሞችን ፣ ታሪካዊ ተውኔቶችን እና መጻሕፍትን ሲጽፍም ቆይቷል። በሕትመት ቅድመ ምርመራ የታገዱ ጹሑፎቹም ነበሩ። እስብታቸውም የንጉሡን ሥርዐት የሚቃወሙ ናቸው በማለት እየተነቀፉ ሲሆን በዚያም ሳቢያ ከፅኑ ቅጣት ይድን የነበረው በሚወዱት ባለሥልጣናት ድጋፍ ነበር።

ፑሺኪን በንጉሡ ትእዛዝ በግዞት ይላክባቸው በነበሩት ሥፍራዎች ሁሉ ለሥነ-ጽሑፍ የፈጠራ ሥራውዎ እጅግ ተፈጥሯዊ የስልሳሌ ግብአት እየሰጠው ያልፍ ነበር። ከሥራውም በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ በወሰነበት ወቅት በሩሲያ በሚገኘው በሴት አያቱ ርስት ፕስኮቭ እንዲኖር ተወስኖበት ቆይቷል።

ፑሽኪን አዋቂ እና ታዋቂ ሆኖ በግጥሙ እና በሥነጽሑፍ ዘመኑን ሲያስደምም ፤ በቤተ መንግሥቱ ተቀባይነት በማግኘቱ የትዳር አጋሩን ናታሊያ ፑሽኪንን አግብቶ በፒተርስቡርግ ቤተ መንግሥት ግቢ ልጆችም ወልደው ይኖሩ ነበር። ናታሊ (1812-1863 እ.ኤ.አ.) በውበቷ ወደር የሌላት ቆንጆ ተብላ በመልካምም ባሕርይዋ ፑሽኪንም በዕውቀቱ እና በታላቅ ተግባሩ ይደነቁ በነበረበት ወቅት ፤ እጅግ በጣም የሚቀኑባቸውም ክፉዎች ግለሰቦችም ነበሩ። ነገር አዋሳጆችም ናታሪያ ቆንጂት የተባለላትን በወቅቱ ለሩሲያ መንግሥት ያገለግል የነበረው የፈረንሳይ የጦር መኮንን ደ አንቴስ (እ.ኤ.አ. 1812-1895) እቁባቱ እንደሆነች ከሹክሹክታ ባለፈ በምንም እና በማንም ያልተረጋገጠ አሉባልታ የያዘ ደብዳቤ ካልታወቀ ተንኮለኛ ሰው ካልተጠቀሰ አድራሻ ለፑሽኪን ይደርሰዋል።

በዚያ አሳዛኝ የቤተመንግሥት ውስጠ ዙሪያ ሤራ አሌክሳንደር ፑሽኪን ስለክብሩ መነካት የሽጉጥ ፍልሚያ እንደሚጠይቅ በዘመኑ ሥርዐት ተጠባቂ ነበር። ከጦር መኮንኑ ደ አንቴስም ጋር ሲፋለሙ እ.ኤ.አ. እሑድ ጥር 29 ቀን 1837 በጽኑ ቆስሎ እጅግ በርካታ ወዳጆቹ አክባሪዎቹ በከፍተኛ ሐዘን ተሰባስበው እንደቆዘሙ ብዕር ሲያፍተለትሉ የኖሩት የአሌክሳንደር ጣቶች በክር ታሠሩ። በሥጋም ማረፉ በአገሩ ተስተጋባ።

አሌክሳንደር ፑሽኪን በፍልሚያ ከወደቀባት ሥፍራ ዛሬ ከሚታየው የማስታወሻ ሐውልት ጀምሮ ዛሬም በዓለም ዙሪያ አደባባዮች እና ሐውልቶች የቅርስ ወግ እና የኪነ ጥበብ ታሪክ ምልክት ሆነው ይኖራሉ። የቆንጂቱና አስደማሚዋ ሚስቱ ናታሊያ እና የፑሽኪን አብሮነት ወግ መታሰቢያ ሐውልቶች በቆሙባቸው አደባባዮች ላይ ሁሉ ትውልድን በስልሳሌ ትኩረቱን ሲማርኩት ይኖራሉ።

የታላቁ ገጣሚ አሌክሳንድ ፑሽኪን ታሪኩና የጥበብ ሥራዎቹ ለትውልድ ታሳቢ ሆነው እንዲኖሩ ዓለም አቀፍ እውቅና የተሰጣቸው የተለያዩ ሐውልቶች ዛሬም ድረስ በዓለም የተለያዩ ከተሞች እየተተከሉ ይመረቃሉ። አብዛኛዎቹም ሐውልቶች ከሩሲያ መንግሥት ወይም ከሩሲያ ደራሲያን ማኅበር በሥጦታ የተበረከቱ እና የሚሰጡ ናቸው።

ሕዳር 10 ቀን 1995 ዓ.ም የአሌክሳደር ፑሽኪን ከደረት በላይ የተቀረጸው ሐውልቱ በአዲስ አበባ ሣር ቤት ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ቆሞ ጎዳናውም በስሙ ተሰይሞለት ነበር። በወቅቱ የኢፌዲሪ የወጣቶች ስፖርትና የባሕል ሚኒስትር የነበሩት አምባሳደር ተሾመ ቶጋ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ከንቲባ አቶ ዓሊ አብዶ፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ተገኝተው ነበር።

በሥነ ሥርዓቱ የክብር እንግዳ በወቅቱ የሞስኮ ከተማ ምክርቤት ተጠሪ ቪ..አይ. ሚሊሽኮቭ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር ለክፍለ ዘመናት ጸንቶ የቆየው የሁለቱ አገሮች ታሪካዊ ወዳጅነት በአሁኑ ጊዜም በሞስኮ እና በአዲስ አበባ መካከል በሚደረጉ የትብብር ሥራዎች ቀጣይ በምጣኔ ሀብት ፣ በንግድ፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ በሥነፍጥረት ምርምር፣ በትምህርት፣ በባሕልና ቱሪዝም በጋራ ለመሥራት እንደሚያስችሉ ጠቅሰው ነበር።

የፑሽኪን ሐውልት በመዲናችን አዲስ አበባ ተመርቆ ሲቆም በዓለም ላይ በተለያዩ ጊዜያት ተመርቀው ከቆሙት 294 ከሚደርሱ መታሰቢያ ሐውልቶች ለአፍሪቃ የመጀመሪያው እንደነበር ይታወቃል። ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ከተማችን የሚከናወነው የመንገዶችና እና የመሠረተ ልማት ግንባታ የፑሽኪን አደባባይ በሚገኝበት ሳርቤት አካባቢም በመቀጠሉ ምክንያት የፑሽኪን ሐውልት ከአደባባዩ ተነስቶ ቅርሶች በአደራ በሚቀመጡበት በቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን እንዲቆይ ለብሔራዊ ቤተመዘክር ተሰጥቶ ለዕይታ ቆሞ ቆይቷል። በመስከረም ወር 2007 ዓ.ም የፑሽኪን አደባባይ እና ጎዳና የግንባታው ሥራ መጠናቀቁን ተከትሎ አደባባዩን የሚመጥን ባለ 11 ሜትር ሙሉ ቁመና ያለው የፑሽኪን አዲስ ሐውልት ታንፆ ከሞስኮ ለአዲስ አበባ በሥጦታ ሊበረከት መዘጋጀቱን ፤ የማጓጓዣው ዝግጅት ጉዳይ ላይ ውይይት እየተደረገ እንደሆነና በቅርብ እንደሚመጣ ተገልጾ እንደነበር ይታወቃል።

በዚያ አጋጣሚም የወቅቱ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሴርጌይ ላቭሮቭ በአዲስ አበባ እና በአፍሪካ ሕብረት ለሥራ ጉብኝት መጥተው ስለነበር ጉዳዩም በኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ





ሚኒስቴር ይፋዊ መግለጫ ተሰጥቶበት እንደነበር በዓለም የመገናኛ ብዙኃን ተሰራጭቷል። የፑሽኪንም አደባባይ ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት ላይ ሲውል በታሪካዊው ቅርስ ፊንታ በማይገባ እና ወጉም ባልሆነ መልኩ ቦታው በንግድ ተወሯል።

የአሌክሳንደር ፑሽኪንን ሐውልት ከሞስኮ የመረከቡ አካሄድ የመዘግየቱ ሰበብ ግልጽ ባለመሆኑ በዚያው የሹክሹክታ ወግ የመደመጡ ሁኔታ በወቅቱ በአስመራና በአዲስ አበባ ባለሥልጣናት መካከል በእጅጉ ሻክሮ በነበረው የዠርዐ-ነገር ግንኙነት ብሎም የፑሽኪን ሙሉ ቁመናው የሚታይበት ሐውልት በአስመራ ከተማ መመረቁ በአዲስ አበባ ባለሥልጣናት ዘንድ ኩርፊያ አንግሦ ጉዳዩን በቸልታ የማረሳሳት ወግ ሸፈነው።

በየዓመቱ በሚከበረው የፑሽኪን ልደት መታሰቢያ በአዲስ አበባ በሩሲያ ሳይንስና ባሕል ማዕከል በፑሽኪን አዳራሽ የውይይት መድረክ ላይ የፑሽኪን ባለሙሉ ቁመና አዲስ ሐውልት ከሞስኮ በሥጦታ የሚበረከት ነው በተባለው መሠረት ተጓጉዞ በአደባባዩ ላይ እንዲቆም ባነሳሁት ሃሳብ ላይ የወቅቱ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ፕሬዚዳንት ‹‹… በእኛ በኢትዮጵያዊያን በራሳችን ሠዓሊዎችና ቀራጺዎች ሐውልቱን ለማሠራት የውድድር ጥሪ ዕቅድ ይዘጋጃል …›› የሚል ከዕውነታው የራቀ መግለጫ ተሰጠ። ዛሬም ዓመታት አልፈው የመግለጫቸውን ምሥል እና ድምፅ ሳስተውል በዐይነ ኅሊናዬ ንግርት የቀረበው ወግ የትዝብት ፈገግታ ያጭርብኛል። ምክንያቱም በወቅቱ የፑሽኪንን ሙሉ ቁመና በመዳብ ወይም በነሐስ ወ.ዘ.ተ ገንብቶ ለማቆም፤ የውድድር ጥሪ ለማድረግ ማንኛውም የመንግሥትም ይሁን የግል ድርጅት ዕቅድ አልነበረውም።

ይሁን እንጂ ትክክለኛው የሞስኮ እና የአዲስ አበባ ዕቅድ የአሌክሳንደር ፑሽኪን የሐውልት ርክክብ ጉዳይ ተራማጅ ሃሳብ ይጠብቁ ለነበሩት በወቅቱ ውይይቱን ለፈቀዱልን የሳይንስና የባሕል ማዕከሉ ሥራ መሪ ቭያችስላቭ አሌክሳንደር ኮኒክ የነበረውን እስብት ያለምንም መሸፋፈን ቅሬታ በሸፈነው ፈገግታ ማስረዳት ነበረብኝ። በወቅቱ የኔ እስብታ ትንታኔ ሌሎች አገራት ያደረጉት እንደነበርና እያደረጉም እንደሚታየው ሥጦታውን በጸጋ ተቀብሎ በአደባባዩ ላይ ለታሪክ ማቆም ፤ በዚያም የጥበብ ሥራ ተነሳሽነትን በማበልፀግ ቅርስና ባሕልን በማጥናት የምርምርንም ተሞክሮ ለመጪው ትውልድ ትሩፋት ለማድረግ ነበር።

የፑሽኪን ሐውልቶች እና አደባባዮች የሚታዩባቸውን ሌሎች አገራት እንደ አብነት ለመጥቀስ ያህል በቻይና ዩዬ አንግሉ ፣ በሜክሲኮ በጀርዲን ቱሽኪን መናፈሻ ፣ በቤላሩስ፣ በብራስልስ፣ ቤልጂየም፣ ዋሺንግተን ዲሲ፣ በጃክሰን ኒውጀርሲ እንዲሁም ሞንሮይ ኒዮርክ ፣ በግሪክ እና በቡልጋርያ ይገኛሉ። በተለየ ሁኔታ ደግሞ ስድሳ የሚሆኑ የፑሽኪን ሐውልቶች በዩክሬይን የተለያዩ ከተሞች እና አደባባዮች ላይ ይገኛሉ። 140 በአይነታቸው የተለያዩ ጥበባዊ አቋም እና ይዘት ያሏቸው የፑሽኪን ሐውልቶች በሩሲያ የተለያዩ ከተሞች አደባባዮች ላይ ቆመው ትውልድን በጥበብ ታሪክ ወግ እያስደመሙ ይገኛሉ።

ለዚህ ጽሑፌ ማጠቃለያ ለመድረስ የሚቀረኝ እስብታ፤ በሥነ ጥበብ ውጤቶች አስተውሎ ማለፉ ነው። ይኸውም ፑሽኪን ‹‹የራስ ምሥል›› ብሎ ከሠራቸው እና በግጥሞቹ የፈጠራ ተመስጦ ውስጥ ሲመላለስ በንድፍ ሥዕል ካኖራቸው አሻራዎቹ በየድርሰቶቹ እና ግጥሞቹ ውስጥ ተሰንደው መገኘታቸውን እና በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዓለም የሥነጥበብ ዘርፍ በአድናቆት ከሚነገርላቸው ከሃያ በላይ ሠዓልያን ፑሽኪን በእርሳስ ንድፍ ፣ በቀለም ቅብ ፣ በውሃ ቀለም ቅብ ወዘተ የሠራቸው ምሥሎች አራት ሺህ የሚደርሱ ስብስቦች እና እጅግ በተከበሩ መዘክሮች እንዲሁም የትርኢት ሥፍራዎች ተቀምጠው የሚታዩ የጥበብ ወኀች መሆናቸውን በማስታወስ ነው።

# የትርጉም ስራችን ወዴት እያመራ ነው?

**በዮሐንስ ተፈራ /ኦስሎ ኖርዌይ/**

**መጽሐፍ ፡-** የኢትዮጵያ ታሪክ ከሰሎሞን ሥርወ መንግሥት እስከ አብዮቱ ውድቀት ( 2ኛ ዕትም ) ( የእንግሊዝኛው ርዕስ A History of Ethiopia ከማለቱ በስተቀር በትርጉሙ ላይ በንዑስ ርዕስነት የተጨመረው “ ከሰሎሞን ሥርወ መንግሥት እስከ አብዮቱ ውድቀት” የሚለው እ. ኤ. አቆጣጠር በ 1994 በታተመው የእንግሊዝኛ ዕትም ላይ የለም፡፡)

**ደራሲ፡-** ማርቆስ ሓሮልድ

**ትርጉም፡-** በሽፋን ገጽ ላይ ቴዎድሮስ ጸጋዬ ሲል በውስጥ ገጽ ላይ ደግሞ ዓለም ገረመው ይላል፡፡

ስለትርጉም ስራ መጀመሪያ የሰማሁትና ትርጉም የሚለውን ቃል ስሰማ ወደ አዕምሮዬ የሚመጣው ከመቅድመ ተዓምረ ማርያም “ ወመጽሐፈ ሥርዓቶሙሰ ተተርጎመት እምነገረ ዐረቢ ለግዕዝ ብሔረ ኢትዮጵያ በመዋዕለ ጳጳሳቲነ አባ ሚካኤል ወአባ ገብርኤል ወኤጲስ ቆጶስነ አባ ዮሐንስ እምአመ ወጽኡ ውስተ ብሔረ ኢትዮጵያ በ፲ ዓመት .“ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል በሚባሉ ጳጳሳት ዘመን አባ ዮሐንስም ኤጲስ ቆጶስነት በተሾመ ወራት ከግብጽ ወደ ኢትዮጵያ በወጡ በ፲ ዓመት ፣ የሥራታቸውም መጽሐፍ ከዐረብ ቋንቋ ለኢትዮጵያ ሰዎች በግዕዝ ቋንቋ ተተረጎመች” ( መቅድመ ተአምረ ማርያም) የሚለው ነው፡፡[1]

በኢትዮጵያ የመጻሕፍት ትርጉም ሥራ እጅግ የሚደነቅ የእውቀት ምንጭ ሆኖ የኖረና የተከበረ ሙያ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል ፡፡ እኔን በተመለከተ ግን በልጅነት ዘመኔ ስመ ጥር የነበሩትን አቶ ማሞ ውድነህን ፣ አቶ ተክለጻድቅ መኩሪያን ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌንና በየጊዜው ብቅ እያሉ እጅግ ጠቃሚ አበርክቶ ያደረጉትን ወጣት ተርጓሚዎች ሳስብ ከነሱም ስራ የተጠቀምኩትንና ያተረፍኩትን በረከት መለስ ብዬ ስቃኝ ዛሬም ለትርጉምስራና ለተርጓሚዎች ትልቅ አክብሮት አለኝ፡፡ አሁን ግን ይህ የተከበረ የትርጉም ስራ ደረጃው ወድቆና ተንገላትቶ የሚገኝበት ደረጃ ላይ የደረሰ ስለመሰለኝ በፍርሐትና የወደፊቱንም ሳስብ በስጋት ተሞልቻለሁ፡፡ በዚህም ምክንያት ዝም ማለት አልቻልኩም፡፡

ለዚህ አባባሌ መነሻ የሆነኝ አዲስ አበባ ከተማ ጥቅምት 17 ቀን 2014 ዓመተ ምሕረት ከኢትዮጵያ ታሪክ ጋር በተያያዘ ለማዘጋጀት ላሰብኩት ስራ ማመሳከሪያ ሊሆኑ ይችላሉ ካልኳቸው መጻሕፍት ውስጥ A History of Ethiopia by Marcus Harold, በሚል ርዕስ በማርቆስ ሓሮልድ የተጻፈውን መጽሐፍ የአማርኛ ትርጉም አዲስ አበባ ከብሔራዊ ትያትር ጀርባ ከሚገኙት የመጻሕፍት መሸጫዎች ከአንዱ ገዝቼ ወደ ቤቴ ከገባሁ በኋላ በጉጉት ለማንበብ ስዘጋጅ ያጋጠመኝ ነገር አሳዛኝ ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡

ለጊዜው አዲስ አበባ የምገኝ ሲሆን ያለሁትም በአጭር የእረፍት ጊዜና በተደራራቢ የስራ ጫና ውስጥ ቢሆንም ሁኔታው አሳዛኝ ሆኖ ስላገኘሁት ብቻ አለፍ አለፍ ብዬ ያገኘሁትን ከዚህ በታች በጥቂቱ በምሳሌነት ሳቀርብ እኔ በጭራሽ ስላልገባኝና እናንተ ምን ያህል ይገባችኋል ? የሚለውን ለአንባቢው ውሳኔ በመተው ነው፡፡

በመቀጠል በመጽሐፉ የውስጥ ይዘት ውስጥ የሚከተሉት ከተራ ቁጥር 1 እስከ 30 ለምሳሌነት ያቀረብኳቸው ለኔ ያልገቡኝና ምንም ትርጉም ሊሰጡኝ ያልቻሉ ሲሆን በኔ ዕምነት መጽሐፉ በጎግል ተተርጉሞ እንደወረደ ለመታተም የበቃ ነው የሚል ግምት ስላደረብኝ ለአንባቢ ፍርድ ይረዳ ዘንድ ለአብነት ከመጽሐፉ የሚከተሉተን ቀንጨብ አድርጌ አቅርቤያለሁና ተመልከቱት ፡፡

1. የእነሱ ዋና ትብብር ለኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነው ፣ እናም በመንደሮች የተደራጁ ናቸው ቀሳውስት እና ተጓዥ ቅዱስ ቅዱሳን የክርስትናን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገው በመመልከት በስነ ምግባር እና በሃይማኖታዊ የበላይት እንዲታመኑ ያደርጉላቸዋል (ገጽ 5)

**እንግሊዝኛው**

Their primary affiliation is to the Orthodox Church. And they are loosely organized into parishes. Priests and itinerant holy men keep the banner of Christianity high and drill their auditors to believe in their moral and religious superiority.( Page xi)

2. በኢትዮጵያ የደቡባዊ ክልሎች ውስጥ የተለያዩ ሕዝቦች ይኖራሉ፡፡ ከእነዚህም ወስጥ በጣም አስፈላጊ የሆኑት ሴሚካዊ ተናጋሪ ጉራጌ እና ኩሽቲክ ተናጋሪ የሆኑት ኮንሶና ሲዳማ ናቸው፡፡ (ገጽ 5)
3. ጉራጌዎች በአብዛኛው ሙስሊሞች ቢሆኑም በመካከላቸው አንዳንድ ክርስቲያኖችን ይመድባሉ (ገጽ 5)
4. በተጨማሪም **እጅግ አስፈላጊ የሆኑት የሱዳን** ሕዝቦች በኢትዮጵያ ምዕራባዊ ዳርቻ ይኖራሉ፡፡ (ገጽ 5) የኔ ጥያቄ (የማያስፈልግ ሕዝብ አለ)
5. መንግስቱ ኃይለማርያም 1974-1991) ... ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ስብጥርም ፍላጎት ነበረው፡፡ (ገጽ 5)
6. አቢሲስ..... እናም በጥሩ በተስተካከለ ሰረገላ እና ከአራት እጥፍ በላይ የሆነ አካል ነበረው፡፡ (ገጽ 13)
7. ንግድ ክብር እና ጠብ መንጃን የሚወስዱ ልሂቃንን እንዲጨምር የሚፈቅድ ሀብት አምጥቷል፡፡ በአረመኔያዊ ጦርነቶች የተፈጠሩ ምኞት እና ስግብግብነት ፣ ዕድልና ችሎታ ማጠናከሪያን አመጣ፡፡ እናም ስኬት ወደከፍተኛ ሃብት ፣ ብዙ ተከታዮች እና **ተጨማሪ ማስመሰል** አመራ፡፡(ገጽ 17)
8. የአክሱም ግዛት በአንደኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ማብቂያ ላይ **ወደ ሰፊው የተታመ ብርሃን ሲመጣ** ፣ በጥሩ ሁኔታ ካልተቀናጀ የተዋሃደ የንግድ ልውውጥ ነው (ገጽ 17)
9. በየመን የተሳካ ውጤት ጠላቶቻቸውን ያዳክማል ፣ ምናልባትም **ተጋሳጭነትን አያበሳጭም** (ገጽ 26)
10. የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን እንዲመራ የተመረጠችው የግብጽ ቅድመ ቅኝ ግዛት አገሪቷን ፖለቲካዋን ፣ ቋንቋዋን፣ ወይም ባሕሏን በደንብ አልገባችም ዜግዊስ ወደ ግብጽ ባለስልጣናት ለመዞር የፈለጉትን ወደ ሞንፊሽያ ፓትርያርክ ወደነበረበት ተንኮል ነገር ግን ኢትዮጵያን ወደ ጦር መሪዎች ትኩረት እንዲስብ እና በተዛባ እና በፍቅር መንገድ ወደ ምዕራቡ ዓለም እንዲመጣ በማድረግ ግብጽ **ግዛት ስማምስጥ ፈስጉ፡፡** (ገጽ 30)
11. መላው የፖለቲከ ምጣኔ ሀብት የተመሰረተው የእሳተ ገሞራ አፈር ውስጥ ረዘም ላለ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ለመዝራት እና ገበሬዎች በሚጠቀሙበት ገበሬ ላይ ነበር፡፡አዝመራው ከጥቅምት - ህዳር ወር በኋላ አዝመራው እህልና የምግብ ሸቀጣ ሸቀጦችን ለአካባቢያዊው ጌታ ግብር ሰጠው፣ እሱ ግን እጅግ በጣም ትልቅ ከሆነው ቤትና ከቀጠለ በስተቀር ፣እንደ ተገዢዎቹ በጣም የሚለምደው በአብዛኛው **በአገር ውስጥ በተሠሩ መሳሪያዎች ፣ በጨርቅ ነው ፡፡ ተንቀሳቃሽው ፍርድ ቤት በቀላሉ የሚንቀሳቀስ ነበር ፡፡** (ገጽ 31)
12. ባለፉት ምዕተ አመታት የኢትዮጵያ ዋና ዋና ከተማ በመሆኗ ከመላው ግዛቶች የመጡ መምህራንን እና አጋቾችን ሳበ፡፡ ዘረዓ ያዕቆብ እንኳ በብዙ ሃይማኖታዊ በራሪ ወረቀቶች ውስጥ ስሙን በማንሳት በሀብታም ባሕላዊ ሕይወት ውስጥ ተሳትፏል ፡፡አዲሱ ካፒታል የውጪውን ዓለም ፍላጎት እንኳ ቀልብሷል፡፡ ውጤቱም ንጉሡ ነገሥቱን ያስደስተዋል፡፡ (ገጽ 45)
13. **አካባቢው ንጉሠ ነገስቱ እስር ቤት እንዲገባ በጣም ሰፊ ነበር፣** እና ደጋማ አካባቢዎች በሞቃታማ እና ደረቅ በሆነ ሀገር ውስጥ በሙስሊሞች መካከል መኖርን ይጠሉ ነበር (ገጽ 47)

14. በመሃል ላይ ያለው በየጊዜው መከፋፈል በሰለስቲካዊ የፖለቲካ ኃይል ፍሰት ላይ **በሴንትሪልገጣ** ሃይሎች ተደምስሷል።በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ የቋንቋና ሃይማኖታዊ ትስስር ያላቸው ሰዎች በሰሜናዊ-ማዕከላዊ ከፍታ ቦታዎች ላይ ያተኮረ የበተችና የተዋሃደች አገር ነች። ዋናው ቦታው በቅርብ ጊዜ በተያዙት አውራጃዎች ደውሎ ነበር። ነዋሪዎቻቸው ቢያንስ እጅግ የላቁ ክርስቲያኖች እና አስተዳደራዊውም በባሕላዊ ግዛቶች ውስጥ የመንግስት መስሏል። (ገጽ 48)

15. በባህል ፣ በሃይማኖታዊ እና በኢኮኖሚያዊነቱ እና በአካባቢዎች ይለምዳሉ። ችግር በሚኖርበት ጊዜ ወይም በእውነቱ የንጉሳዊ አለመረጋጋት ፣ ሞት ወይም የተተካው መንግስት ኮንትራት ጀመረ። (ገጽ 49)

16. አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሃገር ውስጥ ማሰብን ቀጠሉ፣ እናም ለእነሱ መንግስት በግብር ፍላጎት ላይ ብቻ ራሱን የሚያንጸባርቅ ጨለማ አካል ነው።(ገጽ 49)

17. እሷ ለየት ያለ ብልህ ሰው ነች፤የፖለቲካ ተሰጥኦዋ ከዛራ ያቢብ መሪነት በባዳ ማርያም የግዛት ዘመን (1468-1478)ፍርድ ቤት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ላይ የወሰደችው መጀመሪያ ላይ ከሃዲያ ፣ ስሜቷ ለኢትዮጵያ ከሚያስችላቸው ሃብቶች ጋር ተጣምሮ ነበር፣ እናም የትምክሕት ምርጡ የንጉሠ ነገስቱ አነስተኛ ንጉሠ ነገስታዊ መንግስት እንደሆነች ያምናሉ። (ገጽ 49)

18. በዳ ማሪያም ግብር ለማዕከላዊ ቦታ እንዲሰጥ ከመከልከል ይልቅ መንገዱን ለመፈለግ ወደ መንገድ ሄደች (ገጽ 50)

19. ግን እንደ ቀድሞው ሁኔታ ያለመከሰስ ጉዳይ ምንም እንኳን የዘገው የኦሮሞና የቤተ እስራኤል አስፈላጊ ሕዝቦች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ክርስቲያናዊ ሴማዊ ተናጋሪ ሕዝቦችን ያካተተ በቀላሉ ሊወገድ የሚችል ማሕበራዊ ትብብራዊ ቡድን ነበር። በተረቂቶች በስተቀር ሰዎቹ የሰለሞናዊው መንግስት የፖለቲካ ምጣኔ ሃብት ውስጥ የሚኖሩት አርሶ አደሩ ገበሬ ነበር።ክርስቲያኖቻቸው በአንድ ወቅት ገዢዎቻቸው እጅግ በታም ትልቅ በሆነ ግዛት ሲይዙ እንደነበር ሁሉ መቼም አልረሱም፡እናም ኢትዮጵያዊነት በሰሎሞን ነገድ ስርወ መንግስት ስርወት ስራዎች ሕጋዊነት እንዲጨምር በማድረግ የፖለቲካ መሪን ወደ አለቃውና የገበሬው ጭንቅላት ውስጥ የገባ የፖለቲካ ሀሳብ ነበር (ገጽ 63)

20. የተሃድሶና የተሻሻለ ወታደራዊ በአዲሱ ኢትዮጵያ ውስጥ ግልጽ የሆነ ወሳኝ ሚና ነበረው። ሳራ ዴንጋ ብዙ ወታደሮችን በመመልመል አክሊል ቀጥታ ትዕዛዝ ስር ተጨማሪ ክፍሎችን አቋቋመ። (ገጽ 63)

21. መንትዮቹ የኦሮሞ-ሙስሊም ቀውሶች የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን ውጤታማነት በተመለከተ ጥያቄዎችን አስነስቷል።**ክርስቲያኖች ቀሳውስትን ንብረታቸውንን ክልላቸውን ለሙስሊሞች ትተው ለኦሮሞ መስጠታቸውን ስለሚቀጥሉ የቤተክርስቲያኒቱ ርዕዮተ ዓለም ጉድለት ነበረው።**የገዢው መደብ ክፍሎችለመዋጋት የገበሬን ውሳኔ ያዳከመው ወይም ከኦሮሞ መስፋፋት በስተጀርባ ያለውን ጫና የሚረዱ የግጭት አፈጻጸም አድናቆት የላቸውም ።እራሳቸውን እንከን የለሽ አድርገው የሚቆጥሯቸው በሆነ ምክንያት ፤የፍርድ ቤት ባለስልጣናት የኢትዮጵያ ጦር አዳዲስ ዘዴዎችን፣ እና ድጋፎችን የመፈለግ ፤የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መታደስ ያስፈልጋታል ሲሉ አስረድተዋል። (ገጽ 65)

22. ሃሳቦቻቸው የሚያነቃቃ ተጽዕኖ ባላቸው ፖረቹጋሊዎች በፍርድ ቤት ተቀባይነት ያላቸው ቄሶች ይመጣሉ።አጼ ገላውዴዎስ (እ ኤ. አቆጣጠር 1540-1559) በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተምሕሮዎች ላይ እምነት መታለን የሚያረጋግጥ ዝነኛ አምነት መግለጫን በመጻፍ ምላሽ ሰጡ። ከአምሳ አመት በኋላ እና ብዙ የኦሮሞ መስፋፋት ግዛቶች በኋላ ንጉሠ ነገሥት ዘ ዴንደር ከ (1603-1604)ቅድመ ተተኪው ቤተክርስቲያን ትምሕርት ውስጥ ያላቸውን እምነት ማካፈል አልቻሉም።እናም በተስፋና በምስጢር ወደ ሮማ ካቶሊክነት ተለወጡ። ከደረሰ በኋላ ወዲያውኑ በአሰቃቂ የክልል ንጉሶች ተወግዶ .. (ገጽ 65-66)

23. የፔዝ ትዕግስት የሌለው ተተካ፤አፈኒሶ ማዴን የተባለ ሌላ የስፔናዊው ኢዚት **የኢትዮጵያ ካቶሊክ ኢትሆፍ ቆጶስ** ሆኖ ከ 1625 በኋላ እንዲህ አይነት ለውጥ ተደረገ-፤፤የቅዱስ እናት የበታች ኢትዮጵያውያንን ነፍሳት ለማዳን አንድ ቀን መጠበቅ እንደማይችል ወሰነ። (ገጽ 67)

24. ጨካኝ ፖለቲከኛ ፤ዋና ከተማቸውን በኦሮሞ ወታደሮች፣ በአስተዳዳሪዎች እና በፍርድ ቤቶች ሲሞላ የተመለከቱትን **የአቢሲኒያ ወግ አጥባቂዎች ተፈጥሯዊ ጭንቀቶችን** ተጠቅሟል። ባሕላዊ እንደመሆናቸው፣ የሰሎሞናዊው መንግሥት በፍጥነት ወደ እስልምና አዝጋሚ ተንሸራታች እየቀነሰ እንደነበረ ያምናሉ፣ ዮአስ ታዋቂውን ሰው ከክርስቲያን አማላጅነት ወደ ምዕራብ በመዘዋወር ብቸኛው ኀል ያስቆጠረ ነው። (ገጽ 75)

25. አስገዳጅ የቤተክርስቲያን ጋብቻ አለመኖሩን እና በ 1820 አካባቢ ደጃዝማች አዲስ መመሪያ መርጣለች **እና አጼ ወንድ ልጅዋን ወደ ጎንደር ወሰዳት፣ ኃይለኛ መንስሔ የሆነውን ኮሶ በመሸጥ ኑሯቸውን ተመሪስች።** ለልጁ በበቂ ሁኔታ ማቅረብ ባለመቻሏ ደጃ በሚሆንበት ጊዜ ወደ ኪዋራ መልሷታል።(ገጽ 94)

26. ሆኖም በአጪር ጊዜ ውስጥ አውሮፓውያን ከምጽዋ አርባ አምስት ማይል ብቻ የሚሆኑ ደስ የሚሉ እና ጨዋ በሆኑት የቦጎስ **ተራሮች ሳቢዎችን ይስባሉ።** (ገጽ 130)

27. በሃዘን ወደ ቤት ሲዘዋወር ተበታትነው ነበር። **ራሰዝ አሳውላ እና ሚካይል የተባሉት** አነስተኛ ሀይሎች ብቻ ይዘው የሚቆዩ ናቸው።ሆኖም ምኒልክ በላስታ ፤ቤጄ፣ ጎጃም ፣ ወሎ ውስጥ ያሉ የአካባቢ ባለሥልጣናትን በማስረከቡ ሰሜኑን በኃይል በፍጥነት ተጓዘ። (ገጽ 137)

28. እ.ኤ.አ ማርች 1 ቀን ከምሽቱ 4 ሰዓት ምኒልክ ለህዝባቸው የክተት አዋጅ አስነገሩ። **ይህ የምግብ ሁኔታ ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት 2 ቀን በጦር ሰፈሩ እንዲመታ ያዘዘው ስለሆነ ኣሳዛኝ ጊዜ ነበር።** በርከት ያሉ መልዕክተኞችና ሯጮች ጠላት እየገሰገሰ መሆኑን ለመዘገብ በተጣደፉ ጊዜ የእፎታው ከፍተኛ መሆን አለበት። ( ገጽ 153)

29. **ቀደም ሲል ኢትዮጵያውያን ለአፍሪካ ወንድሞቻቸው ድንቁርናን እና ውርደትን** ያካፈሉበት ፣ ግን በድንገት ጉልበታቸው ፣ የእውቀት ብርሃን እና እድገታቸው ፣ ነባር ቀሳውስት ንቅናቄ እና ብልሹ ሥነ-ምግባርን በመጎበኘት የሚነቀፈው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አሁን እንደ መንፈስ ቅዱስ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ መንፈስ እውነተኛ ተሸከርካሪ ሆና ታየች።(ገጽ 155)

30. **እንደ ጃፓኖች የኢትዮጵያውያን ህዝብ በጥሩ ስነ ስርዓት አልተስተካከለም።** ግዛቱ አዲስ የተቋቋመ ሲሆን አስተዳደሩም አሁንም ሥርዓተ - ሥርዓቱ ነበር። (ገጽ 165)

**እንግሊዝኛው**

The Ethiopian People were not so well disciplined as the Japanese, the empire was newly established and its administration still rudimentary. (Page 106)

በአጠቃላይ በዚህ ወደ አማርኛ በተተረጎመው መጽሐፍ ላይ ዕጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ምንም ትርጉም የማይሰጡ የቃላት ክምችቶች መጽሐፍ ተብለው የቀረቡበት ሁኔታ መስሎ ስላገኘሁት ይህን የማንቂያ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ተገድጃለሁ። የጽሑፉ ዋና ዓላማም የሚከተለው ነው

1ኛ) መጽሐፉ ከአንድ ጊዜ በላይ መታታሙን እኔ የገዛሁት 2ኛ ዕትም ስለሚል በዚህ ማረጋገጥ ይቻላል። በዚህ መጽሐፍ ተርጓሚነት ስማቸው የተጠቀሰው ቴዎድሮስ ጸጋዬ / ዓለም ገረመው ወይም ማንኛውም ግለሰብ ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 25 ለጠቀስኩት ጥቅስ ማብራሪያ እንዲሰጡኝ እጠብቃለሁ። እኔ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ከሩብ ምዕተ አመት በላይ በውጪ አገር የኖርኩ በመሆኔ ምናልባትም በነዚህ 30 አመታት የአማርኛ ቋንቋ ለውጥ አሳይቶና ያልተረዳሁት ነገር ካለ ለመማርም ፈቃደኛ መሆኔን እገልጻለሁ፡

2ኛ) ጉዳዩን በባለቤትነት በመውሰድ መልስ የሚሰጥ ከጠፋ ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ የደራስያን ማሕበር፣ የትምሕርት ሚኒስቴር፣ የታሪክና የቅርስ ጉዳይ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች ወዘተ.. እንደዚህ አይነት በተለይም የአገርን ታሪክ በዚህ መንገድ ጽፎ፣ አሳትሞ በገበያ ላይ የሚያውል ማንኛውም አካልም ሆነ ግለሰብ በሕግ አግባብ የሚጠየቅበት፣ የሚታረምበት፣ ገበያ ላይ እየተሸጠ ያለውም ደረጃውን ያልጠበቀና ትክክለኛውን የደራሲውን መልዕክት የማያስተላልፍ ሆኖ ከተገኘ ተገቢው እርምጃ የሚወሰድበት መንገድ ካለ ለማሳሰብና የግሌን አስተያየት ለመስጠት ነው።